# <u>የኤርትራ ፡ ሕግጋት ፡ እንቆቅልሽ*</u>

ከፋሲል ፡ ናሆም**

የኤርትራ ፡ የፌዴራል ፡ አስተዳደር ፡ እንዲቀር ፡ በ፲፱፻፶፭*** ዓ. ም.[1] ውሳኔ ፡ ሲደረግ ፤ ውሳኔውን ፡ የሸኘው ፡ ሕጋዊ ፡ ቀዶ ፡ ጥገና ፡ የተሟላና ፡ የሚያጠግብ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ከአሥር ፡ ዓመታት ፡ በኋላ ፡ <u>በነባህታ ፡</u>[2] ፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ የተነሱ ፡ የሕግ ፡ ምስቅልቅሎች ፡ ይፈጠሩ ፡ ነበርን? ለዚህ ፡ ጥያቄ ፡ በቀላሉ ፡ መልስ ፡ ለማግኘት ፡ ቢያስቸግርም ፡ በ፲፱፻፵፪ ፡ ዓ. ም. «ስለሽፍቶች» ፡ የወጣው ፡ ሕግና ፡[3] ሌሎችም ፡ ተመሳሳይ ፡ ሕጎች ፡[4] እንደሚያመለክቱት ፡ እርግጠኛ ፡ ሆኖ ፡ የሚታየው ፡ በሕገ ፡ መንግሥትና ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ያስነሱት ፡ የተመሳቀለ ፡ የሕግ ፡ ችግር ፡ ሲሆን ፤ ሥረ ፡ መሠረታቸው ፡ የተያያዘው ፡ የፌዴራሉ ፡ አስተዳደር ፡ መቅረት ፡ ካስከተለው ፡ ያልተሟላ ፡ ቀዶ ፡ ጥገና ፡ ጋር ፡ ነው ። ስለዚህም ፡ በፍርድ ፡ ጉዳዮችና ፡ በተደነገጉ ፡ ሕጎች ፡ የተነሱት ፡ ምስቅልቅሎች ፡ ለየብቻቸው ፡ ሳይሆን ፡ ከጠቅላላው ፡ የኤርትራ ፡ ሕግጋት ፡ እንቆቅልሽ ፡ ጋር ፡ መመርመር ፡ ይኖርባቸዋል ። ይህንንም ፡ ረቀቅ ፡ ያለ ፡ የሕግ ፡ ችግር ፡ ለማስወገድ ፡ አጠቃላይ ፡ አስተያየቶችን ፡ መሠንዘር ፡ ለችግሩ ፡ መፍትሔ ፡ ለማስገኘት ፡ ይረዳ ፡ ይሆናል ፡ ተብሎ ፡ ተስፋ ፡ ይደረጋል ።

---

* ይህ ፡ ጽሑፍ ፡ በመጀመሪያ ፡ ሲታቀድ ፡ <u>ስለነባህታ ፡</u> ፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ ትችት ፡ ከመስጠት ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ የበለጠ ፡ አልነበረም ። ነገር ፡ ግን ፡ ወዲያውኑ ፡ የፍርድ ፡ ጉዳዩ ፡ በኤርትራ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ ስላለው ፡ እንቆቅልሽ ፡ መሠረታዊ ፡ ችግር ፡ ላይ ፡ በሚደረገው ፡ የመግቢያ ፡ ውይይት ፡ ላይ ፡ ከሚያስፈልጉት ፡ ነገሮች ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ ብቻ ፡ ሆኖ ፡ ተገኘ ። ጸሐፊው ፡ በጥር ፡ ወር ፡ በ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ. ም. በውጭ ባደረጉት ፡ የምርምር ፡ ጥናት ፡ ብዙ ፡ ነገሮችን ፡ ለማግኘት ፡ ችለዋል ። ደራሲው ፡ እርዳታቸው ፡ እጅግ ፡ አስፈላጊ ፡ ለነበረው ፡ ለብዙዎቹ ፡ የአሥመራ ፡ የጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍ/ቤት ፡ ዳኞች ፡ ሕግ ፡ አስከባሪዎችና ፡ ጠበቆች ፡ ባለውለታ ፡ ነው ። በቀዳማዊ ፡ ኃይለሥላሴ ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ የሕግ ፡ ፋክልቲ ፡ መምህራንና ፡ ሠራተኞች ፡ ላደረጉትም ፡ ፍሬያማ ፡ አስተያየት ፡ ምስጋና ፡ ይገባቸዋል ።

** አቶ ፡ ፋሲል ፡ ናሆም ፡ በቀ. ኃ. ሥ. ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ፋክልቲ ፡ ረዳት ፡ ፕሮፌሰር ፡ ናቸው ።

*** በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የፍርድ ፡ ጉዳዮች ፡ ውሳኔ ፡ ከተሰጠባቸው ፡ ዓ. ም. በስተቀር ፡ የተጠቀሰው ፡ ዘመን ፡ በሙሉ ፡ እንደአውሮፓውያን ፡ አቆጣጠር ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

1. የኤርትራን ፡ ፌዴራል ፡ አስተዳደር ፡ ለማስቀረትና ፡ በኤርትራ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ የአንድነት ፡ አስተዳደር ፡ ለመተካት ፡ የወጣ ፡ ትእዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፳፯ ፡ ፲፱፻፶፭ ፡ ዓ. ም. <u>ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡</u> ፳፪ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፫ ።
2. <u>እንባህታ ፡ ይግባኝ ፡ ባዮች ፡ ዓቃቤ ፡ ሕግ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡</u> የወንጀል ፡ ይግባኝ ፡ ቁጥር ፡ ፸፬/፶፫ ፡ በጠቅላይ ፡ ን. ነ. ፍ/ቤት ፡ አሥመራ ፡ ተበየነ ፡ አሥመራ ፡ ሰኔ ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ. ም. የፍርዱን ፡ ጉዳይ ፡ ሙሉ ፡ ቃል ፡ በዚህ ፡ መጽሔት ፡ እትም ፡ ገጽ ፡ ፪፻፷ ፡ ተመልከት ።
3. ስለሽፍቶች ፡ የወጣ ፡ ሕግ ፡ ፲፱፻፵፪ ፡ ዓ. ም. <u>በኤርትራ ፡ ጋዜጣ ፡</u> ቮልዩም ፡ ፲፱ ፡ ፲፱፻፵፪ ፡ ዓ. ም. ቁ. ፲፩ ። ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ተሻሽሏል ። ስለሽፍቶች ፡ የወጣው ፡ ሕግ ፡ (ከነማሻሻያዎቹ) ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. በኤ<u>ርትራ ፡ ጋዜጣ</u> ፡ ቮልዩም ፡ ፳፩ ፡ ቁ. ፲፩ ፤ በ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. ስለሽፍቶች ፡ የወጣ ፡ ሕግ ፡ (ከነማሻሻያዎቹ ፡ ፪ኛ) ፡ <u>በኤርትራ ፡ ጋዜጣ</u> ፡ ቮልዩም ፡ ፳፪ ፡ (፲፱፻፶ ፡ ዓ. ም.) ቁ. ፪ ፡ ስለሽፍቶች ፡ የወጣው ፡ ሕግ ፡ ከነማሻሻያዎቹ ፡ ሙሉው ፡ ቃል ፡ በተቀጥላ ፡ ፩ ፡ ሀ ላይ ፡ በገጽ ፡ 288 ፡ ተያይዞ ፡ ይገኛል ።
4. ስለሽፍቶች ፡ ከወጣው ፡ ሕግ ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ስላላቸው ፡ ወደፊት ፡ የምናገኛቸው ፡ ፪ቱ ፡ ሕጎች ፤ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ (ማሻሻያ ፡) ደንብ ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ. ም. ከአሁን ፡ ጀምሮ ፡ አንቀጽ ፡ ፬፻፴፯ሀ ፡ በመባል ፡ የታወቀው ፡ (የኤርትራ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ (ማሻሻያ) የሚገኘው ፡ <u>በኤርትራ ፡ ጋዜጣ</u> ፡ ቮልዩም ፡ ፲፯ (፲፱፻፵፯ ፡ ዓ. ም.) ቁ. ፲፯ና ፡ ስለጋራ ኃላፊነት ፡ የወጣ ፡ ሕግ ፡ (፲፱፻፶ ፡ ዓ. ም) ኤርትራ ፡ ጋዜጣ ፡ ቮልዩም ፡ ፳፪ ፡ ቁ. ፱ ፡ እነዚህም ፡ በተከታታይ ፡ በተቀጥላ ፡ ፩ሐ ፡ ገጽ ፡ 293ና ፡ በተቀጥላ ፡ ፩መ ፡ ገጽ ፡ 293-94 ፡ ላይ ፡ ተያይዘው ፡ ይገኛሉ ።

የፌዴራሉ ፡ አስተዳደር ፡ ሲቀር ፡ ሕጋዊ ፡ ችግሮቹ ፡ አልጠፉም ። በአሁኑ ፡ ጊዜ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ በማደናገር ፡ ረገድ ፡ ረቀቅ ፡ ያለው ፡ የሕግ ፡ ሥርዓት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ ሥርዓት ፡ ጋር ፡ በሙሉ ፡ የማይመሳሰል ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። የአስ ቸኳይ ፡ ጊዜ ፡ አዋጅ ፡ መታወጅ ፡ ለዚህ ፡ አጠራጣሪ ፡ ሁኔታ ፡ በግልጽ ፡ ተጨማሪ ፡ ነገር ፡ ነው ።[5] ሆኖም ፡ ይህ ፡ የሕግ ፡ እንቆቅልሽ ፡ የመነጨው ፡ ከኤርትራ ፡ የሕግ ፡ ታሪክ ፡ ብቻ ፡ በመሆኑ ፡ የፌዴራሉ ፡ አስተዳደር ፡ ሲያቆም ፡ አጥጋቢ ፡ መፍትሔ ፡ ሊገኝለት ፡ ይቻል ፡ እንደነበረ ፡ ይታመናል ።[6] እውነትም ፡ ከጥቂት ፡ ዓመታት ፡ በፊት የተደረገው ፡ የፌዴራሉ ፡ አስተዳደር ፡ መቅረት ፡ ኤርትራን ፡ በብዙ ፡ ዓመታት ፡ የተ ለየ ፡ ታሪኳ ፡ ያጠራቀመቻቸውን ፡ አስፈላጊ ፡ ያልሆኑ ፡ ሕግጋት ፡ በጠቅላላ ፡ ገንጥሎ ፡ ለመጣል ፡ አመች ፡ ጊዜ ፡ ነበር ። የኤርትራ ፡ ሕግ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ አስፈላጊ ፡ ያልሆኑ ጉዳዮችን ፡ ቢያጠቃልል ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ መሠረታዊ ፡ ችግሩ ፡ የሕግ ፡ ችግር ፡ ነው ። ይህንንም ፡ ለማስተዋል ፡ የኤርትራን ፡ ዘመናዊ ፡ የሕግ ፡ ታሪክ ፡ በአጭሩ ፡ መመል ከት ፡ ይገባል ።

## ፩. የኤርትራ ፡ የሕግ ፡ ታሪክ ፡ (፲፰፻፹፪—፲፱፻፶፬ ፡ ዓ. ም.)

የሕጋዊ ፡ ችግሮች ፡ ሥረ ፡ መሠረቶች ፡ ወደአንድ ፡ መቶ ፡ ዓመታት ፡ ይጠጋል ። በ፲፰፻፹፪ ፡ ዓ. ም. አቅኚው ፡ የጣሊያን ፡ መንግሥት ፡ ቅኝ ፡ ግዛት ፡ አድርጎ ፡ ኤርት ራን ፡ ከሠየማት ፡[7] ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ በየጊዜው ፡ እየተከታተሉ ፡ ለ፶ ፡ ዓመታት ፡ ያህል ፡ የወጡት ፡ ሕጎች ፡ በጣሊያንኛ ፡ ቋንቋ ፡ በአዋጅ ፡ እየጸደቁ ፡ ነበር ። የጣሊያንም ፡ ሕጋዊ ፡ ሥልጣን ፡ የተመሠረተው ፡ በጣሊያን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የበላይ ፡ ገዥነት ፡ ነበር ። ስለዚህም ፡ በዚች ፡ ቅኝ ፡ ሀገር ፡ የነበሩት ፡ ሕግጋት—ቅኝ ፡ ግዛቱንም ፡ እንዲ

---

5. ስለአስቸኳይ ፡ ጊዜ ፡ ሁኔታ ፡ አዋጅ ፡ በኤርትራ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ በአንዳንድ ፡ ስፍራዎች ፡ የአስቸ ኳይ ፡ ጊዜ ፡ ሁኔታ ፡ መኖሩን ፡ ስለማስታወቅ ፡ የወጣ ፡ ትእዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፷፯ ፡ ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ. ም፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፴ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፯ ፡ ተመልከት ። የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቁጥር ፡ ፫፻፺፮ ፡ ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ. ም. በኤርትራ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ በአንዳንድ ፡ ሥፍራዎች ፡ የአስቸኳይ ፡ ጊዜ ፡ ሁኔታ ፡ ስለመኖሩ ፡ ለማስታወቅ ፡ የወጣ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፴ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁ. ፯ ፡

6. በተለይ ፡ ሊታወስ ፡ የሚገባው ፡ የኤርትራ ፡ ሕግጋት ፡ ሁሉ ፡ የወጡት ፡ የአስቸኳይ ፡ ጊዜ ፡ ሁኔታ ፡ ከመ ታወጁ ፡ ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፡ ከአሥር ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ነበር ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ የአስቸኳይ ፡ ጊዜ ፡ ሁኔ ታው ፡ የታወጀው ፡ በጅኦግራፊ ፡ ተከልሎ ፡ "በኤርትራ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ በአንዳንድ ፡ ሥፍ ራዎች" ብቻ ፡ ሲሆን ፤ የኤርትራ ፡ ሕግጋት ፡ ግን ፡ በመላው ፡ የኤርትራ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ይውላሉ ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ የኤርትራ ፡ ሕግጋትና ፡ የአስቸኳይ ፡ ሁኔታ ፡ አዋጅ ፡ በቦታም ፡ ሆነ ፡ በጊዜ ፡ አይመሳሰሉም ። በኋላ ፡ እንደምናየው ፡ የፖለቲካ ፡ አጥፊዎች ፡ የሚከሰሱት ፡ በኤርትራ ፡ ሕግጋት ፡ መሠረት ፡ አይደለም ። በእንደዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ጊዜ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ይውላል ። እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ምክንያቶች ፡ የኤርትራ ፡ ሕግጋት ፡ እንቆቅልሽ ፡ ከኤርትራ ፡ የሕግ ፡ ታሪክ ፡ የመነጨ ፡ በመሆኑ ፡ ከአስቸኳይ ፡ አዋጁ ፡ ተለይቶ ፡ መመርመር ፡ አለበት ፡ ወደሚለው ፡ መደምደሚያ ፡ በቀጥታ ፡ ይመራሉ ።

7. በታሪክ ፡ እንደምንመለከተው ፡ ይህ ፡ ክፍለ ፡ ሀገር ፡ የጥንቱ ፡ የአክሱም ፡ መንግሥት ፡ ክፍል ፡ ነበር ። በእስላሞች ፡ መምጣትና ፡ የበጃ ፡ ነገዶች ፡ የቆላውን ፡ የባህር ፡ ጠረፍ ፡ በመያዛቸው ፡ ምክንያት ፡ የአ ክሱም ፡ መንግሥት ፡ ተከፋፈለ ። በሚቀጥሉት ፡ ጥቂት ፡ መቶ ፡ ዓመቶች ፡ ምን ፡ እንደተደረገ ፡ ያለን ፡ እ ውቀት ፡ አነስተኛ ፡ ነው ። በመካከለኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ መጨረሻ ፡ አካባቢ ፡ ይኸው ፡ ክፍለ ፡ ሀገር ፡ በባላባቶች ፡ ነገሥታት ፡ ሥር ፡ የባህረ ፡ ነጋሽ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ ሆኖ ፡ ነበር ። በባህሩ ፡ አካባቢ ፡ (በተለይም ፡ ምፅዋ) የሚገኘው ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የኦቶማን ፡ ግዛት ፡ (ኢምፓየር) የመጨረሻ ፡ ደቡባዊ ፡ ወሰን ፡ ሆኖ ፡ ይቆጠር ፡ ነበርና ፡ በየተራ ፡ በቱርኮችና ፡ በግብጾች ፡ ፓሻዎች ፡ ተገዝቷል ። አውሮፓውያን ፡ አፍሪካን ፡ ለቅኝ ፡ ግዛት ፡ በሚቃረጡበት ፡ ዘመን ፡ ይህ ፡ ከኤርትራ ፡ ባህር ፡ በስተምዕራብ ፡ የሚገኘው ፡ አካባቢ ፡ ኤርትራ ፡ ተብሎ ፡ የጣሊያን ፡ የመጀመሪያ ፡ ቅኝ ፡ ግዛት ፡ ሆነ ።

ያጠቃልሉ ፡ ከተደረጉት ፡ ደንበኛ ፡ የጣሊያን ፡ ሕጎች ፡ በስተቀር—[8] የወጡት ፡ ሕጎች ፡ ለማመንጨት ፡ በሚያስችሉት ፡ ከሮማ ፡ በወጡት ፡ መሠረታዊ ፡ ሕግጋት ፡ መሠረት ፡ ነበር ። የእንግሊዝ ፡ ወታደራዊ ፡ አስተዳደር ፡ የኤርትራን ፡ አስተዳደር ፡ ሥልጣን ፡ በ፲፱፻፵፩ ፡ ዓ. ም. በተረከበ ፡ ጊዜ ፡ ይኸው ፡ የሕግ ፡ አቋም ፡ በሙሉ ፡ እንዳለ ፡ ሳይነካ ፡ ቆይቷል ።[9] የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ በኤርትራ ፡ ላይ ፡ የነበረው ፡ ሥልጣን ፡ ጊዜያዊ ፡ ጠባይ ፡ ብቻ ፡ ያለው ፡ ሳይሆን ፤[10] አንድ ፡ መንግሥት ፡ እተረከበው ፡ እጠላት ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ የነበረውን ፡ ሕግና ፡ ኢንስቲቲዩሽኖች ፡ እንዳይለውጥ ፡ የሚከለክለውን ፡ የሔግን ፡ ስምምነት ፡ ውል ፡ በተጨማሪ ፡ ማክበር ፡ እንዳለበት ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ተሰማው ።[11] በኋላም ፡ የእንግሊዝ ፡ ወታደራዊ ፡ አስተዳደርና ፡ የበላይ ፡ ተጠባባቂነት ፡ በኤርትራ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ለውጥ ፡ ሲያመጣ ፤ በእንግሊዘኛና ፡ በጣሊያንኛ ፡ ቋንቋዎች ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ በከፊል ፡ የተለያዩ ፡ ክፍሎችን ፡ በማሻሻል ፡ ነበር ።[12]

የፌዴራሉ ፡ አስተዳደር ፤[13] የ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ. ምህረቱን ፡ አዲስ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከማስገኘቱ ፡ በስተቀር ፡ የነበረውን ፡ የሕግ ፡ ሥርዓት ፡ እንዳለ ፡ ትቶታል ።[14] አዳዲስ ፡ ሕጎችም ፡ በጣሊያንኛና ፡ በእንግሊዘኛ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፤ በተጨማሪም ፡ የኤርትራ ፡ ሕገመንግሥት ፡ የኦፊሲዩል ፡ ቋንቋ ፡ ባደረጋቸው ፡ በአረብኛና ፡ በትግርኛም ፡ ይወጡ ፡ ነበር ።[15] በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ከወጡት ፡ ሕግጋት ፡ አንዱ ፡ በ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. ስለ ሽፍቶች ፡ የወጣው ፡ ሕግ ፤[16] ሲሆን ፤ በነባህታ ፤[17] ፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ የተዳከመ ፡ ቢሆንም ፡ ከፍተኛ ፡ ቦታ ፡ ስለአለው ፡ በሚቀጥለው ፡ ጽሑፍ ፡ እንመለከታለን ።

ለማጠቃለል ፡ ያህል ፤ እንደተመለከትነው ፡ እስከ ፡ ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ. ም. ድረስ ፡ የኤርትራ ፡ የሕግ ፡ ሥርዓት ፡ በጣሊያንኛ ፤ በእንግሊዝኛ ፤ በትግርኛና ፡ በአረብኛ ፡ እንደ

---

8. እንደጣሊያን ፡ ፍትሐብሔር ፡ ሕግና ፡ እንደጣሊያን ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ያሉት ፡ ስምምነቶችም ፡ ሁሉ ፡ ይችን ፡ ቅኝ ፡ ግዛት ፡ እንዲያጠቃልሉ ፡ ተደርገዋል ። ለምሳሌ ፡ ስለዚህ ፡ ሁኔታ ፡ የጸሐፊውን ፡ አስተያየት ፡ "የኢንተርናስዮናል ፡ ሕግ ፡—በአገሮች ፡ መካከል ፡ ስለሚደረግ ፡ የሙሉ ፡ ገዥነት ፡ መረካከብ ፡" በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ቮልዩም ፡ ፭ ፡ ቁ. ፡ ፩ ፡ ገጽ ፡ ፪፻፪—፪፻፬ ፡ (፲፱፻፷፫ ፡ ዓ. ም) ተመልከት ።
9. ጂ. ኬ. ኤን. ትሬቫስኪስ ፡ ኤርትራ ፡ ኤ. ኮለኒ ፡ ኢን ፡ ትራንዚሽን ፡ (፲፱፻፵፩—፲፱፻፶፪ ፡ ዓ. ም.) ገጽ ፡ ፹፬—፹፯ ፡ በኦክስፎርድ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ፕሬስ ፡ ሎንደን ፡ (፲፱፻፷ ፡ ዓ. ም.)
10. ምንም ፡ እንኳ ፡ አሥመራ ፡ ከጣሊያን ፡ ነፃ ፡ የሆነችው ፡ በሚያዝያ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፵፩ ፡ ዓ. ም. ቢሆንም ፡ ፪ኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ እስከ ፡ ፲፱፻፵፭ ፡ ዓ. ም. ድረስ ፡ አላለቀም ፡ ነበር ። የሠላም ፡ ውል ፡ የተፈረመው ፡ በ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ. ም. ነበር ።
11. ትሬቫስኪስ ፡ እላይ ፡ እተጠቀሰው ፡ መጽሐፋቸው ፡ ውስጥ ፡ ገጽ ፡ ፳፬ ፡
12. የጣሊያንኛ ፡ ቋንቋ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲቆይ ፡ የተደረገበት ፡ ዋናው ፡ ነገር ፡ ምቹ ፡ በመሆኑ ፡ ነው ።
13. ለኦፊሴላዊው ፡ የኤርትራ ፡ ፌዴራል ፡ አስተዳደር ፡ አቋቋም ፡ "የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ኰሚሽነር ፡ በኤርትራ ፡ የመጨረሻው ፡ ራፖር" ተመልከት ። የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ጠቅላላ ፡ ስብሰባ ፡ ሰባተኛው ፡ መደበኛ ፡ ስብሰባ ፡ ተጨማሪ ፡ ቁጥር ፡ ፲፭ ፡ (A/፪ሺ፻፹፰) ኒው ፡ ዩርክ ፡ (፲፱፻፶፪ ፡ ዓ.ም.)
14. በአንቀጽ ፡ ፺፮ ፡ የኤርትራ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ እንደሚለው ፡ ማናቸውም ፡ ሕጎችና ፡ መምሪያዎች ፡ በሚያዝያ ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፩ ፡ ዓ. ም. በሥራ ፡ ላይ ፡ ያሉና ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ በአስተዳደሩ ፡ ሥልጣን ፡ ያልተደመሰሱትና ፡ በዚህ ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ የወጡት ፡ ሕጎችና ፡ መምሪያዎች ፡ በሕግ ፡ እንደ ፀኑ ፡ ይቆያሉ ። በሕጎቹና ፡ በመምሪያዎቹ ፡ እንዲሁም ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ መካከል ፡ አለመስማማት ሲኖር ፡ የኋለኛው ፡ የሚፀና ፡ መሆኑን ፡ አንቀጽ ፡ ፺፮ ፡ (፪) በግልጽ ፡ ይናገራል ።
15. የኤርትራ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፴፰ ፡ (፩)
16. የግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፫ ፡ ተመልከት ።
17. የግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፪ ፡ ተመልከት ።

ነገሩ ፡ ተውጣጥቶ ፡ የተዘጋጀ ፡ ሲሆን ፤ ኤርትራ ፡ በዓለም ፡ አቀፍ ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ የወረሰችው ፡ የማያስተማምንና ፡ ያልተረጋጋ ፡ ዕድል ፡ ነው ።[18]

ኢትዮጵያም ፡ ከ፲፱፻፴፬ ፡ ዓ. ም. ጀምራ ፡ በየጊዜው ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡[19] በአማርኛና ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ብዙ ፡ ሕጎችን ፡ በአዋጅ ፡ አጽድቃ ፡ ካወጣች ፡ በኋላ ፤ ከ፲፱፻፵፱ ዓ. ም. እስከ ፡ መጀመሪያዎቹ ፡ ፲፱፻፷ ፡ ዓ. ም. ድረስ ፡ በኮድ ፡ መልክ ፡ በተፋጠነ ፡ ሁኔታ ፡ ስታወጣ ፤[20] ለአዲሱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ ሥርዓት ፡ መሠረቱ ፡ በ፲፱፻፵፰፡ ዓ. ም. ተሻሽሎ ፡ የወጣው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ነበር ።[21] ይህ ፡ አዲስ ፡ የሕግ ፡ አቋም ፡ በአሥመራ ፡ በኩል ፡ ሲታይ ፡ ላለው ፡ ችግር ፡ አዲስ ፡ ተጨማሪ ፡ ስፋት ፡ ሰጥቶታል። የፌዴራሉና ፡ የእንግሊዝ ፡ አስተዳደሮች ፡ እንዲሁም ፡ የቅኝ ፡ አገዛዝ ፡ ሕጎች ፡ (በጠቅላላው ፡ የኤርትራ ፡ ሕግጋት ፡) ሕጋዊ ፡ ረቂቅነት ፡ እንደአዳንድ ፡ ችግር ፡ ሆነው ፡ ቢወሰዱ ፤ ከ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. በኋላ ፡ የወጣው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ በኤርትራ ፡ ላይ ፡ የሚኖረውን ፡ ውጤት ፡ ለመወሰን ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ። እዚህ ፡ ላይ ፡ አተኩረን ፡ መመልከት ፡ ያለብን ፡ ይህ ፡ ልብወለድ ፡ ትምህርታዊ ፡ የምርምር ፡ ጉዳይ ፡ ሳይሆን ፡ በእርግጥ ፡ ሲደረግ ፡ የሚታይ ፡ ነገር ፡ ነው ። በተለይም ፡ የኤርትራ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አጽድቆ በኤርትራ ፡ ላይ ፡ እንዲሠራባቸው ፡ የፈቀዳቸው ፡ ሕጎች ፡ እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ያሉት ፡ ናቸው ።[22] በ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ. ም. የፌዴራሉ ፡ አስተዳደር ፡ ማለቅና ፡ ኤርትራ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ሆና ፡ መቀላቀል ፡ ይህንን ፡ ሥርዓት ፡ ሕጋዊ ፡ ለማድረግ ፡ በአእምሮ ፡ የማውጠንጠንን ፡ ችግር ፡ ለማስወገድ ፡ እትብቱን ፡ ቆርጦ ፡ ችግሮቹን ፡ ማጥፋት ፡ ይቻል ፡ እንደነበር ፡ ግልጽ ፡ ነው ፤ እንደአጋጣሚ ፡ ሆኖ ይህ ፡ ሊሆን ፡ አልቻለም ።

18. የፌደራሉ ፡ አስተዳደር ፡ ሕግ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የፈረመበት ፡ ኦፊሲዮላዊ ፡ የአማርኛ ፡ ቅጅ ፡ እንዳለ ፡ መገንዘብ ፡ ያስፈልጋል ።

19. ከጠላት ፡ ወረራ ፡ በፊት ፡ ሕጎች ፡ በኦፊሲዮላዊው ፡ ጋዜጣ ፡ በብርሃንና ፡ ሠላም ፡ በአማርኛና ፡ በፈረንሳይኛ ፡ ወጥተው ፡ ነበር ።

20. ሕጎቹና ፡ ኦፊሲየላዊው ፡ አጠራራቸው ፡—
የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፤ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፻፶፰ ፤ ፲፱፻፵፱ - ዓ. ም. ፲፮ኛ ፡ ዓመት ፤ በተለይ ፡ የወጣ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ቁጥር ፡ ፩ ።
የባህር ፡ ሕግ ፤ በ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ. ም. የወጣ ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፻፷፬ ፤ ፲፱ኛ ፡ ዓመት ፡ በተለይ ፡ የወጣ ፤ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ቁ. ፩ ።
የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ. ም. የወጣ ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፻፷፭ ፤ ፲፱ኛ ዓመት ፤ በተለይ ፡ የወጣ ፤ ነጋሪት ፤ ጋዜጣ ፤ ቁጥር ፡ ፪ ።
የንግድ ፤ ሕግ ፤ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፻፷፮ ፡ በ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ. ም. ፲፱ኛ ፡ ዓመት ፤ በተለይ ፡ የወጣ ፤ ነጋሪት ፤ ጋዜጣ ፡ ቁጥር ፡ ፫ ።
የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፤ የአዋጅ ፡ ቁጥር ፡ አልተሰጠውም ፤ ፳፩ኛ ፡ ዓመት ፡ በ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ. ም. በተለይ ፡ የወጣ ፤ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፤ ቁጥር ፡ ፩ ።
የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፤ ድንጋጌ ፡ ቁጥር ፡ ፶፪ ፤ ፳፭ ፡ ዓመት ፡ በ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ. ም. በተለይ ፡ የወጣ ፤ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፤ ቁጥር ፡ ፩ ።

21. የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፤ ፲፭ኛ ፡ ዓመት ፤ ቁጥር ፡ ፪ ። የመጀመሪያውን ፡ የ፲፱፻፳፫ ዓ. ም. የኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥትን ፡ ሽሮታል ።

22. የ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ምቱ. የኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ኤርትራንም ፡ እንዲያጠቃልል ፡ መስከረም ፡ ፲ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፩ ፡ ዓ. ም. የኤርትራ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ በሕግ ፡ ተቀብሎት ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ እንደራሴ ፡ ህዳር ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ በአዋጅ ፡ አጸደቀው ። የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ (ኤርትራን ፡ የሚያጠቃልል ፡) ሕግ ፡ በ፲፱፻፶፩ ፡ ዓ. ም. የወጣውን ፡ የኤርትራ ፡ ጋዜጣ ፡ ቮልዩም ፡ ፳፭ ፡ ቁጥር ፡ ፲፪ ፡ ተመልከት ። በተቀጥላ ፡ ፩መ ፡ ገጽ ፡ ፩፻፶፫ ፡ ተያይዞ ይገኛል ። ነገር ፡ ግን ፡ የተገኘው ፡ ኦፊሴላዊው ፡ ግልባጭ ፡ በጣልያንኛ ፡ ቋንቋ ፡ ነው ።

የፌዴራሉ ፡ አስተዳደር ፡ በተፈጸመበት ፡ ጊዜ ፡ የኤርትራን ፡ ሕግጋት ፡ በሚመለከቱ ፡ ሁኔታዎች ፡ ላይ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ሦስት ፡ መሠረታዊ ፡ አማራጮች ፡ ነበሯት ። እነሱም ፡ ሁለት ፡ ቀላል ፡ አቋራጭ ፡ መንገዶችና ፡ አንድ ፡ ጠቅላላ ፡ ለውጥ ፡ ለማካሄድ ፡ የሚያስችል ፡ ነበር ። ላይ ፡ ላዩን ፡ ስንመለከተው ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ያልሆኑትን ፡ ፀንተው ፡ የሚሠራባቸውን ፡ ማናቸውንም ፡ ሕጎች ፡ በሙሉ በማጥፋት ፡ ሁሉንም ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕጎች ፡ ብቻ ፡ በከመቅጽበት ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ እንዲሠሩ ፡ ማድረግ ፡ ትክክለኛ ፡ ጥበብ ፡ ነገር ፡ ይመስላል ። ይህንን ፡ አቋራጭ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ከሕግ ፡ ውጭ ፡ የሆኑ ፡ አስተያየቶችን ፡ በማስተዋል ፡ሳይ ጠቀምበት ፡ ቀርቷል ። በተቻለ ፡ መጠን ፡ አነስተኛ ፡ የሆነ ፡ የሕዝቡን ፡ የዕለት ፡ ኑሮ፡ የሚነካ ፡ ለውጥ ፡ ተፈላጊ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ ብንወስድ ፡ ይህ ፡ ዓይነቱ ፡ ጊዜያዊ ፡ የሕግ ፡ ሥርዓት ፡ መመሰቃቀልን ፡ በመፍጠር ፡ የሚገኝ ፡ መፍትሔ ፡ የማያስፈልግ ፡ ጩኸትና ፡ ኡኡታን ፡ ያስከትላል ። ይህ ፡ መፍትሔ ፡ በተለይም ፡ በመንግሥቱ ፡ አስተዳደር ፡ ውስጥ ፡ ተካፋይ ፡ የሆኑትን ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ፖሊሶች ፡ የጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ የሕግ ፡ አስከባሪዎች ፡ ጠበቆች ፡ ዳኞች ፡ የሕግ ፡ አማካሪዎችና ፡ የማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ ሠራተኞችን ፡ አስፈላጊ ፡ የሚሆነውን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕግ ፡ እንዲፈልጉ ፡ ያስገድዳቸው ፡ ነበር ።[23]

ሕጋዊ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ ብቻ ፡ ስንመለከተው ፡ መፍትሔው ፡ ተፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ አይገኝም ። የረቀቁትን ፡ ዘመናዊ ፡ ሕጎች ፡ አተረጓጐም ፡ የሚያመጡት ፡ ችግርና ፡ በተጨማሪ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የወጡት ፡ ሕጎች ፡ ቅጅ ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ በብዛት ፡ እንዲገኙ ፡ ለማድረግ ፡ ያለው ፡ የአስተዳደር ፡ ችግር ፡ በአንዳንድ ፡ ቦታዎች ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕግ ፡ የሚመሳሰሉ ፡ ለማግኘት ፡ የሚፈልጉ ፡ እንዳያገኙ ፡ አድርጓቸዋል ። ቀደም ፡ ብለው ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ሕጎች ፡ ተሟልተው ፡ የነበሩት ፡ ክፍሎች ፡ በአሁኑ ፡ የሕግ ፡ ሥርዓት ፡ በድንገት ፡ ያልተሟሉ ፡ ቦታዎች ፡ ተፈጥረው ፡ በግልጽ ፡ ይገኛሉ ። ምሳሌዎችን ፡ ለመጥቀስ ፡ ያህል ፡ ይህ ፡ ዕድል ፡ የሚደርሳቸው ፡ ክፍሎች ፡ ከሠራተኛና ፡ አሠሪ ፡ ግንኙነትና ፡[24] የኢንዱስትሪ ፡ ንብረት ፡ መብቶች ፡[25] ጀምሮ ፡ የማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ ስለጤንነትና ፡ የህንጻ ፡ ሥራ ፡ ያወጣቸውን ፡ ደንቦች ፡ እንዲሁም ፡ ጫካና ፡ የዱር ፡ አራዊት ፡ ጥበቃ ፡[26] ደንቦችን ፡ ያጠቃልላል ። ከኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ጋር ፡ የሚመሳሰለውን ፡ ክፍል ፡ በአንዳንድ ፡ ሁኔታዎች ፡ ከኤርትራ ፡ ሕግ ፡ የተለየ ፡ መፍትሔ፣

23. በመጀመሪያ ፡ የሚያጋጥመው ፡ የታወቀው ፡ የቋንቋ ፡ ችግር ፡ ለዚህ ፡ ተጨማሪ ፡ ነው ። በዚህ ፡ የቋንቋና ፡ የሕግ ፡ ችግር ፡ ለመጀመሪያ ፡ ምርምር ፡ በአርክቦርና ፡ ፋሲል ፡ ናሆም ፡ "ቋንቋ ፡ በፍርድ ፡ ቤት" በሚል ፡ ርዕስ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቋንቋ ፡ ጥናት ፡ በሚል ፡ መጽሐፍ ፡ ላይ ፡ በመታተም ፡ ላይ ፡ ስለሆነ ፡ ተመልከት ።

24. በአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ መካከል ፡ ባለው ፡ ግንኙነት ፡ ላይ ፡ ስላለው ፡ ችግር ፡ የተደረገ ፡ ጥሩ ፡ ትችት ፡ ሮበርት ፡ ሚንስ ፤ "የ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ. ም. የኤርትራ ፡ ሠራተኛ ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ያለው ፡ አቋም ፡" በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ የመጽሔት ፡ ቮልዩም ፡ ፫ ፡ ቁ. ፩ ፡ (፲፱፻፷፰ ፡ ዓ. ም. ) ተመልከት ።

25. ፒተር ፡ ዊንሸፕ ፡ "የእንዱስትሪ ፡ ንብረት ፡ መብት ፡ በኢትዮጵያ" በዚህ ፡ እትም ፡ ገጽ ፡ ፫፻፵፯ ላይ ፡ በሚገኘው ፡ ጽሑፋቸው ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ በቂ ፡ የሆኑ ፡ የቅጂ ፡ አገዛዝ ፡ ሕጎች ፡ ስለአሉ ፡ መላው ፡ ኢትዮጵያን ፡ የሚያጠቃልሉ ፡ አዲስ ፡ ሕጎች ፡ በፍጥነት ያስፈልጋሉ ፡ ይላሉ ።

26. በሌላ ፡ መስክ ፡ ደግሞ ፡ በኤርትራ ፡ ጋዜጣ ፡ ቮልዩም ፡ ፳፩ ፡ ቁ. ፪ ፡ (፲፱፻፶፬ ፡ ዓ. ም.) የሚገኘው ፡ የድሃ ፡ መከላከያ ፡ ጠበቃ ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓትና ፡ ለጠበቆች ፡ በሞያቸው ፡ በመከራከር ፡ ስለ ፡ አገልግሎት ፡ የሚከፈላቸውን ፡ አበል ፡ ይደነግጋል ። እንደዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ሕግ ፡ ለሌላው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ መዳረስ ፡ ይኖርበታል ።

እንዲገኝለት ፡ ሕጉ ፡ ማድረግ ፡ ነበረበት ።[27] ስለዚህ ፡ እንደዚህ ፡ ዓይነቶቹ ፡ ችግሮች ፡ ሁሉ ፡ ይህንን ፡ አጭር ፡ መንገድ ፡ ከመከተል ፡ አይቀሩም ፡ ነበር ። አጋጣሚ ፡ ሆኖ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ይህንን ፡ ምርጫ ፡ ላለመውሰድ ፡ ወሰነ ። ሆኖም ፡ ችግሩን ፡ በትእዛዝ ፡ ፳፯ ፡ እንደተመለከተው ፡ ለማስወገድ ፡ መረጠ ።[28]

> ይህንን ፡ ለመሸፈን ፡ የወጣው ፡ ትእዛዝ ፡ ፳፯ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ደንግጓል ። በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ ፀንተው ፡ የሚሠራባቸው ፡ ወይም ፡ የፌዴራል ፡ አቋም ፡ በመኖሩ ፡ ምክንያት ፡ የወጡት ፡ ሕጎች ፡ አዋጆችና ፡ ደንቦች ፡ በሙሉም ፡ ሆነ ፡ በከፊል ፡ ለአስተዳደሩ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆነው ፡ እንዲሠራባቸው ፡ የሚያስፈልጉት ፡ ሁሉ ፡ ወደፊት ፡ በሚወጡ ፡ ሕጎች ፡ ተሰርዘው ፡ እስኪተኩ ፡ ድረስ ፡ እንዳሉ ፡ ፀንተው ፡ የሚሠራባቸው ፡ ይሆናሉ ። ያሉትም ፡ የአስተዳደር ፡ ድርጅቶች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ሆነው ፡ እነዚህኑ ፡ ሕጎች ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ መዋላቸውን ፡ እንዲቀጥሉ ፡ ያደርጋሉ ።[29]

ትእዛዝ ፡ ፳፯ን ፡ ላይ ፡ ላዩን ፡ ስንመለከተው ፡ አነስተኛ ፡ የመከላከልን ፡ መስመር ፡ በመከተል ፡ የሕጉ ፡ ሥርዓት ፡ ቢያንስም ፡ ቢበዛም ፡ እንዳለ ፡ እንዲቆይ ፡ ያደርጋል ። ሕጐቹ ፡ ሁሉ ፡ በግልጽ ፡ እስከተሻሩ ፡ ድረስ ፡ እንዳሉ ፡ የፀኑና ፡ የሚሠራባቸው ፡ ሕጎች ፡ ሆነው ፡ ይቀራሉ ። ቢሆንም ፡ "ለአስተዳደሩ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆነው ፡ እንዲሠራባቸው ፡ የሚያስፈልጉት" የሚል ፡ ከሕጉ ፡ የተለየ ፡ ድንጋጌ ፡ ተጨምሮ ፡ ይገኛል ። ይህም ፡ ትእዛዝ ፡ የታቀደው ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ የተራው ፡ ሕዝብ ፡ የኑሮ ፡ ሁኔታ ፡ እንዳይበላሽ ፡ መሆኑን ፡ በግልጽ ፡ ሲያስረዳም ፡ ማንኛውም ፡ የኤርትራ ፡ ሕግ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ፀንቶ ፡ እንዳለ ፡ ሊቆይ ፡ የሚችለው ፡ ለዚችው ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ አስተዳደር ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደሆነ ፡ ብቻ ፡ መሆኑን ፡ ይገልጻል ። ይህም ፡ ማለት ፡ ማንኛውም ፡ ሕግ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ሲውል ፡ ለኤርትራ ፡ አስተዳደር ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ እንዲሠራበት ፡ ማስፈለጉ ፡ ወይም ፡ አለማስፈለጉ ፡ መጠየቅ ፡ አለበት ። በሌላ ፡ አነጋገር ፡ ትእዛዝ ፡ ፳፯ ፡ የሚኖረው ፡ ውጤት ፡ ማንኛውንም ፡ ሕግ ፡ በኤርትራ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ጽኑነት ፡ አጠራጣሪ ፡ ያደርገዋል ።[30]

ይህ ፡ የአጭር ፡ መንገድ ፡ መፍትሔ ፡ አንድ ፡ ሕግ ፡ የኤርትራን ፡ አስተዳደር ፡ ሥራ ፡ በመቀጠል ፡ ለማካሄድ ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ ወይም ፡ አለመሆኑን ፡ የሚወስነው ፡ ማን ፡ እንደሆነ ፡ መልስ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ጥያቄ ፡ ነው ። ለዚህ ፡ ጥያቄ ፡ ትእዛዝ ፡ ፳፯ ፡ መልስ ፡ አይሰጥም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ሕጎችን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ ግዴታ ፡ የተጣለበት ፡ ባለሥልጣን ፡ ይህንንም ፡ ጥያቄ ፡ ለመመለስ ፡ የሚችል ፡ ይመስላል ፡ ብለን ፡ ለመገመት ፡ እንችላለን ። በተሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ያልረካው ፡ ባለጉዳይ ፡ እንደነገሩ ፡ ውጤት ፡ ሕጉ ፡ አያስፈልግም ፡ ስለዚህ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ሊውል ፡ አይገባውም ፤ ወይም ፡ ያስፈልጋል ፡ ስለዚህ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ መዋል ፡

27. በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ የሥራ ፡ ግብር ፡ አገማመት ፡ ዘዴና ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ አሁንም ፡ ቢሆን ፡ ፍጹም ፡ የተለየ ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ በሌሎች ፡ የኢትዮጵያ ፡ ግዛቶች ፡ ነጋዴዎች ፡ ትርፋቸውንና ፡ (ኪሣራቸውን) በዓመት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ መግለጽ ፡ (ማስታወቅ) ፡ ሲኖርባቸው ፡ በኤርትራ ፡ ግን ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ተቋቁሞ ፡ በነበረው ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ መሠረት ፡ በዓመት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ መግለጽ ፡ ይኖርባቸዋል ።

28. የግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ፩ ፡ ተመልከት ።

29. ትእዛዝ ፡ ፳፯ ፡ አንቀጽ ፡ ፪ ።

30. ማንኛውም ፡ የኤርትራ ፡ ሕግ ፡ አጠራጣሪ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ለመደምደም ፡ ሕጉ ፡ "አስፈላጊ ፡" አይደለም ፡ በሚለው ፡ ወገን ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ የማረጋገጥ ፡ ግዴታና ፡ ሕጋዊ ፡ ለመሆኑ ፡ ወይም ፡ ላለመሆኑ ፡ በግምት ፡ መቀበል ፡ አስፈላጊ ፡ አይደለም ።

አለበት ፡ በማለት ፡ ይግባኝ ፡ ለማለት ፡ ይችላል ። ለምሳሌ ፡ አንድ ፡ በሕግ ፡ ላይ ፡ የተመረኰዘ ፡ አስተዳደርን ፡ የሚመለከት ፡ ውሳኔ ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ "ለአስተዳደሩ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆነው ፡ እንዲሠራባቸው ፡ የሚያስፈልጉ" ፡ አይደሉም ፡ ብሎ ፡ የሚያስበው ፡ ወገን ፡ ባለሥልጣኖች ፡ በአስተዳደር ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ የይግባኝ ፡ መብቱን ፡ እስኪጨረስ ፡ ድረስ ፡ ለበላይ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ይግባኝ ፡ ማለት ፡ ይችላል ።

በማናቸውም ፡ የፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ነገሩን ፡ ባለጉዳዩ ፡ ወደፍርድ ፡ ቤት ፡ በመውሰድ ፡ ይህንኑ ፡ ጭብጥ ፡ በማንሳት ፡ ክርክር ፡ የተነሳበት ፡ ሕግ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ሊውል ፡ አይገባም ፡ ለማለት ፡ ይችላል ። በፍርድ ፡ ቤት ፡ ባለው ፡ የበታችና ፡ የበላይ ፡ አቋሞች ፡ መሠረት ፡ ከበታች ፡ ወደበላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ብዙ ፡ ይግባኞች ፡ ይኖራሉ ። በማናቸውም ፡ የአስተዳደርም ፡ ሆነ ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ይግባኝ ፡ ላይ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ሕጉ ፡ የማያስፈልግና ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ሊውል ፡ የማይገባው ፡ መስሎ ፡ ሲታያቸው ፡ ነገሩ ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ አያቆምም ። ክሱ ፡ መጀመሪያ ፡ ወደተነሳበት ፡ ተመልሶ ፡ በሌላ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ውሳኔ ፡ ይሰጣል ። በአንድ ፡ በተለየ ፡ የፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ፣ ካሉ ፡ ችግሮች ፡ ሌላ ፡ በአንድ ፡ ባለሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ በሌሎች ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ወይም ፡ ተመሳሳይ ፡ ጭብጦች ፡ ባሏቸው ፡ በሌሎች ፡ የፍርድ ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ፣ ያለው ፡ ውጤት ፡ በየትኛውም ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ አይገኝም ።[31] ለአስተዳደሩ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆነው ፡ እንዲሠራባቸው ፡ የሚያስፈልጉት ፡ ሕጎች ፡ ሁሉ ፡ ፀንተው ፡ ይኖራሉ ፡ የሚለው ፡ ወሰን ፡ ያልተበጀለት ፡ ድንጋጌ ፡ ውጤቱ ፡ ሕጋዊ ፡ ምስቅልቅሎችን ፡ ማብዛት ፡ ነው ። ምንም ፡ እንኳን ፡ ትእዛዝ ፡ ፳፯ ፡ ዋና ፡ ዓላማው ፡ በፊት ፡ የነበሩትን ፡ ሕግጋት ፡ ጽኑነት ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ ለመጠበቅ ፡ ቢሆንም ፡ የሚኖረው ፡ ሕጋዊ ፡ ውጤት ፡ ጠቅላላውን ፡ የኤርትራን ፡ ሕግጋት ፡ አጠራጣሪ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ መጣል ፡ ነው ። ሁኔታውም ፡ ከኋላ ፡ የቀረ ፡ ታሪካዊ ፡ አይደለም ። ለወደፊቱ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ አጠቃላይ ፡ መፍትሔ ፡ ካልተገኘ ፡ በቀር ፡ በትእዛዝ ፡ ፳፯ ፡ ላይ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ሥሩን ፡ የሰደደው ፡ መፍትሔ ፡ ምንም ፡ የሕጉ ፡ ሥርዓት ፡ የተስተካከለ ፡ ባይሆን ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በምጥ ፡ ስቃይ ፡ ላይ ፡ ይገኛል ። የኤርትራ ፡ የሕግ ፡ ታሪክም ፡ ሆነ ፡ የሕግ ፡ ችግሮች ፡ ከተለመዱት ፡ ለየት ፡ ያሉ ፡ በመሆናቸውና ፡ ያልተለመዱ ፡ መፍትሔዎች ፡ ስለማይጠይቁ፡ በሠፊው ፡ በታቀደው ፡ ቀዶ ፡ ጥገና ፡ ችግሩን ፡ ከማውጣት ፡ በስተቀር ፡ ሌላ ፡ መፍትሔ ፡ ለኤርትራ ፡ ሕግጋት ፡ እንቆቅልሽ ፡ ለማግኘት ፡ አይቻልም ።

### ፫. <u>የባህታ ፡ ፍርድ ፡ ጉዳይ</u> ።

ምናልባት ፡ አንድ ፡ የኤርትራን ፡ ሕግ ፡ አስፈላጊነት ፡ ጥርጣሬ ፡ ላይ ፡ የሚጥለው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ የሚፈለገውን ፡ ነገር ፡ በትክክል ፡ አሟልቶ ፡ እንደሚሸፍን ፡ በማሳየት ፡ ነው ። ሆኖም ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ አንድን ፡ ሕግ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ማዋል ፡ ሕጋዊነትና ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊነት ፡ ማንሳት ፡ ሌላው ፡ መንገድ ፡ ነው ። በፊታችን ፡ ያለው፡ የፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ በሁለቱም ፡ ነጥቦች ፡ ላይ ፡ ለመተቸት ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ የሆነ ፡ አጋጣሚ ፡ የሚሆነው ፡ <u>በነባታ ፡ ፍርድ</u> ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ በኤርትራ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ ሁለቱ፡ ዓይነት ፡ ችግሮች ፡ ስለሚነሱ ፡ ነው ። በዚህ ፡ በሕግ ፡ በኩል ፡ አስደናቂ ፡ በሆነው፡

31. ችግሩ ፡ አንድ ፡ ባለሥልጣን ፡ የሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ በሌሎች ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ውጤት ፡ በግልጽ ፡ ክፍ ፡ ያለ ፡ የጥያቄ ፡ ክፍል ፡ ነው ። ምናልባትም ፡ የተሰጡት ፡ ውሳኔዎች ፡ በውሳኔ ፡ ሰጭዎቹ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ እየተመደቡ ፡ ተከፋፍለው ፡ የውሳኔዎቹን ፡ ውጤቶች ፡ በየክፍል ፡ ክፍላቸው ፡ መተንተን ፡ ይሻል ፡ ይሆናል ።

የፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ አቃቤ ፡ ሕጉ ፡ በ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. ስለሽፍቶች ፡ ከወጣው ፡ ሕግ ፡[32] ውስጥ ፡ ክፍል ፡ ፪ ፡ ፫ና ፡ ፬ን ፡ ጥሳችኋል ፡ ብሎ ፡ ብዙ ፡ ተከሳሾችን ፡ ከሰሰ ። የክሱ ፡ ፍሬ ፡ ነገሮችና ፡ ሕጋውያን ፡ ጭብጦቹ ፡ ተመሳሳዮች ፡ ናቸው ። ከፍተኛ ፡ ፍ/ቤት ፡ የትግሬ ፡ ጠ/ግዛት ፡ ነዋሪዎች ፡ የሆኑትን ፡ አምስቱን ፡ ተከሳሾች ፡ ጠብመንጃ ፡ ወይም ሌላ ፡ ፈንጂ ፡ መሣሪያ ፡ ይዘው ፡ በመወንበድ ፡ጥፋተኛ ፡ ሆነው ፡ አግኝቷቸዋል ። ሰኔ፡ ፳፯ ፡ ፲፱፻፳፯ ፡ ዓ. ም. በኤርትራ ፡ በባረንቱ ፡ አጠገብ ፡ በሱዳን ፡ ጠረፍ ፡ በኩል ፡ ከሁለት ፡ ሰዎች ፡ ፪፻፸፡ ከብቶችን ፡ ዘርፈው ፡ ነበር ። የተከሳሾቹ ፡ ጠበቃ ፡ ለጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍ/ቤት ፡ ለይግባኝ ፡ ካቀረባቸው ፡ አቤቱታዎች ፡ መካከል ፡ ክሱ ፡ ስለሽፍቶች ፡ በወጣው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ መታየት ፡ እንዳልነበረበት ፡ አመልክቷል ። ለዚሁም ፡ ሁለት ፡ ምክንያቶችን ፡ አቅርቦ ፡ ነበር ። ፩ኛ/ በዚህ ፡ ክስ ፡ ላይ ፡ ስለሽፍቶች ፡ የወጣውን ፡ ሕግ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ማዋል ፡ በሕግ ፡ እኩል ፡ ሆኖ ፡ መጠበቅን ፡ ከሚደነግገው ፡ ከተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ጋር ፡ ይቃረናል ። ፪ኛ/ አስፈላጊ ፡ ከሆነም ፡ ክሶቹ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ መቅረብ ፡ አለባቸው። በትእዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፳፯ ፡ እንደተገለጸው ፡ የተከሳሾቹ ፡ ጠበቃ ፡ ሁለተኛ ፡ አቤቱታ ፡ የተመሠረተው ፡ ስለ ፡ ሽፍቶች ፡ የወጣው ፡ ሕግ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ክሱ ፡ የተመሠረተባቸው ፡ ክፍሎች ፡ ለአስተዳደሩ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆነው ፡ እንዲሠራባቸው ፡ የሚያስፈልጉ፡ ናቸው ፡ የሚል ፡ ክርክር ፡ ነው ፤ ምክንያቱም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ የወንጀል ፡ ነክ ፡ ስለሆኑ ፡ ጉዳዮች ፡ ሁሉ ፡ በደንብ ፡ አጠቃሎ፡ ይዟል ። ምናልባት ፡ ክሶቹ ፡ ስለሽፍቶች ፡ ከወጣው ፡ ሕግ ፡ ይልቅ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መሠረት፡ ሲታዩ ፡ ግልጽ ፡ የሆኑ ፡ ጥቅሞችን ፡ አገኛለሁ ፡ ብሎ ፡ የተከሳሾች ፡ ጠበቃ ፡ አስቦ ፡ ይሆናል ። የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በይበልጥ ፡ ሰብአዊ ፡ ርኅራኄ ፡ ያለበትና ፡ ስለቅጣት ፡ ያለው ፡ ዝንባሌ ፡ ይበልጥ ፡ የላላ ፡ ነው ። ይህም ፡ ስለሽፍቶች ፡ ከወጣው ፡ ሕግ ፡ ጽኑና ፡ አስገዳጅ ፡ ከሆኑት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ጋር ፡ ሲነፃፀር ፡ ለፍ/ቤቱ ፡ ቅጣትን ፡ ስለ ፡ መወሰኑ ፡ ጉዳይ ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ ሥልጣን ፡ ይሰጠዋል ። ጠቅላይ ፡ ን ፡ ነ ፡ ፍ/ቤት ፡ ክሶቹ ፡ በተሳሳተ ፡ ሕግ ፡ ተመስርተው ፡ ሲያገኛቸው ፡ የከፍተኛውን ፡ ፍ/ቤት ፡ ውሳኔ

32. «የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ስለያዙ ፡ ሽፍቶች ፡»

፪. ሁለት ፡ ወይም ፡ ከዚህ ፡ የበለጡ ፡ ሰዎች ፡ የጋራ ፡ ዓላማቸው ፡ ማናቸውንም ፡ የኃይል ፡ ሥራ ፡ ለመፈጸም ፡ ከሆነና ፡ ቢያንስ ፡ ቢያንስም ፡ አንዳቸው ፡ ጠብመንጃ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ፈንጅ ፡ መሣሪያ ፡ ከያዙ ፡ ፍ/ቤቱ ፡ ቅጣቱን ፡ የሚያቃልልበት ፡ በጣም ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ ምክንያት ፡ ካላገኘ ፡ በቀር ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ከአምስት ፡ ዓመት ፡ በማያንስ ፡ እሥራት ፡ ይቀጣሉ ።

፩ኛ/ <u>የቅጣት ፡ ማክበጃ ።</u>

፫. በአንቀጽ ፡ ፪ ፡ የተመለከተውን ፡ ወንጀል ፡ በመፈጸም ፡ ጥፋተኛ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ከአሥር ፡ ዓመት ፡ በማያንስ ፡ እሥራት ፡ የሚቀጣው ፡ የሽፍቶች ፡ አባል ፡ ሆኖ ፡ ከምግብ ፡ ዝርፊያ ፡ ሌላ ፡ ኃይልን ፡ በመጨመር ፡ ማናቸውም ፡ ወንጀል ፡ ፈጽሞ ፡ በተገኘ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

፪ኛ/ <u>የቅጣት ፡ ማክበጃ ።</u>

፬. በአንቀጽ ፡ ፪ ፡ የተመለከተውን ፡ ወንጀል ፡ በመፈጸም ፡ ጥፋተኛ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በአሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ በማያንስ ፡ እስራት ፡ የሚቀጣው ፤

(፩) የሽፍቶቹ ፡ አባል ፡ ሆኖ ፡ ከምግብ ፡ ዝርፊያ ፡ ሌላ ፡ ሁለት ፡ የኃይል ፡ ወንጀሎችን ፡ መፈፀሙ ፡ የተረጋገጠበት ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፤

(፪) የኃይል ፡ ወንጀሉ ፡ ከመፈጸሙ ፡ በፊት ፡ ጥቂት ፡ አስቀድሞ ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ከሽፍቶቹ ፡ አንዱ ፡ ጠብመንጃ ፡ የተኮሰ ፡ ወይም ፡ ፈንጅ ፡ መሣሪያ ፡ ያፈነዳ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ።

አፍርሶ ፡ ክሱ ፡ እንደገና ፡ እንዲታይ ፡ ያዛል ፡[33] ብሎ ፡ በጠበቃው ፡ ዘንድ ፡ ተስፋ ፡ መደረጉ ፡ የተሳሳተ ፡ አይደለም ። በሁለቱም ፡ መንገዶች ፡ በኩል ፡ የጠበቃው ፡ ተስፋ ሳይቃናና ፡ ቀረ ፤ ምክንያቱም ፡ ጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍ/ቤት ፡ ይግባኙን ፡ አልቀ በልም ፡ አላለም ፡ ወይም ፡ ፍርዱን ፡ አልለወጠም ። በበታች ፡ ፍ/ቤት ፡ የተወሰነውን ፡ የአሥር ፡ ዓመት ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ደግፎታል ። የተከሳሾቹ ፡ ጠበቃ ፡ በዋናው ፡ ክስ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ቢሸነፍም ፡ ቅሉ ፡ በሕጋዊ ፡ ክርክሮች ፡ በኩል ፡ በማሸነፍ ፡ ጠቃሚ ፡ ለሆኑ ፡ ሁለት ፡ ጭብጦች ፡ በር ፡ ከፈተ ።[33ሀ]

ይህም ፡ የነባህታን ፡ ፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ በተለያዩ ፡ ሁለት ፡ ምክንያቶች ፡ የተንሣ ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ በኩል ፡ ከፍተኛ ፡ ያደርገዋል ። በአንድ ፡ ጊዜ ፡ ሁለት ፡ ጠቃሚ ፡ የሕግ ፡ ጭብጦችን ፡ ስለሚገልጽ ፡ የነባህታ ፡ ፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ በአንድ ፡ ድንጋይ ፡ ሁለት ፡ ዎፎችን ፡ እንደገደለ ፡ ይቆጠራል ። በጣም ፡ ሰፊ ፡ ከሆኑት ፡ ሁለት ፡ ምክንያ ቶች ፡ አንዱ ፡ ብቻ ፡ ይበቃ ፡ ነበር ፡ በማለት ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ጉዳዩን ፡ በሌላ ፡ ይተረ ጉሙትና ፡ ከተፈላጊነት ፡ በላይ ፡ አድርገው ፡ ይመለከቱት ፡ ይሆናል ። ፍ/ቤቱ ፡ ስለሽ ፍቶች ፡ የወጣውን ፡ ሕግ ፡ መጠቀምን ፡ አጥብቆ ፡ የሚቃወሙ ፡ ከባድ ፡ ክርክሮች ፡ እንደአጋጣሚ ፡ ለማግኘት ፡ ቻለ ። እነዚህም ፡ ሁልጊዜ ፡ ለጭብጦቹ ፡ ደንብን ፡ የተከ ተሉ ፡ መልሶች ፡ አልነበሩም ። የተያያዙም ፡ አልነበሩም ። አንዳንዶቹ ፡ ከሌሎች ፡ በይበልጥ ፡ በሰፊው ፡ የሚያወሩ ፡ ነበሩ ። ጥቂቶች ፡ ክፍል ፡ ፫ና ፡ ፬ ፡ ተፍቀዋል ፡ ሲሉ፣ ሌሎቹ ፡ ደግሞ ፡ ስለሽፍቶች ፡ የወጣው ፡ ሕግ ፡ እራሱ ፡ በሙሉ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ አይው ልም ፡ ለማለት ፡ ሞክረዋል ። ስለሽፍቶች ፡ የወጣውን ፡ ሕግ ፡ ጨርሶ ፡ እስከመተው ፡

33. "ፕሮፌሰር ፡ ሮናልድ ፡ ስክላር ፡ እንደገለጹልኝ ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍ/ቤት ፡ ውሳኔውን ፡ እንዲያፈር ስና ፡ እንደገና ፡ ክሱ ፡ መሰማት ፡ እንዲጀምር ፡ ለማዘዝ ፡ የሚያስችለው ፡ ስልጣን ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ይግባኝ ፡ በሚለው ፡ (ስልጣን) ፡ አንቀጽ ፡ በግልጽ ፡ አልተሰጠም ። ቁጥር ፡ ፫፻፰ ፡ አንዳንድ ፡ ይግባኝ ፡ የማየት ፡ ስልጣን ፡ ይሰጣል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ፍ/ቤቱ ፡ ውሳኔን ፡ ስለ ማፍረስ ፡ የክሱ ፡ እንደገና ፡ መሰማት ፡ እንዲጀምር ፡ ለማዘዝ ፡ የሚያስችል ፡ ስልጣን ፡ አልተሰጠም ። ምንም ፡ እንኳን ፡ ይህ ፡ ሥልጣን ፡ በቁጥር ፡ ፫፻፰ ፡ የሌለ ፡ ቢሆንም ፡ የኢትዮጵያ ፡ የይግባኝ ፡ ሰሚ ፡ ፍ/ ቤቶች ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡ ሥልጣን ፡ ተጠቅመውበታል ። አእምሮ ፡ ንጉሤ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ አቃቤ ፡ ሕግ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፤ የአዲስ ፡ አበባ ፡ ከፍተኛ ፡ ፍ/ቤት ፡ የወንጀል ፡ ይግባኝ ፡ መዝገብ ፡ ቁጥር፣ ፪፻፲፫/፶፰ ፡ ፲፱፻፷፯ ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፷፱ ፡ "የኢትዮጵያ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡" የሚል ፡ በዚ. ፊሸር ፡ የተጻፈውን ፡ መጽሐፍ ፡ በገጽ ፡ ፩፻፴ ፡ ላይ ፡ ተመልከት ፤ እንዲሁም ፡ ፊሸር ፡ ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ያቀረቧቸውን ፡ ትችቶች ፡ በገጽ ፡ ፩፻፴፮ ያለውን ፡ አስተውል ። የይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍ/ቤት ፡ የበታች ፡ ፍ/ቤት ፡ የሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡ የሚያስለ ውጥ ፡ የሕግ ፡ ስህተት ፡ ሲያገኝ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ተከሳሹ ፡ ጥፋተኛ ፡ በመሆኑ ፡ ቅጣት ፡ የሚገባው ፡ ቢሆን፣ ይህን ፡ ሥልጣን ፡ በመጠቀም ፡ ክሱን ፡ መጀመሪያ ፡ ክሱ ፡ መስማት ፡ ወደተጀመረበት ፡ የበታች ፡ ፍ/ ቤት ፡ በመምራት ፡ ሙሉ ፡ የክስ ፡ መስማት ፡ እንዲጀመር ፡ ማዘዝ ፡ በእርግጥ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። የክሱ ፡ መጀመሪያ ፡ ሰሚ ፡ ፍ/ቤት ፡ እንደገና ፡ ሙሉ ፡ የክስ ፡ መሰማት ፡ የሚደረግበት ፡ ትክክለኛ ፡ ቦታ ፡ ነው ። ቁጥር ፡ ፫፻፰ ፡ ለይግባኝ ፡ ሰሚ ፡ ፍ/ቤቶች ፡ ይህን ፡ አስፈላጊ ፡ ሥልጣን ፡ ባለመስጠቱ ፡ የሚያሳዝን ፡ ነገር ፡ ነው ። ሁልጊዜ ፡ አለመሟላትን ፡ ከዚያም ፡ መደበላለቅን ፡ የሚያስከትለውን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ይግባኝ ፡ የመስማት ፡ ስልጣኖችን ፡ ለመዘርዘር ፡ ሞክሯል ። ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ የሚመረ ጠው ፡ ይህ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ለይግባኝ ፡ ሰሚ ፡ ፍ/ቤት ፡ በጠቅላላው ፡ አስፈላጊና ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ ከታየው ፡ ማንኛውም ፡ የፍትህ ፡ ዓይነት ፡ የመስጠት ፡ ሥልጣን ፡ ቢያ ጐናጽፈው ፡ ይሻል ፡ ነበር ።"

33ሀ. "ይህ ፡ በጠቅላላው ፡ የማይኖር ፡ ልዩነት ፡ ነው ። በሕጋዊ ፡ ክርክሮች ፡ ማሸነፍ ፡ በፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ የተለየ ፡ ውጤት ፡ ያስከትላል ። ቢሆንም ፡ ፍ/ቤቱ ፡ በዚህ ፡ ፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ ክሱ ፡ የተመሠረተው ፡ በተ ሳሳተ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ መሆኑን ፡ ከተረዳ ፡ በኋላ ፡ ወዲያውኑ ፡ የክሱ ፡ መመስረቻ ፡ ሕግ ፡ ስለሽፍቶች ፡ ከወጣው ፡ ሕግ ፡ ወደወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ እንዲለወጥ ፡ ወሰነ ። ከዚያም ፡ በኋላ ፡ በተተኪው ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ ባለው ፡ ቅጣት ፡ ከተመለከተው ፡ ጋር ፡ ስለሚስማማ ፡ ፍ/ቤቱ ፡ የፊተኛውን ፡ ፍርድ ፡ ወዲ ያውኑ ፡ አጸናው ። ምንም ፡ እንኳን ፡ ጊዜ ፡ ቢቆጥብ ፡ ቅሉ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓቱ ፡ ያልተስተካከለ ፡ ይመስ ላል ።"

ያዘነበለው ፡ የፍ/ቤት ፡ አስተሳሰብ ፡ እነዚህን ፡ ሁሉ ፡ ክርክሮች ፡ ስላመጣና ፡ አንዳዶቹም ፡ እግብ ፡ ላይ ፡ ሳይደርሱ ፡ ስለቀሩ ፡ በሁለቱ ፡ የሕግ ፡ ጭብጦች ፡ መሃከል ፡ ያለውን ፡ ልዩነት ፡ የማማታት ፡ ዝንባሌን ፡ አሳይቶአል ። በዚህ ፡ የተነሳ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ፍ/ቤቱ ፡ ቢያየውና ፡ ውሳኔ ፡ ቢሰጥበትም ፡ አንዳንድ ፡ ትልልቅ ፡ ችግሮች መፍትሔ ፡ ሳይገኝላቸው ፡ ይጐተታሉ ። ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ ፍ/ቤት ፡ ከክፍል ፡ ፪ ፡ ፫ና ፬ ፡ሌላ ፡ ስለሽፍቶች ፡ የወጣው ፡ ሕግ ፡ በጥቅም ፡ ላይ ፡ ውሎ ፡ እንዲቆይ ፡ ይቻል ፡ ወይም ፡ አይቻል ፡ እንደሆነ ፡ ስላለው ፡ ሐሳብ ፡ በጣም ፡ ግልጽ ፡ አይደለም ።[34]

የሆነው፡ ሆኖ፡ የተጠቀሱት፡ ሁለት፡ ነጥቦች፡ ከሁለት፡የተለያዩ፡ ክፍሎች ፡ የመነጩ ፡ ናቸው ። አንድ ፡ የተጠቀሰው ፡ ጭብጥ ፡ ስለሽፍቶች ፡ የወጣውን ፡ ሕግ ፡ ተፈፃሚ ፡ ማድረግ ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ መልኩን ፡ ይገልጻል ። ስለአንድ ፡ሕግ በግብር ፡ ማዋል ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊነት ፡ የሚያነሳ ፡ ጉዳይ ፡ ጥቂት ፡ ቢሆንም ፡ ራሱ በጣም ፡ ትልቅ ፡ ትርጉም ፡ ያዘለ ፡ ነው ። ከዚህም ፡ ቀጥሎ ፡ ከትእዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፳፯ ፡ በፊት ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ ተፈፃሚነት ፡ የነበረው ፡ ሕግ ፡ አሁንም ፡ የፀና ፡ መሆኑ ፡ የሚያስጠይቅ ፡ ነው ። ይህም ፡ ጭብጥ ፡ ዕለታዊ ፡ የተለምዶ ፡ ጥቅም ፡ ያለውና ፡ ይህ፡ የምርምር ፡ ጽሑፍ ፡ እንዲቀርብ ፡ ካደረጉት ፡ ዋና ፡ ምክንያት ፡ ነው ። ሁለቱም ፡ነገሮች ፡ ማስተዋልን ፡ ስለሚጠይቁ ፡ በአጭሩ ፡ ይተነተናሉ ።

<u>ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ ጭብጥ</u> ፡— "ስለሽፍቶች ፡ የወጣው ፡ ሕግ ፡ ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አይስማማም ፡" በማለት ፡ የተከሳሾች ፡ ጠበቃ ፡ ላቀረበው ፡ ክርክር ፡ ፍ/ቤቱ፡ መልስ ፡ ሲሰጥ ፡ በገሃድና ፡ በግልጽ ፡ ስለሽፍቶች ፡ የወጣው ፡ ሕግ ፡ "ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አይስማማም ፡" ብሏል ። ቢሆንም ፡ ፍ/ቤቱ ፡ ስለሽፍቶች ፡ የወጣው ፡ ሕግ ፡ <u>እራሱ</u> ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ አይደለም ፡ አላለም ። ስለሽፍቶች ፡ የወጣውን ፡ ሕግ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ማዋል ፡ ጐጅ ፡ በመሆኑ ፡ ይህ ፡ ፍ/ቤቱ ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ ሳይሆን ፡ ያገኘው ፡ ነጥብ ፡ አንዳንድ ፡ ማብራሪያዎችን ፡ የሚጠይቅ ፡ ስለሆነ ፡ ፍ/ቤቱ ፡ ያቀረበውን ፡ ምክንያት ፡ ማየት ፡ ይበጃል ።

እነዚህ ፡ በፍ/ቤቱ ፡ የተጠቀሱት ፡ የክርክር ፡ ክፍሎች ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ በሕግ ፡ እኩል ፡ ሆኖ ፡ መጠበቅ ፡ በሚለው ፡ ፅንስ ፡ ሀሳብ ፡ ላይ ፡ የተመሠረቱ ፡ ናቸው ። ሕግን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ በማዋል ፡ ረገድ ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ ዜጐች ፡ መካከል ምንም ዓይነት ፡ ልዩነት ፡ እንዳይደረግ ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፴፯ና ፡ ፴፰ ፡ እንደሚከለክል ፡ ፍ/ቤቱ ፡ አስረድቷል ።[35] አዲሱ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ይህንን ፡ ጉዳይ ፡ ይደግፈዋል ፡ ምክንያቱም ፡ ትእዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፳፯ ፡ "በመላው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ . ተሻሽሎ ፡ የወጣው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ብቻ ፡ ነው" ይላል ።[36] ይህ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ በሕግ ፡ በኩል ፡ እኩል ፡

34. "ለምሳሌ ፡ እንደ ፡ አሜሪካ ፡ ባሉት ፡ በአንዳንድ ፡ የሕግ ፡ ሥርዓቶች ፡ ፍ/ቤቱ ፡ ስለ ፡ ጉዳዩ ፡ በሰጠው ፡ ውሳኔና ፡ በሀሳብ ፡ ውስጥ ፡ ባሉት ፡ ሁሉ ፡ በሌሎች ፡ መካከል ያለውን ፡ መለየት ፡ የተለመደ ፡ ነገር ፡ ነው ። በሀሣብ ፡ ውስጥ ፡ ባሉ ፡ በሌሎች ፡ ሁሉ ፡ የተባለው ፡ ፍ/ቤቱ ፡ ካሳለፈው ፡ ውሳኔ ፡ ጋር ፡ ያልተያያዘ ፡ (ዲክተም) በመባል ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ይህም ፡ በተመሳሳይ ፡ ክስ ፡ ላይ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ የተሰጠ ፡ ውሳኔን ፡ በመከተል ፡ የሕግ ፡ ሥርዓት ፡ ላላቸው ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ <u>በነባሀታ</u> ፡ የፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ እንደዚህ ፡ ልዩነት ፡ ማየት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ።"

35. አንቀጽ ፡ ፴፯ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ "ማንም ፡ ሰው ፡ በሕግ ፡ እኩል ፡ ሆኖ ፡ ይጠበቃል ።" እንዲሁም ፡ አንቀጽ ፡ ፴፰ ፡ "በብሔራዊ ፡ (ሲቪል) መብቶች ፡ ረገድ ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ አይደረግም ፡" ይላል ።

36. "ትእዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፳፯ ፡ ክፍል ፡ ፫ ።"

ሆኖ ፡ መጠበቅን ፡ መነፈግ ፡ እንደሌለበት ፡ ያረጋግጣል ። በፍ/ቤቱ ፡ በቀረበው ፡ ክር ክር ፡ መሠረት ፡ በተለያዩ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ለሚፈ ጸመው ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ወንጀል ፡ (በጦር ፡ መሣሪያ ፡ ውንብድና ፡ )[37] የተለያዩ ፡ ሕጐችን ፡ መጠቀም ፡ በሕግ ፡ እኩል ፡ ሆኖ ፡ መጠበቅን ፡ እንደመንፈግ ፡ ይቆጠራል። የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በሌሎች ፡ የመንግሥቱ ፡ ግዛቶች ፡ ተፈፃሚ ፡ ሲሆን ፡ በኤርትራ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ግን ፡ ስለሽፍቶች ፡ የወጣውን ፡ ሕግ ፡ ፍ/ቤቱ ፡ በዚህ ፡ ክስ ፡ ላይ ፡ እንዲጠቀምበት ፡ ተጠይቋል ። ለአንድ ፡ ዓይነት ፡ ወንጀል ፡ ሁለት ፡ የተ ለያዩ ፡ ሕጐችን ፡ መጠቀም ፡ በሕግ ፡ እኩል ፡ ሆኖ ፡ መጠበቅን ፡ እንደመንፈግ ፡ ስለ ሚቆጠር ፡ በአንዱ ፡ ብቻ ፡ መገልገል ፡ ያስፈልጋል ። ይህን ፡ ሁሉ ፡ ካደረገ ፡ በኋላ ፡ ለምን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ መዋልና ፡ ስለሽፍቶች ፡ የወጣ ውም ፡ ሕግ ፡ መሠረዝ ፡ ስላለበት ፤[38] ስለሽፍቶች ፡ የወጣውን ፡ ሕግ ፡ መጠቀም ፡ ሕገ ፡ መን ግሥታዊ ፡ አለመሆኑን ፡ ፍ/ቤቱ ፡ ማሳየት ፡ ጀመረ ። በልምድ ፡ በኩል ፡ ስንመለከተው ፡ ስለ ሽፍቶች ፡ የወጣውን ፡ ሕግ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ማዋል ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ አይደለም ፡ ማለት ፡ ሕጉ ፡ ራሱ ፡ በእርግጥ ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ አይደለም ፡ እንደማለት ፡ ይቆ ጠራል ።[39] ስለሽፍቶች ፡ የወጣውን ፡ ሕግ ፡ በእርግጥ ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ አይደ ለም ፡ ለማለት ፡ ፍ/ቤቱ ፡ ወደተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፻፳፪ ፡ ሄዶ ፡ መመልከት ፡ አለበት ።[40] ይህ ፡ ፍ/ቤት ፡ ይህንን ፡ ማድረግ ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ አልታየውም ። ስለሽፍቶች ፡ በወጣው ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ ጥልቅ ፡ ምርምር ፡ ማድረግ ፡ አስ ፈላጊ ፡ ስለአልነበር ፡ ፍ/ቤቱ ፡ ችግሩን ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ መመልከቱ ፡ ጊዜና ፡ ድካ ምን ፡ ሊቆጥብለት ፡ ችሏል ። በእርግጥ ፡ በክፍል ፡ ፪ ፡ ፫ና ፡ ፬ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ጠባብ ፡ የሕገ ፡ መንግሥት ፡ ጭብጥ ፡ በተለይ ፡ በዚህ ፡ በቀረበው ፡ ክስ ፡ ላይ ፡ ወደዋናው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ መግባቱ ፡ ምናልባት ፡ አስፈላጊ ፡ አልነበረም ።

<u>የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ነክ ፡ የሆኑ ፡ ክርክሮች፡</u>— በፍ/ቤቱ ፡ ስለሽፍቶች ፡ የወጣ፡ ሕግን ፡ ለማስወገድ ፡ የቀረቡት ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ነክ ፡ የሆኑትና ፡ በሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ የቀረቡት ፡ ክርክሮች ፡ ከወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ የመነጩ ፡ ናቸው ። ፍ/ ቤቱ ፡ የወንጀለኛ ፡ ሥርዓት ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ እንደተገለጸው ፡ "ከፍተኛ ርኅራኄ ፡ የተመላበትና ፡ ቀላል ፡ መሆኑን ፡" አመልክቷል ። ይህ ፡ ሕግ ፡ ለፍ/ቤት ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ ፍርድ ፡ የመስጠትን ፡ ስልጣን ፡ እንደሚፈቅድለት ፡ ተረድቶታል ። በተ ቃራኒ ፡ ስለሽፍቶች ፡ የወጣው ፡ ሕግ ፡ ለፍ/ቤቱ ፡ ቅጣት ፡ የመወሰን ፡ ስልጣን ፡ የማ ይሰጥ ፡ አስገዳጅ ፡ ሕግና ፡ በተለይ ፡ <u>ለዚህ ፡ ወንጀል ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ቅጣት ፡ ይገባ ዋል ፡</u>[41] የሚል ፡ ሆኖ ፡ ተገኝቷል ። ፍ/ቤቱ ፡ ይህንን ፡ ተቃውሞ ፡ የሚገባ ፡ ነው ፡

---

37. በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፲፻፴፯ ።

38. እዚህ ፡ ላይ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፳ ፡ (፩) ን ፡ ማብራራት ፡ አስፈላጊ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀ ርም ።

39. (፩) አንዳንድ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ግልፅ ፡ የሆኑ ፡ ወንጀሎችን ፡ ለማጠቃለል ፡ ባለመቻላቸው ፡ ስለሽፍቶች ፡ የወጡት ፡ ሕጐች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ካልሆኑና ፤
(፪) ፍ/ቤቱ ፡ ከሕገ ፡ መንግሥት ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ ሕግ ፡ በመውጣቱ ፡ ማንንም ፡ ሰው ፡ ካልነቀፈ ፡ በስ ተቀር ።

40. አንቀጽ ፡ ፻፳፪ ፡ "ይህ ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ . በአንድነት ፡ ሆኖ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት የበላይ ፡ ሕግ ፡ ይሆናል ። ወደፊትም ፡ የሚሰሩ ፡ ሕጎች ፡ ድንጋጌዎች ፡ ፍርዶች ፡ ውሳኔ ዎች ፡ ሁሉ ፡ ከዚህ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ጋር ፡ የማይስማሙ ፡ ሲሆኑ ፡ ዋጋ ፡ የሌላቸውና ፡ የማያገለግሉ ፡ ይሆናሉ ፡" ይላል ።

41. ስለሽፍቶች ፡ የወጣው ፡ የመጀመሪያው ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፲፫ ፡ "ከወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፶፮ (፪) ፡ ፫፻፱ ፡ እስከ ፡ ፬፻፫ና ፡ ከቁጥር ፡ ፯፻፵፰ ፡ እስከ ፡ ፯፻፲፮ ፡ በስተቀር ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ጠቅላላ ፡ ክፍልን ፡ ይከተላል ፡" ይላል ።

ሲል ፡ ከወሰነ ፡ በኋላ ፡ "እርሱ ፡ [ስለሽፍቶች ፡ የወጣው ፡ ሕግ] ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ መሠረት ፡ ከወጡ ፡ ዘመናውያን ፡ ሕጐቻችን ፡ ጋር ፡ የሚስማማ ፡ አይደለም ፡" በማለት ፡ ሀሳቡን ፡ አጠቃሏል ። አንድ ፡ ሰው ፡ ይህንን ፡ አባባል ፡ እጥቅም ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ ቢፈቀድለት ፡ ይህ ፡ ዓይነቱ ፡ ምክንያት ፡ አደራደር ፡ "በተዘዋዋሪ ፡ መንገድ ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ አይደለም ፡" እንደማለት ፡ ያለ ፡ ነው ። ምርምሩም ፡ እንደሚከተለው ፡ ይሆናል ፤ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕጉ ፡ ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ይስማማል ፤ ስለሽፍቶች ፡ የወጣው ፡ ሕግ ፡ ከወንጀለኛ ፡ መቅጫው ፡ ሕግ ፡ ጋር ፡ አይስማማም ፤ ስለዚህ ፡ ስለሽፍቶች ፡ የወጣው ፡ ሕግ ፡ ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ጋር ፡ አይስማማም ። ተመራማሪዎች ፡ ስህተቱ ፡ ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ ያገኙታል ። ሕጋዊ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ ስናየው ፡ ፍ/ቤቱ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫውን ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌሎች ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕጐች ፡ በላይ ፡ አድርጐ ፡ ያያቸው ፡ ይመስላል ። የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ "ለወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ጠቅላላ ፡ ሕግ ፡ ማሟያ ፡ የሚሆኑት ልዩ ፡ ሕጐች ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው ፡" ይላል ።[42] ይህን ፡ ክርክር ፡ በሚመለከት ፡ ነገር ፡ ስለሽፍቶች ፡ የወጣው ፡ ሕግ ፡ ወንጀል ፡ ነክ ፡ የሆነ ፡ ልዩ ፡ ሕግ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ አይቆጠርም ፡ ወይ?

ስለ ፡ ሽፍቶች ፡ የወጣውን ፡ ሕግ ፡ ያወጡት ፡ ሕግ ፡ አዋቂዎች ፡ በዚህ ፡ ክፍል ፡ ሊገኙ ፡ ስለሚችሉት ፡ ችግሮች ፡ ያውቁ ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ የ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ. ም. ማሻሻያ፡ "የወንጀለኛው ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ አንዳንድ ፡ ነገር ፡ ልዩ ፡ ችግሮችን ፡ ለማስወገድ ፡ ተስማሚ ፡ ባለመሆኑ ፡ ስለሽፍቶች ፡ የወጣውን ፡ ሕግ ፡" እንዲታወጅ ፡ አስፈልጐ ፡ በጠቅላላው ፡ ክፍል ፡ የሚገኙትን ፡ አንቀጾች ፡ በተለይ ፡ ለመተው ፡ ስለሽፍቶች ፡ የወጣውን ፡ ሕግ ፡ ክፍል ፡ ፲፫ ፡ ተክቶታል ።[43] የማሻሻያው ፡ አንዱ ፡ ዓላማው ፡ ስለሽፍቶች ፡ በወጣው ፡ ሕግና ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ግንኙነት ፡ ለማሳየት ፡ ሲሆን ፡ ፍ/ቤቱ ፡ በአንዳንድ ፡ ባልታወቁ ፡ ምክንያቶች ፡ ማሻሻያውን ፡ ምንም ፡ ሳይጠቅሰው ፡ አልፏል ።

ስለሽፍቶች ፡ የወጣው ፡ ሕግ ፡ ስለቅጣት ፡ ያለውን ፡ የአስገዳጅነት ፡ ጠባይ ፡ ከተመለከትን ፡ ዘንድ ፡ የዚህ ፡ ሕግ ፡ ክፍል ፡ ፪ ፡ ፫ ና ፡ ፬ ፡ በተከታታይ ፡ ከአምስት ፡ ከአሥርና ፡ ከአሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ "በማያንስ" እስራት ፡ የሚል ፡ ዓይነት ፡ ቅጣት ፡ አለበት ። እነዚህ ፡ ክፍሎች ፡ አነስተኛውን ፡ ቅጣት ፡ ቢወስኑም ፡ ለፍ/ቤቱ ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ ከታየው ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ቅጣት ፡ እንዲበይን ፡ ስልጣን ፡ ይሰጡታል ። ለምሳሌ ፡ ፍ/ቤቱ ፡ ከባድ ፡ ያልሆኑ ፡ ጥፋቶች ፡ በክፍል ፡ ፪ ፡ መሠረት ፡ ከአምስት ፡ እስከ ፡ አሥር ፡ ዓመት ፡ እስራት ፡ ሊፈርድበት ፡ ይችላል ። በተለይ ፡ በዚህ ፡ ክፍል ፡ ፍ/ቤቱ ፡ "ቅጣቱን ፡ የሚያቀልበት ፡ በጣም ፡ ልዩ ፡ የሆኑ ፡ ምክንያት ፡ ካገኘ" በእርግጥ ፡ ከተመደበው ፡ ዝቅተኛ ፡ የአምስት ፡ ዓመት ፡ እስራት ፡ በታች ፡ ለመፍረድ ፡ ሰልጣን ፡ አለው ። እንደዚሁም ፡ ፍ/ቤቱ ፡ በክፍል ፡ ፫ና ፡ ፬ ፡ መሠረት ፡ በተከታታይ ፡ ከ፲―፲፭ ዓመትና ፡ ከ፲፭―፳ ዓመት ፡ የእስራት ፡ ቅጣት ፡ የመፍረድ ፡ ስልጣን ፡ አለው ። በተዘዋዋሪ ፡ መንገድም ፡ ቢሆን ፡ በእያንዳንዱ ፡ ክፍል ፡ የተወሰነው ፡ ዝቅተኛ ፡ ቅጣት ፡ እየጨመረ ፡ ስለሚሄድ ፡ በእያንዳንዱ ፡ ክፍል ፡ የሚወሰነውን ፡ ከፍተኛ ቅጣት ፡ ልናውቀው ፡ እንችላለን ። እርግጥ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተሰጠው ፡ ስልጣን ፡ ከወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ይልቅ ፡ ስለሽፍቶች ፡ በወጣው ፡ ሕግ ፡ ያለው ፡ ያነሰ ፡

42. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፫ ። ጥያቄ ፡—በሕግ ፡ እኩል ፡ ሆኖ ፡ መጠበቅ ፡ የሚለውን ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ አንቀጽ ፡ ለማሟላት ፡ (ለማርካት) እነዚህን ፡ ልዩ ፡ ሕጎች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ግዛቶች ፡ በሙሉ ፡ ተፈጻሚ ፡ እንዲሆኑ ፡ ማድረግ ፡ ይገባል ፡ ወይ?

43. ይህ ፡ ስለሽፍቶች ፡ የወጣው ፡ ሕግ ፡ የ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ. ም. ሁለተኛ ፡ ማሻሻያ ፡ ነው ። በተቀጥላ ፡ ፭ ፡ (መ) በገጽ ፡ ፪፻፺፫ ፡ ተመልከት ።

ነው ።[44] ከዚህም ፡ በላይ ስለሸፍቶች ፡ የወጣው ፡ ሕግ ፡ ከወንጀለኛ ፡ መቅጫው ፡ ሕግ ፡ በመለየት ፡ ፍ/ቤቱን ፡ የታገደ ፡ ውሳኔ ፡ እንዳይሰጥ ፡ ይከለክለዋል ።[45] ምንም ፡ እንኳን ፡ ይህ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫና ፡ ስለሸፍቶች ፡ በወጣው ፡ ሕግ ፡ መካከል ፡ ልዩ ነት ፡ ቢፈጥር ፡ ለፍ/ቤቱ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ከአ ንቀጽ ፡ ፻፺፯ ፡ እስከ ፡ ፻፺፰ ፡ ድረስ ፡ የታገደ ፡ ፍርድን ፡ ለማዘዝ ፡ ስልጣን ፡ ቢፈቅድ ለት ፡ በአሳሳቢ ፡ ወንበዴነት ፡ ወይም ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ የወንበዴነት ፡ ሥራ ፡ ወንጀል ፡ የታገደ ፡ ፍርድን ፡ ለመወሰን ፡ የሚችል ፡ አይመስልም ።[46] በመጨረሻ ፡ በተሻሻ ለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ወይም ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሌሎች ፡ የሕገ ፡ መን ግሥታዊ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ችግሮች ፡ ከሌሉ ፡ በልዩ ፡ ሕጐች ፡ ውስጥ ፡ "አስገዳጅ ፡ ቅጣትን ፡" የሚከለክል ፡ የለም ።[47] ስለዚህ ፡ "አስገዳጅ ፡ ቅጣት ፡" የሚል ፡ ክር ክር ፡ ሕጋዊነት ፡ ስለሸፍቶች ፡ የወጣውን ፡ ሕግ ፡ ከሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከሚስማማው ፡ ከወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ባለመስማማቱ ፡ "በተዘዋዋሪ ፡ መንገድ ፡ ሕገ ፡ መንግ ሥታዊ ፡ አይደለም ፡" የሚባለው ፡ አጠራጣሪ ፡ ይመስላል ።

በእርግጥ ፡ ፍ/ቤቱ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ጠቅላላ ፡ ክፍልን ፡ መጥቀሱ ፡ ተፈላጊ ፡ አይደለም ። አንቀጽ ፡ ስድስትና ፡ ዘጠኝ ፡ በነባሀታ ፡ ፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ከተጠቀሱት ፡ በጠቅላላው ፡ የተለየ ፡ ሁኔታዎች ፡ አላቸው ። አንድ ፡ ትክክለኛ ፡ ጥያቄ ፡ ማቅረብ ፡ ቢያስፈልግ ፡ ፍ/ቤቱ ፡ በእነዚህ ፡ አንቀጾች ፡ የተጠቀሱ ትን ፡ ሁኔታዎች ፡ በመመልከት ፡ የተሻለ ፡ ቅጣት ፡ መጠቀም ፡ የሚለውን ፡ ጽንስ ፡ ሀሳብ ፡ ሊያፈልቅ ፡ ስለመቻሉ ፡ ነው ። ፍ/ቤቱ ፡ ስለሸፍቶች ፡ ከወጣው ፡ ሕግ ፡ ይልቅ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግን ፡ የሚመለከት ፡ መሆኑን ፡ ከወሰነ ፡ ግን ፡ በቀ ጥታ ፡ "ይህ ፡ ሕግ ፡ እንዲጸና ፡" ከመደረጉ ፡ በፊት ፡ ስለተደረጉ ፡ ወንጀሎች ፡ የሚ መለከቱ ፡ አንቀጾችን ፡ ሳይጠቅስ ፡ እንደ ፡ አንቀጽ ፡ ፯፻፴፮ና ፡ ፯፻፴፯ ፡ የመሳሰሉትን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ የተለዩ ፡ አንቀጾችን ፡ ሊጠቀም ፡[48] ወይም ፡ ደግሞ ፡ "አዲሱ ፡ ሕግ ፡ ከመጽናቱ ፡ በፊት ፡ በተሰጡት ፡ ፍርዶች ፡ ላይ ፡ የዚህ ፡ ሕግ ፡ አፈ ጻጸም ፡" ሊከተል ፡ ይችላል ።[49] የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ስለሸፍቶች ፡ በውጣው ፡ ሕግ ፡ ከተተካ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ የማዛመዱ ፡ ሀሳብ ፡ አስፈላጊ ፡ አይደለም ።

አሁንም ፡ ፍ/ቤቱ ፡ ያቀረበው ፡ ሌላው ፡ ክርክር ፡ ተከሳሾች ፡ የትግሬ ፡ ጠ/ግዛት ፡ ነዋሪዎች ፡ ናቸው ፡ በሚለው ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ሲሆን ፡ በቀጥታ ፡

---

44. ስለሸፍቶች ፡ በወጣው ፡ ሕግ ፡ በያንዳንዱ ፡ ክፍል ፡ መጀመሪያ ፡ ለፍ/ቤቱ ፡ የሚሰጠውን ፡ የቅጣት ፡ መወሰን ፡ ስልጣን ፡ እስከ ፡ ፰ ፡ ዓመት ፡ ሲወሰን ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫው ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፯፻፴፯ (፩) ግን ፡ ይህን ፡ ሥልጣን ፡ እስከ ፡ ፲፰ ፡ ዓመት ፡ በሚደርስ ፡ ያደርገዋል ። ስለሸፍቶች ፡ ተሻሽሎ ፡ የወጣው ፡ ሕግ ፡ ክፍል ፡ ፲፫ ፡ ፍ/ቤቱ ፡ ከአነስተኛው ፡ ቅጣት ፡ ሲሶ ፡ እንዲቀንስ ፡ ይፈቅድለታል ። ጥያቄ ፡— ከሞት ፡ ቅጣት ፡ ሲሶው ፡ ምንድን ፡ ነው?

45. ስለሸፍቶች ፡ የወጣው ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፫ ፡ እንደተሻሻለ ፤ አሁንም ፡ ከተሻሻለ ፡ በኋላ ፡ "በዚህ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የተሰጠው ፡ ማናቸውም ፡ ፍርድ ፡ በገደብ ፡ አይታገድም ፡" ይላል ። ተቀጥላ ፩(ሀ) ተመልከት ።

46. በቁጥር ፡ ፻፺፯ ፡ ያለው ፡ ቅጣት ፡ እንዳይፈጸም ፡ ጊዜ ፡ ስለመስጠትና ፡ ለቅጣት ፡ ውሳኔ ፡ ጊዜ ፡ ስለመስ ጠት ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ እንዳለ ፡ መገንዘብ ፡ ያስፈልጋል ። ሁለተኛው ፡ በአንቀጽ ፡ ፻፺፰ ፡ ሥር ፡ ያለ ፡ ሲሆን ፡ በመሣሪያ ፡ ወንበዴነትን ፡ የመሰለ አሳሳቢ ፡ ጉዳይ ፡ ሲያጋጥም ፡ ይህ ፡ ዓይነቱ ፡ ስልጣን ፡ ለፍ/ቤቱ ፡ ሊሰጥ ፡ አይችልም ።

47. ተሻሽሎ ፡ ስለሸፍቶች ፡ በወጣው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ቅጣቶቹን ፡ ከተወሰነው ፡ አነስተኛ ፡ ቅጣት ፡ እስከ ፡ ሲሶ ፡ መቀነስ መቻሉ ፡ "አስገዳጅ ፡ ቅጣት ፡" የሚለው ፡ ክርክርን ፡ ያዳክመዋል ።

48. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፯ ።

49. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፱

ስህተት ፡ ካልሆነ ፡ ተፈላጊ ፡ አለመሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ነው ። ፍ/ቤቱ ፡ ተከሳሾቹ ፡ ይህን ፡ ስለሽፍቶች ፡ የወጣውን ፡ ሕግ ፡ አያውቁም ፡ ነበር ፡ ከማለቱም ፡ ሌላ ፡ "እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ምናልባት ፡ የተያዙ ፡ እንደሆነ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ እንደሚቀጡ ፡ ያስቡ ፡ እንደነበሩ ፡ ጥርጥር ፡ የለውም ።" ይህንንም ፡ ክርክር ፡ ከተቀበልን ፡ ዘንዳ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የሚውለው ፡ ስለሽፍቶች ፡ የወጣ ፡ ሕግ ፡ ሳይሆን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ነው ። ይህ ፡ ክርክር ፡ ለጉዳዩ ፡ የኢንተርናሽናል ፡ ሕግ ፡ ጮራ ይሰጠዋል ። ቢሆንም ፡ ምናልባት ፡ ተከሳሾቹ ፡ የተያዙ ፡ እንደሆነ ፡ ይህ ፡ የተለየ ፡ ሕግ ፡ የሚፈጸምባቸው ፡ መሆኑን ፡ የሚያውቁ ፡ መሆናቸውንና ፡ (እንደዚህ ፡ መሆኑ ፡ ቢገመትም) የመኖሪያ ፡ ቦታውን ፡ መጥቀስ ፡ አስፈላጊ ፡ አይደለም ። በኢንተርናሽናል ፡ ሕግ ፡ እንኳን ፡ ወንጀሉ ፡ በተፈጸመበት ፡ ቦታ ፡ ሕግ ፡ እንጂ ፡ የተከሳሾቹ ፡ መኖሪያ ፡ ቦታ ፡ ሕግ ፡ ተፈፃሚ ፡ አይሆንም ፤ ይህም ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕጋችን ፡ በደንብ ፡ ተገልጿል ።[50] ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንደ ፡ ተባለው ፡ ይህ ፡ ክርክር ፡ አስፈላጊ ፡ አይደለም ።

ነገር ፡ ግን ፡ ፍ/ቤቱ ፡ በጥሩ ፡ መንፈስ ፡ ተነሳስቶ ፡ ስለሽፍቶች ፡ የወጣውን ፡ ሕግ ፡ ውድቅ ፡ ለማድረግና ፡ ተፈጻሚ ፡ እንዳይሆን ፡ ያገናኛቸውን ፡ ክርክሮች ፡ ማቅረቡ ፡ ሊገባ ፡ የሚችል ፡ ነው ። እንዲያውም ፡ ፍ/ቤቱ ፡ በሀሳቡ ፡ የሕጉ ፡ የመጀመሪያ ፡ ክፍሎች ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ሌሎች ፡ ችግሮችን ፡ የሚገልጹ ፡ ክፍሎች ፡ ሳይታዩት ፡ አይቀሩም ።[51] ፍ/ቤቱ ፡ እነዚህ ፡ "የአገሬው /የመንደረተኞቹ/ ፡ የጋራ ፡ ኃላፊነት" እና ፡ "የቦታ ፡ ኃላፊነት ፡" የሚሉትን ፡ ክፍሎች ፡ በክሱ ፡ ሳያነሳና ፡ ሳያብራራቸው ፡ አልፏል ።[52] እኛ ፡ ግን ፡ በመጀመሪያ ፡ ስለ ፡ ሽፍቶች ፡ የወጣው ፡ ሕግ ፡ የቀዳሚ ፡ ክፍሎች ፡ ከወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ጋር ፡ ያላቸውንም ፡ ግንኙነት ፡ እንመረምራለን ።

## ፩. <u>የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ስለሽፍቶች ፡ ከወጣው ፡ ሕግ ፡ ጋር ፡ ሲነፃፀር ።</u>[53]

ስለሽፍቶች ፡ በወጣው ፡ ሕግ ፡ በመጀመሪያ ፡ ክፍሎች ፡ ያለው ፡ ስህተት ፡ ምንድነው ? በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ካሉትስ ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንዴት ፡ ይለያል ? የሚል ፡ ጥያቄ ፡ ይቀርብ ፡ ይሆናል ። በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ባሉት ፡ ድንጋጌዎችና ፡ ስለሽፍቶች ፡ በወጣው ፡ ሕግ ፡ የመጀመሪያ ፡ ክፍሎች ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ መሠረታዊ ፡ ልዩነት ፡ ጥሩትን ፡ ለማግኘት ፡ በሚያስፈልገው ፡ የማስረጃ ፡ ደረጃ ፡ ነው ። ስለሽፍቶች ፡ የወጣው ፡ ሕግ ፡ የእያንዳንዱን ፡ ተከሳሽ ፡ ጉዳይ ፡ በተለይ ፡ ለማየት ፡ የሚያገለግለውንና ፡ በከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ ሁሉንም ፡ የሥነ ፡ ሥር

---

50. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፲፩ (፩)

51. ስለሽፍቶች ፡ የወጣ ፡ ሕግ ፡ ክፍል ፡ ፲

52. " " " " ፲፩

53. በዚህ ፡ የምርምር ፡ ጽሑፍ ፡ ክፍል ፡ ስለሽፍቶች ፡ በወጣው ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የመጀመሪያ ፡ ክፍሎች ፡ (ከአንድ ፡ እስከ አምስት) ብቻ ፡ ከወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌ ጋር ፡ ይነፃፀራሉ ። ያገሬው ፡ (የመንደረተኞች) ፡ የጋራ ፡ ኃላፊነትና ፡ የቦታ ፡ ሃላፊነት ፡ ክፍሎች ፡ ከጋራ ፡ (አባሪ ፡) ኃላፊነት ፡ (ኮሌክቲቭ ፡ ሊያቢሊቲ አክት) ተጣምረው ፡ በምርምሩ ፡ ጽሑፍ ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ እንመረምራቸዋለን ። ቢሆንም ፡ ይህ ፡ ክፍል ፡ ስለሽፍቶች ፡ ከወጣው ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ መጀመሪያ ፡ ክፍሎች ፡ ሌላ ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፴፯ (ሀ)ንና ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፫ ፡ ከተጠቀሰው ፡ <u>የነውሬታ</u> ፡ ፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ ይህንኑ ፡ አጣምሮ ፡ ይመለከታል ።

ዓትም ፡ ሆነ ፡ ዋና ፡ መብቶቹን ፡ የሚያስከብርለትን ፡ ዘመናዊውን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ሕግ ፡ ጥራትና ፡ ብዛት ፡ ያሰወገደ ፡ ይመስላል ።[54]

ወንጀለኛው ፡ ጥፋተኛ ፡ ሆኖ ፡ ከተገኘ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በተለመደው ፡ የወንጀ ለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ አስፈላጊውን ፡ ቅጣት ፡ እንደገና፡ በጥንቃቄ ፡ ይመለ ከትለታል ።[55] ስለሽፍቶች ፡ የወጣው ፡ ሕግ ፡ ከወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ለየት ፡ በማለት ፡ በአንዳንድ ፡ ነገሮች ፡ አጭር ፡ የፍርድ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ይዞ ፡ ይገኛል ። ከሁለት ፡ ወይም ፡ ከዚህ ፡ ከበለጡ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ቢያንስ ፡ አንዱ ፡ ጠብመንጃ ፣ ወይም ፡ ሌላ ፡ ፈንጂ ፡ መሣሪያ ፡ ኖሮት ፡ ሌላው ፡ ጓዳቸው ፡ ከጠቅላላው ፡ ሰዎች ፡ ሐሳብ ፡ (ዕቅድ) ውጭ ፡ ወንጀል ፡ ቢፈጽም ፡ ለከፍተኛው ፡ ወንጀል ፡ ሁሉም ፡ ሰዎች፡ ልዩነት ፡ ሳይደረግ ፡ ሓላፊዎች ፡ ይሆናሉ ።[56] ለምሳሌ ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ጥቂት ከብቶች ፡ ለመዝረፍ፡ ሲያድሙ ፡ ጥይት ፡ እንዳይተኮስ ፡ ወይም፡ ሌላ ፡ ፈንጅ ፡ ነገር ፡ እንዳይፈነዳ ፡ ሁሉም ፡ በግልጽ ፡ እርስ ፡ በራሳቸው ፡ ተስማሙ ፡ እንበል ። ወንጀሉን ፡ በሚፈጽሙበት ፡ ጊዜ ፡ ከመካከላቸው ፡ አንዱ ፡ ከስምምነታቸው ፡ ውጭ ፡ አፈንግጦ ፡ ቢተኩስ ፡ ወይም ፡ ፈንጂ ፡ መሣሪያ ፡ ቢያፈነዳ ፡ (የተዘረፈው ፡ ሰው ፡ ባይጐዳም ፡ ወይም ፡ ለመጉዳት ፡ ሙከራ ፡ ባይደረግበትም ፡ ቅሉ ፡) ሁሉም ፡ ሰዎች ፡ ለተኩሱ ፡ ኃላፊ ፡ ይሆናሉ ። ለመጀመሪያ ፡ ሐሳባቸው ፡ (ዕቅዳቸው) የሚፈረድባቸው ፡ ቅጣት ፡ ከአሥር ፡ ዓመታት ፡ ያላነሰ ፡ እስራት ፡ ሲሆን ፣[57] ያሁኑ ፡ ቅጣት ፡ ግን ፡ በሁሉም ፡ ላይ ፡ የማይቀር ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ነው ።[58] ከሁለት ፡ ወይም ፡ ከዚህ ፡ ከበለጡ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ አንደኛው ፡ ጠብመንጃ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ፈንጅ ፡ መሣሪያ ፡ ኖሮት ፡ በማንጸ ጸር ፡ ጥፋቱ ፡አነስተኛ ፡ ቢሆንም ፡ ቅሉ ፡ በተለየየ ፡ ጊዜ ፡ አሥር ፡ ብር ፡ በኃይል ፡ እን ደመውሰድ ፡ ባሉት ፡ በማናቸውም ፡ ሦስት ፡ ወንጀሎች ፡ ጥፋተኞች ፡ ሆነው ፡ ከተገኙ፡ የሚበየንባቸው ፡ እንደገና ፡ የማይቀር ፡ የሞት ፡ ቅጣት ፡ ነው ።[59] በያንዳንዱ ፡ ክፍል ፡ የተመደበው ፡ የሞትም ፡ ሆነ ፡ ዝቅተኛ ፡ ቅጣት ፡ በምንም ፡ ዓይነት ፡ የማይቀር ፡ በመ ሆኑ ፡ ሲያስፈልግ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ እንደሚደረገው ፡ ሁሉ ፡ ፍ/ቤት ፡ የቅጣት ፡ ማቃለያ ፡ ሁኔታዎችን ፡ የሚሰማበት ፡ መንገድ ፡ ሊኖረው ፡ አይ ችልም ።[60]

ከዚህ ፡ ከማይቀር ፡ ቅጣት ፡ ብቻውን ፡ ለየት ፡ ብሎ ፡ የምናገኘው፡ ክፍል ፡ ሁለት ፡ "ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ቅጣቱን ፡ የሚያቃልልበት ፡ በጣም ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ ምክንያት ፡" ካገኘ፡ ከአምስት ፡ ዓመት ፡ ላነሱ ፡ ጊዜ ፡ እንዲታሰር ፡ የሚያደርግበትን ፡ መንገድ ፡ ይፈቅ ድለታል ። በዚህ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ "ከሁለት ፡ ወይም ፡ ከዚህ ፡ የበለጡ፡ ሰዎች ፡ የጋራ ፡

54. በወንጀል ፡ ክስ ፡ ጊዜ ፡ መሠረታዊያን ፡ የመብቶች ፡ ዋስትናዎች ፡ ተሻሽሎ ፡ በወጣው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት፣ በሦስተኛ ፡ ምዕራፍ ፡ ተዘርዝረዋል። በአንቀጽ፡ ፴፯ ፡ ያለው ፡ የሕግ ፡ እኩልነት ፡ በአንቀጽ ፡ ፵፫ ፡ ውስጥ፣ ያለው ፡ በሕግ ፡ መሠረት ፡ እንደዚሁም ፡ በሰፊው ፡ ከአንቀጽ ፡ ፶፩ ፡ እስከ ፡ ፶፯ ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ ዋናዎቹ፣ የመብት ፡ ዋስትናዎች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በወንጀል ፡ ለተከሰሰ ፡ ሰው ፡ የተሰጡ ፡ ናቸው ።

55. ስለሽፍቶች ፡ የወጣው ፡ ሕግ ፡ (ከነማሻሻያዎቹ) ፡ ከወንጀለኛ ፡ መቅጫው ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የጠቅላላ ውን ፡ ክፍል ፡ ቁጥሮች ፡ እንደ ፡ ቁ. ፫፻፲—፫፻፲፫ ፡ ማለት ፡ ቅጣትን ፡ ስለማቃልያና ፡ ማክበጃ ፡ ምክንያ ቶች ፡ የመሳሰሉትን ፡ ፍ/ቤት ፡ በሚበይንበት ፡ ጊዜ ፡ ሊመለከታቸው ፡ የሚገባውን ፡ በግልጽ ፡ ለይቶ ታል ።

56. ይህ ፡ ከክፍል ፡ ፪ ፡ በቀጥታ ፡ ይሆናል ፡ ተብሎ ፡ የተወሰደ ፡ ነው ።

57. በሕጉ ፡ ክፍል ፡ ፫ ፡ መሠረት ፣

58. በሕጉ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፫ ፡ መሠረት ፣

59. የሕጉ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።

60. ከዚህ ፡ የተለየው ፡ ሕግ ፡ በተሻሻለው ፡ ክፍል ፡ ፲፫ ፡(፩)፡ መሠረት ፡ በዚሁ ፡ ሕግ ፡ የሚወሰነው ፡ ማና ቸውም ፡ አነስተኛ ፡ ቅጣት ፡ እስከ ፡ ሲሦ ፡ ዝቅ ፡ ሊል ፡ ይችላል ። እንደገና ፡ ለመመራመር ፡ እንዴት ፡ የሞት ፡ ቅጣት ፡ ሲሦ ፡ ሊተመን ፡ ይችላል?

ዓላማቸው ፡ ማናቸውንም ፡ የኃይል ፡ ወንጀል ፡ ሥራ ፡ ለመፈጸም ፡ ከሆነና ፡ ቢያንስ ፡ ቢያንስም ፡ አንዳቸው ፡ ጠብመንጃ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ፈንጅ ፡ መሣሪያ ፡ ከያዘ ፡” ወንጀል ፡ ነው ፡ ሲል ፡ ተርጉሞታል ። ይህ ፡ ስለሽፍቶች ፡ የወጣው ፡ ሕግ ፡ ጠቅላላ ፡ መግቢያ ፡ ክፍል ፡ በመሠረቱ ፡ የመከላከያ ፡ ጠባይ ፡ አለው ፤ ምክንያቱም ፡ የሚያስፈልጉት ፡ ዝርዝር ፡ ነገሮች ፡ ፩ኛ. ሁለት ፡ ወይም ፡ ከዚህ ፡ የበለጡ ፡ ሰዎች ፡ መኖር ፣ ፪ኛ. ከመካከላቸው ፡ አንደኛው ፡ ጠብመንጃ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ፈንጅ ፡መሣሪያ ፡ ያለውና ፡ ፫ኛ. የጋራ ፡ ዓላማቸው ፡ ማናቸውንም ፡ የኃይል ፡ ወንጀል ፡ ሥራ ፡ ለመፈጸም ፡ ስለ ሆነ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ላይ ፡ መጠቀስ ፡ ያለበት ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ በሦስተኛው ፡ ዝርዝር ፡ ነገር ፡ ዓላማን ፡ ለማርገጥ ፡ በጣም ፡ አስቸጋሪ ፡ የሆነው ፡ ስለሽፍቶች ፡ በወጣው ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ ቀላል ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ።[61] ከሁለት ፡ ወይም ፡ ከዚህ ፡ ከበለጡ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ አንደኛው ፡ ጠብመንጃ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ፈንጅ ፡ መሣሪያ ፡ ይዞ ፣ ሁሉም ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ ቢገኙ ፣ ቢያንስም ፡ ቢበዛም ፡ የጋራ ፡ ዓላማቸው ፡ የኃይል ፡ ወንጀል ፡ ሥራን ፡ ለመፈጸም ፡ ነው ፡ ተብለው ፡ ይገመታሉ ። ስለ ዚህ ፡ ዐውቀው ፡ ከማጥፋት ፡ ንጹህ ፡ (ጥፋት ፡ የሌለባቸው) ለመሆናቸው ፡ አስቸጋሪው ፡ ማስረጃ ፡ የማቅረብ ፡ ግዴታ ፡ ወደነሱ ፡ ይተላለፋል ፡ ማለት ፡ ነው ።[62]

ስለሽፍቶች ፡ ከወጣው ፡ ሕግ ፡ መጀመሪያ ፡ ክፍል ፡ ተዘርዝረው ፡ የሚገኙት ፡ ወንጀሎች ፡ ሁሉ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግም ፡ የሚያስቀጡ ፡ ሆነው ፡ ይገኛሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ የክሱ ፡ መሰማት ፡ አጀማመር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በተለይም ፡ ማስረጃ ፡ የማቅረብ ፡ ግዴታና ፡ ጥፋትን ፡ ለማግኘት ፡ የሚያስፈልገው ፡ ማረጋገጫ ፡ በጣም ፡ ትክክል ፡ መሆን ፡ አለባቸው ።[63] ከዚህም ፡ በላይ ፡ የሚወሰነው ፡ ቅጣት ፡ ለያንዳንዱ ፡ ተከሳሽ ፡ እንደሚስማማው ፡ ሆኖ ፡ በጠቅላላው ፡ በከፍተኛ ፡ ጥንቃቄ ፡ መታየት ፡ አለበት ። ፍርድ ፡ ቤት ፡ በያንዳንዱ ፡ ክስ ፡ ላይ ፡ ቅጣትን ፡ የማክበድና ፡ የማቅለል ፡ ሁኔታዎችን ፡ የማየት ፡ ሥልጣን ፡ ሊኖረው ፡ ይገባል ።

የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ “አደገኛ ፡ የሆነ ፡ ሥራ ፡ ፈትነት” እና ፡ “የክፉ ፡ አድራጊዎች ፡ ማህበርተኝነት ፡” የሚለው ፡ ስለሽፍቶች ፡ የወጣውን ፡ ሕግ ፡ ክፍል ፡ ሁለትን ፡ ይጠብቀዋል ።[64] በነዚህ ፡ ቁጥሮች ፡ መሠረት ፡ ሊወሰን ፡ የሚገባው ፡ ከፍተኛው ፡ ቅጣት ፡ የሦስት ፡ ዓመቶች ፡ እስራት ፡ ነው ። ጥቂት ፡ ሰዎች ፡ ወንጀል ፡ ቢፈጽሙና ፡ ቅጣትን ፡ በሚያከብዱት ፡ ስለሽፍቶች ፡ በወጣው ፡ ሕግ ፡ ክፍሎች ፡ ፫ ፣ ፬ ፡ ወይም ፡ ፭ ፡ የሚያስከስሳቸው ፡ ቢሆን ፣ እያንዳንዳቸው ፡ በፈጸሙት ፡ የወንጀል ፡ ዓይነት ፡ መሠረት ፡ በግልጽ ፡ በተጠቀሱት ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ ሊከሰሱ ፡ ይችላል ። እንደ ፡ “ከባድ ፡ (የግፍ) አገዳደል” እና ፡ “ከባድ ፡ የሆነ ፡ የወንበዴነት ፡ ሥራ ፡” ያሉት ፡ ወንጀሎች ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ሊያስከትሉ ፡

61. ዐውቆ ፡ ስለማጥፋት ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፶፰ ፡ ተተርጉሟል ። ዐውቆ ፡ ማጥፋትን ፡ ቀጥታና ፡ ቀጥታ ፡ ያልሆነ ፡ ብሎ ፡ በሁለት ፡ ከፍሎታል ። ሮናልድ ፡ ስክላር ፡ “. . . ማወቅ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ወንጀለኛ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡” ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ቮልዩም ፫ ፡ ቁጥር ፡ ፪ ፡ (፲፱፻፷፫)

62. ስለሽፍቶች ፡ የወጣው ፡ ሕግ ፡ ተከሣሾቹን ፡ ሁሉ ፡ አንድነት ፡ ለመክሰስ ፡ ታስቦ ፡ ስለሆነ ፣ ጥፋተኛ ፡ አይደለሁም ፣ ከፍርሃት ፡ የተነሳ ፡ ተገድጄ ፡ ነው ፡ ሰዎቹን የተከተልኩት ፡ ወይም ፡ ሰዎቹ ፡ ሲያዙ ፡ እንደአጋጣሚ ፡ ሆኖ እዚያ ፡ ስለነበርኩ ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ የነሱ ፡ አባል ፡ አይደለሁም ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ ጥፋተኛ ፡ ያለመሆኑን ፡ ለማረጋገጥ ፡ ማስረጃ ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ።

63. ኢትዮጵያ ፡ የማስረጃ ፡ ሕግ ፡ የላትም ። ቢሆንም ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ የሚገኘውና ፡ ከውጭ ፡ የመጣው ፡ ሐሳብ ፡ “እንደጥፋተኛ ፡ ሆኖ ፡ አይቆጠርም ፡” የሚለው ፡ አባባልና ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ሰፋ ፡ ያለው ፡ የወንጀል ፡ ክስ ፡ መስማት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ እንደሚያመለክትው ፡ ትክክለኛ ፡ የሆነ ፡ ማስረጃ ፡ ለማስፈለጉ ፡ ጥርጥር ፡ የለውም ።

64. የወ. መ. ሕ. ቁ. ፭፻፳፩ና ፡ ፭፻፳፪ ፡

ይችላሉ ።[65] ከዚህም ፡ በላይ ፡ በጠቅላላ ፡ ክፍል ፡ "ስለመሞከር ፡" ፡ "ስለዋና ፡ ወንጀል ፡ አድራጊውና ፡ ስለግብረ፡አበሮቹ ፡" ፡ "ስለአባሪነት" እና ፡ "በወንጀል ፡ ሥራ ፡ ስለመስማማትና ፡ ስለማደም" የተሰኙትን ፡ ቁጥሮች ፡ ሲያስፈልጉ ፡ መጥቀስ ፡ ይቻላል ።[66]

<u>ቁጥር ፡ ፬፻፴፯ ሀ</u>[67] በክፍል ፡ ሁለት ፡ እንደተተረጐመው ፡ ስለሽፍቶች ፡ የወጣው ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ "ሁለት ፡ ወይም ፡ ከዚህ ፡ የበለጡ፡ ሰዎች ፡" መግለጹ ፡ ይታወሳል ። እንግዲህ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ያለሕግ ፡ ጠብመንጃ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ፈንጅ ፡ መሣሪያ ፡ ይዞ ፡ ቢገኝ ፡ ጥፋቱ ፡ በተለመደው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ይታያል ፡ ተብሎ ፡ ይታሰብ ፡ ይሆናል ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ አይደለም ። ስለሽፍቶች ፡ የወጣውን ፡ ሕግ ፡ ማሟያ ፡ ከሆኑት ፡ ሕጐች ፡ መካከል ፡ ቁ. ፬፻፴፯ ፡ ሀ በመባል ፡ የታወቀው ፡ በአንደኛው ፡ ውስጥ ፡ ይገኛል ። ይህ ፡ ቁጥር ፡ በኢትዮጵያ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የተጠቀሰው ፡ ቁጥር ፡ አይደለም ። ቁጥር ፡ ፬፻፴፯ ፡ ሀ የጣሊያን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ የተሻሻለበት ፡ ሲሆን ፡ ከ፲፱፻፴፯ ፡ ዓ.ም. ጀምሮ ፡ በ፲፱፻፵፱ ዓ. ም. በኢትዮጵያ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ እስከተተካበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ጸንቶ ፡ የሚሠራበት ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ነበር ።[68] ቁጥር ፡ ፬፻፴፯ ፡ ሀ በ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ እንደወጣ ፡ ከሌሎች ፡ ጥፋቶች ፡ መካከል ፡ ያለሕግ ፡ ጠብመንጃ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ፈንጅ ፡ መሣሪያ ፡ የያዘን ፡ ሰው ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ በሚደርስ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ፪ሺ፭፻ ፡ ብር ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ በሁለቱም ፡ በእስራትም ፡ በገንዘብም ፡ መቀጮ ፡ እንዲቀጣ ፡ ያደርጋል ። ከዚህ ፡ በመለየት ፡ የኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፯፻፷፬ ፡ ለተመሳሳይ ፡ ጥፋት፡ "እስከ ፡ ፭ ፡ ብር ፡ በሚደርስ ፡ መቀጫ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ስምንት ፡ ቀን ፡ በሚደርስ ፡ በማረፊያ ፡ ቤት፡ እስራት ፡"[69] እንዲቀጣ ፡ በማድረግ ፡ አሳንሶ ፡ ወስኖታል ። ይህንን ፡ ልዩነት ፡ አንድ ፡ የጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍ/ቤት ፡ ዳኛ ፡ ሲያብራሩ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ያለ ፡ ሕግ ፡ ጠብመንጃ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ፈንጅ ፡ መሣሪያ ፡ ይዞ ፡ በመረብ ፡ ወንዝ ፡ (የኤርትራንና ፡ የትግሬን ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ በሚያዋስነው ፡) በአንድ ፡ በኩል ፡ ቢገኝ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ በሚያሳስር ፡ የሚያስቀጣው ፡ ከወንዙ ፡ በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ከተገኘ ፡ ለአንድ ፡ ሣምንት ፡ ብቻ ፡ በመቆየት ፡ ነው ፡ የሚቀጣው ፡ ሲሉ ፡ ገልጸውታል ።

<u>የነውሬታ ፡ የፍርድ ፡ ጉዳይ ፡</u>[70] ከ፲፱፻፷፩ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረቱ ፡ <u>የነውሬታ ፡ የፍርድ ፡ ጉዳይ</u> ፡ ውስጥ ፡ ያለሕግ ፡ ጠብመንጃ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ፈንጂ ፡ መሣሪያ ፡ ይዞ ፡ መገኘት ፡ የሚለውን ፡ ክፍል ፡ የከፍተኛው ፡ ፍ/ቤት ፡ ተቀብሎታል ። በ "ቁጥር ፡ ፬፻፴፯ ፡ ሀ" ፡ መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተከሳሹ ፡ ጥፋተኛ ፡ ሆኖ ፡ ስለአገኘው ፡ የሁለት ፡ ዓመት ፡ እስራት ፡ ፈረደበት ። ሌሎች ፡ ተከሣሾችና ፡ ጭብጦች ፡ ስለ

---

65. የወ. መ. ሕ. ቁ. ፩፻፳፪ና ፡ ፻፴፯ ፡
66. የወ. መ. ሕ. ቁ. ፳፯ ፡ ፴፪ ፡ ፴፮ና ፡ ፴፯ ፡
67. ለቁ. ፬፻፴፯ (ሀ) ሙሉ ፡ ቃል ፡ በተቀጥላ ፡ ፩ለ ፡ ተመልከት ።
68. የግርጌ ፡ ማስረጃ ፡ ፷፪ ፡ ተመልከት ።
69. ቁ. ፯፻፷፬ ፡ የደንብ ፡ ተላላፊ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ነው ። በቁ. ፬፻፴፯ ሀና ፡ በቁ. ፯፻፷፬ አስተሳሰብ ፡ መካከል ፡ ከፍተኛ ፡ የሐሳብ ፡ ልዩነት ፡ ያለ ፡ ይመስላል ። አንዱ - ከባድ ፡ ወንጀል ፡ ያደረገውን ፡ ሌላው ፡ አነስተኛ ፡ ጥፋት ፡ አድርጐ ፡ ይቆጥረዋል ።
70. ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ <u>ከሳሽ ፤ እነወሬታ ፡ ተከሣሾች</u> ፡ የወንጀል ፡ ፋይል ፡ ቁጥር ፡ ፷፫/፶፯ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ን. ነ. መንግሥት ፡ የከፍተኛው ፡ ፍ/ቤት ፡ ሐምሌ ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. መንደፈራ ፡ ላይ ፡ የተሰጠ ፡ ውሳኔ ። ያልታተመ ፡ በቀ. ኃ. ሥ. ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ፋክልቲ ፡ አርሽቭ ፡ ቤት ።

አሉበት ፡ ክሱ ፡ ይበልጥ ፡ የተወሳሰበ ፡ ነው ። "ቁጥር ፡ ፩፻፴፯ ፡ ሀ" አሁንም ፡ የጸና ፡ ሕግ ፡ መሆኑን ፡ ለማሳየት ፡ ብቻ ፡ ይህ ፡ ቁጥር ፡ ተጠቅሶ ፡ ነበር ። እንደአጋጣሚ ፡ ሆኖ ፡ ተከሳሾቹ ፡ የተያዙበት ፡ ቦታ ፡ ከመረብ ፡ ወንዝ ፡ (የትግሬ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ወሰን ፡) የራቀ ፡ አልነበረም ።

## ፮. ሕጉ ፡ የወጣበትን ፡ ዓላማ ፡ (ፖሊሲ) ስንመለከተው ፡— ከፍ/ቤት ፡ የተገኘ ፡ አዲስ ፡ ፍንጭ ።

የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፫ና ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ቁጥሮች ፡ ፴፫ና ፡ ፴፭ ፡ ወደተቃራኒ ፡ አቅጣጫዎች ፡ እንዴት ፡ እንደሚመሩ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሊያስብ ፡ ይችላል ። ቅጣትን ፡ የሚመለከት ፡ አንድ ፡ ልዩ ፡ ሕግ ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ በአንድ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ብቻ ፡ እንዲሠራ ፡ ማድረግ ፡ "በሕግ፡ እኩል ሆኖ ፡ መጠበቅ ፡" የሚለው ፡ ጥያቄ ፡ በጣም ፡ ቀርቦ ፡ ይገኛል ። ስለሽፍቶች ፡ የወጣውን ፡ ሕግ ፡ ጽኑ ፡ አድርጎ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ማዋል ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ አይደለም ፡ (ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ጋር ፡ ይቃረናል) ብሎ ፡ ፍ/ቤት ፡ ቢወስን ፡ አያስደንቅም ።

ስለሽፍቶች ፡ የወጣው ፡ ሕግም ፡ ሆነ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፴፯ ፡ ሀ ፡ የወጡት ፡ የኤርትራ ፡ መንግሥት ፡ ገጥሞት ፡ የነበረውን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ችግር ፡ ለማቃለል ፡ ተብሎ ፡ በፌደራሉ ፡ አስተዳደር ፡ ጊዜ ፡ ሲሆን ፡ በፖሊሲ ፡ ረገድ ፡ ስንመለከተው ፡ ደግሞ ፡ ዛሬም ፡ አስፈላጊ ፡ ናቸው ፡ ወይ? ብለን ፡ እንጠይቅ ፡ ይሆናል ። በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ በደራሲው ፡ ለፖሊስ ፡ መኰንኖች ፡ ለሕግ ፡ አስከባሪዎች ፡ ለከፍተኛ ፡ ፍ/ቤትና ፡ ለጠቅላይ ፡ ን. ነ. ፍ/ቤት ፡ ዳኞች ፡ እንዲሁም ፡ ለሌሎች ፡ ለፍ/ቤትና ፡ ለመንግሥት ፡ ሹማምንት ፡ ከተደረጉት ፡ የቃል ፡ መጠይቆች ፡[71] ለመረዳት ፡ እንደተቻለው ፡ በ፲፱፻፶፭ ዓ. ም. መካከል ፡ ላይ ፡ የነበረው ፡ "የሽፍታ" ችግር ፡ ወደ ፡ መጥፋት ፡ ላይ ፡ ነው ። በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ መገናኛን ፡ ሠላም ፡ የነሱት ፡ ተራ ፡ ወንበዴዎች ፡ ከመንግሥቶች ፡ መዘዋወር ፡ አለመረጋጋት ፡ (አለመረጋገጥ) ጋር ፡ የተያያዘ ፡ ይመስላል ።[72] በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ እንደዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ችግር ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ እንደወትሮው ፡ የተለመደ ፡ ስላልሆነ ፡ ከሌላው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ግዛቶች ፡ የተለየ ፡ አይመስልም ። በተጨማሪም ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ የፖለቲካ ፡ ጥፋት ፡ የፈጸሙ ፡ ሰዎች ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ ቢቀርቡ ፡ ስለሽፍቶች ፡ የወጣው ፡ ሕግም ፡ ሆነ ፡ ሌሎች ፡ ተመሳሳይ ፡ ሕጎች ፡ አይሠራባቸውም ። በእንደዚህ ፡ ዓይነቶቹ ፡ ክሶች ፡ ላይ ፡ በጥቅም ፡ ላይ ፡ የሚውለው ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ነው ። ስለሽፍቶች ፡ የወጣው ፡ ሕግም ፡ ሆነ ፡ ሌሎች ፡ ሕጎች፡ የወጡት ፡ ተራ ፡ ወንበዴዎች ፡ ለሚፈጽሙት ፡ ጥፋት ፡ ብቻ ፡ እንዲያገለግሉ ፡ ታቅዶ ፡ ነው ።

ፍርዱ ፡ ስለተለወጠው ፡ የመስፍን ፡ ክስ ፡[73] ምናልባት ፡ እንደሽፍታ ፡ መቀነስ ፡ የመሳሰሉት ፡ ጭብጥ ፡ የአካባቢዎች ፡ ለውጥ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። የጠቅላይ ፡ ንጉሠ ነገሥት ፡ ፍ/ቤት ፡ ለዚህ ፡ አርዕስት ፡ መሪ ፡ የነበረውን ፡ የነባህታን ፡ ክስ ፡ ፍርድ ፡

71. እነዚህ ፡ የቃል ፡ መጠይቆች ፡ በጥር ፡ ወር ፡ ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ.ም. በአሥመራ ፡ ተደረጉ ።

72. ትሬቫስኪስ ፡ እላይ ፡ የተጠቀሰ ፡ "ራስን ፡ ወደመቻል ፡ መሸጋገር" በሚለው ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ ስለነበረው ፡ አንዳንድ ፡ የሽፍታ ፡ ችግር ፡ ቀደም ፡ ያለ ፡ ታሪክ ፡ ገለጻውን ፡ እስከጨረሰበት ፡ እስከ ፡ ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ. ም. ድረስ ፡ ያቀርባል ።

73. እነመስፍን ፡ ይግባኝ ፡ ባዮች ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ የወንጀል ፡ ይግባኝ ፡ ፋይል ፡ ቁጥር ፡ ፳፩/፷፬ ፡ በጠቅላይ ፡ ን. ነ. ፍ/ቤት ፡ ሰኔ ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፯ ፡ ዓ.ም.በአሥመራ ፡ የተሰጠ ፡ ውሳኔ ፡ የክሱ ፡ ቃል ፡ በተቀጥላ ፡ ፪ሀ ፡ ገጽ ፡ ፩፻፺፩ ፡ ተያይዞ ፡ ይገኛል ።

የለወጠውና ፡ ስለሽፍቶች ፡ የወጣውም ፡ ሕግ ፡ በሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ረገድ ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ አይደለም ፡ ያለው ፡ አሥር ፡ ዓመት ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ የፌደራሉ ፡ አስተዳደር ፡ ወዲያው ፡ እንደቀረ ፡ ለጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍ/ቤት ፡ ስለሽፍቶች ፡ በወጣው ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ አንድ ፡ ክስ ፡ ቀርቦለት ፡ ነበር ። በትእዛዝ ፡ ፳፯ ፡ መሠረት ፡ ስለሽፍቶች ፡ የወጣው ፡ ሕግ ፡ እንደ ፡ "አስፈላጊ" ሕግ ፡ ተቆጥሮ ፡ እንዲቆይ ፡ በማሰብ ፡ የጠቅላይ ፡ አቃቤ ፡ ሕግ ፡ ጽ/ቤት ፡ ወስኖ ።[74] ጥያቄው ፡ ፍ/ቤት ፡ ሕጉን ፡ ተቀብሎ ፡ ይቀጥል ፡ ወይም ፡ ይተወው ፡ እንደሆነ ፡ ነበር ። በነመስፍን ፡ ፍርድ ጉዳይ ፡ በ፲፱፻፷ ፡ ዓ. ም. የመጀመሪያ ፡ ተከታታይ ፡ ዓመቶች ፡ ላይ ፡ የፌደራሉ ፡ አስተዳደር ፡ ከመቅረቱ ፡ በፊት ፡ በተደረጉ ፡ ፍሬ ፡ ነገሮች ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ክስ ፡ ለጠቅላይ ፡ ን. ነ. ፍ/ቤት ፡ ቀርቦለት ፡ ነበር ። የከፍተኛው ፡ ፍ/ቤት ፡ የመጀመሪያ ፡ ክስ ፡ ሰሚ ፡ ሆኖ ፡ ሦስት ፡ ተከሣሾች ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ጥፋቶች ፡ ወንጀለኞች ፡ ሆነው ፡ ስላገኛቸው ፡ ስለሽፍቶች ፡ በወጣው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ በያንዳንዳቸው ፡ ላይ ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ በየነባቸው ። ነገሩን ፡ በይግባኝ ፡ ለጠቅላይ ፡ ን. ነ. ፍ/ቤት ፡ አቅርበው ፡ ተከሳሽ ፡ ይግባኝ ፡ ባዮች ፡ ከሌሎች ፡ ክርክሮቻቸው ፡ መካከል ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ እንጅ ፡ ስለሽፍቶች ፡ በወጣው ፡ ሕግ ፡ ልንከሰስ ፡ አይገባም ፡ የሚል ፡ ነበር ። ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ካቀረባቸው ፡ የመቃወሚያ ፡ ክርክሮች ፡ መካከል ፡ ከፍተኛ ፡ ቦታ ፡ የተሰጠው ፡ ወንጀሎቹ ፡ የተፈጸሙት ፡ በፌዴራሉ ፡ አስተዳደር ፡ ጊዜ ፡ ነበር ፡ ለሚለው ፡ ነበር ።[75] በዚህ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ክርክር ፡ ላይ ፡ ፍ/ቤት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ግምት ፡ እንደሰጠው ፡ ለመናገር ፡ አስቸጋሪ ፡ ቢሆንም ፡ በጠቅላላው ፡ ተከሳሽ ፡ ይግባኝ ፡ ባዮቹ ፡ በተከሰሱበት ፡ ወንጀል ፡ ስለሽፍቶች ፡ በወጣው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ጥፋተኞች ፡ ሆነው ፡ አግኝቷቸዋል ።

ከነመስፍን ፡ ፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ ወዲህ ፡ ለፍ/ቤቱ ፡ ብዙ ፡ ክሶች ፡ ሲቀርቡ ፡ ስለሽፍቶች ፡ የወጣው ፡ ሕግ ፡ ቀዋሚ ፡ ሕግ ፡ ሆኖ ፡ ነበር ። ከአሥር ፡ ዓመቶች ፡ በኋላ ፡ የነመስፍንን ፡ ፍርድ ፡ በመለወጥና ፡ ስለሽፍቶች ፡ የወጣው ፡ ሕግ ፡ በሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በኩል ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ ሆኖ ፡ ያለመገኘት ፡ የነባህታ ፡ ፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ የነበረውን ፡ ሕጋዊ ፡ አቋም ፡ ለውጦታል ። ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ስለሽፍቶች ፡ በወጣው ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ በጠቅላይ ፡ ን. ነ. ፍ/ቤት ፡ የተሰጠ ፡ አንድ ፡ ውሳኔ ፡ ሲኖር ፡ ያላለቁ ፡ ብዙ ፡ ሌሎች፡ ክሶችም ፡ ይገኛሉ ።

የነወራሲ ፡ የፍርድ ፡ ጉዳይ ፤[76] በጣም ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ የቀረበው ፡ የነወራሲ ፡ የፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ ሌሎች ፡ የጠቅላይ ፡ ን. ነ. ፍ/ቤት ፡ ዳኞች ፡ በድምፅ ፡ ብልጫ ፡ የከፍተኛውን ፡ ፍ/ቤት ፡ ውሳኔ ፡ ከለወጡ ፡ በኋላ ፡ የነባህታንም ፡ የፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ ማየት ፡ ቀጥለው ፡ ስለሽፍቶች ፡ በወጣው ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተውን ፡ ክስ ፡ ሳይቀበሉት ፡ ቀሩ ። ፍ/ቤቱም ፡ "... በ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. ስለሽፍቶች ፡ የወጣው ፡ ሕግ ፡ ጊዜያዊ ፡ ሲሆን ፡ የታወጀው ፡ በፌደራሉ ፡ አስተዳደር ፡ ጊዜ ፡ ነበር ። በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ,

74. ምናልባት ፡ መታወስ ፡ ያለበት ፡ በፌዴራሉ ፡ አስተዳደር ፡ ጊዜ ፡ ጠቅላይ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ለኤርትራ ፡ አስተዳደር ፡ ዋና ፡ የሕግ ፡ አማካሪ ፡ መሆኑ ፡ ነው ።

75. "ይግባኝ ፡ ባዮቹ ፡ (ሽፍቶቹ) ፡ ይሀን ፡ ወንጀል ፡ የፈጸሙት ፡ በኤርትራ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ጊዜ ፡ ነው ።"

76. እነወራሲ ፡ ይግባኝ ፡ ባዮች ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ የወንጀል ፡ ይግባኝ ፡ ፋይል ፡ ቁ. ፴፮/፹፬ ፡ በጠ. ን. ነ. ፍ/ቤት ፡ መጋቢት ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ. ም. በአሥመራ ፡ የተሰጠ ፡ ውሳኔ ። የክሱ ፡ ቃል ፡ በተቀጥላ ፡ ፪ለ ፡ ገጽ ፡ ፪፻፲፰ ፡ ተያይዞ ፡ ይገኛል ።

በመላው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ጸንቶ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የዋለውና ፡ ደግሞም ፡ በቁጥር ፡ ፲፱፻፴፯ ፡ "ስለሽፍታ" የተደነገገ ፡ ያለበት ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ለመሆኑ ፡ ጥያቄ ፡ የለውም " ብሏል ። ወደተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ መለስ ፡ በማለት ፡ ፍ/ቤቱ ፡ ሲያሳስብ ፡ "አንቀጽ ፡ ፴፯ ፡ 'ማንም ፡ ሰው ፡ በሕግ ፡ እኩል ፡ ሆኖ ፡ ይጠበቃል ፡' ሲል ፡ አንቀጽ ፡ ፴፰ ፡ ደግሞ ፡ 'በብሔራዊ ፡ (ሲቪል) መብቶች ፡ ረገድ ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ አይደረገም ፡' የሚል ፡ ይገኝበታል ። በተጨማሪም ፡ አንቀጽ ፡ ፶፬ ፡ 'ቅጣት ፡ የሚፈጸመው ፡ በአጥፊው ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡' ሲል ፡ አንቀጽ ፡ ፻፳፪ ፡ 'ይህ ፡ የተሻሻለው ፡ ሕግ ፡ መንግሥት ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ ነው ። ወደፊትም ፡ የሚሠሩ ፡ ሕጎች ፡ ድንጋጌዎች ፡ ፍርዶች ፡ ውሳኔዎች ፡ ሁሉ ፡ ከዚህ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ጋር ፡ የማይስማሙ ፡ ሲሆኑ ፡ ዋጋ ፡ የሌላቸውና ፡ የማያገለግሉ ፡ ይሆናሉ ።' በማለት ፡ ይናገራል ።" ፍ/ቤቱ ፡ በሰፊው ፡ በአወንታና ፡ በአሉታ ፡ ስለሽፍቶች ፡ የወጣውን ፡ ሕግ ፡ በነወራሲ ፡ ፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ መከራከር ፡ (ማብራራት) እንኳን ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ አልታየውም ፡ የተከተለውም ፡ በነባህታ ፡ ፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ የተሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ፍ/ቤቱም ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ በፋይል ፡ ቁጥር ፡ ፫፬/፳፫ ፡ ሰኔ ፡ ፳፮ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ. ም. የጠቅላይ ፡ ን. ነ. ፍ/ቤት ፡ እንደወሰነው ፡ በ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. ስለሽፍቶች ፡ የወጣው ፡ ሕግ ፡ ተሽሯል ፡" ብሏል ። ከዚያም ፡ በመቀጠል ፡ እንዲህ ፡ ብሏል ፡ "በአዋጅ ፡ ፻፺፩ ፡ ፲፱፻፶፮ ፡ ዓ. ም. ቁ. ፲፫ ፡ መሠረት ፡ የበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የበላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የሰጡትን ፡ ውሳኔዎች ፡ እንዲከተሉ ፡ ተደርጓል ።" በሌላ ፡ አነጋገር ፡ የከፍተኛው ፡ ፍ/ቤት ፡ የነወራሲን ፡ ፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ እንደ ፡ መጀመሪያ ፡ ክስ ፡ ሰሚ ፡ ፍ/ቤት ፡ ሆኖ ፡ ውሳኔ ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ የነባህታን ፡ ፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ ባለመከተሉ ፡ በጠቅላይ ፡ ን. ነ. ፍ/ቤት ፡ ተወቅሷል ።

ስለፍ/ቤቶች ፡ የወጣው ፡ አዋጅ ፡[77] ወደ አዋጅ ፡ ፻፺፩ ፡ መለስ ፡ ብሎ ፡ መመልከት ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ውጤቱ ፡ ጥሩ ፡ ቢሆን ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ ሥርዓት ፡ ውስጥ ፡ አሁንም ፡ በኤርትራ ፡ ሌላ ፡ የሥነ ፡ ሥርዓትን ፡ አለመስተካከል ፡ ይፈጥራል ። በ፲፱፻፴፪ ፡ ዓ. ም. በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ "ስለፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የወጣው ፡ አዋጅ ፡" የኢትዮጵያን ፡ ፍ/ቤቶች ፡ የሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ከፍ ፡ ለማድረግ ፡ ጠበቅ ፡ ያለ ፡ ውጤቶች ፡ እንዲኖሩት ፡ ታስቦ ፡ ነበር ። ከአዲሱ ፡ አዋጅ ፡ ድንጋጌዎች ፡ መካከል ፡ አንደኛው ፡ ቁጥር ፡ ፲፫ ፡ "የበላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በሕግ ፡ ረገድ ፡ በሚነሳ ፡ ክርክር ፡ የሰጣቸውን ፡ ውሳኔዎች ፡ የበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ " እንዲከተሉ ፡ ያደርጋቸዋል ። ከዚህም ፡ ሌላ ፡ አዋጁ ፡ "ግንቦት ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ. ም. ጀምሮ ፡ የፀና" እንዲሆን ፡ ታስቦ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ወዲያውኑ ፡ ሌላ ፡ ማሻሻያ ፡ አዋጅ ፡ ወጥቶ ፡ በ፲፱፻፴፪ ፡ ዓ. ም. ስለፍርድ ፡ ቤቶች የወጣውን ፡ አዋጅ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ሙሉ ፡ ውጤት ፡ እንዲኖራቸው ፡ ከመደረጉ ፡ በፊት ፡ ማስተካከል ፡ ስለአስፈለገ ፡ በ፲፱፻፴፪ ፡ ዓ. ም ስለፍ/ቤቶች ፡ የወጣው ፡ አዋጅ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ውሎ ፡ ውጤት ፡ እንዳያስገኝ ፡ ታገደ ።[78] አጋጁ ፡ አዋጅ ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡

---

77. ስለፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የወጣ ፡ አዋጅ ፡ አዋጅ ፡ ቁ. ፻፺፭ ፡ ፲፱፻፴፪ ፡ ዓ. ም ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፳፪ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁ. ፯ ፡ ስለፍ/ቤቶች ፡ በወጣው ፡ አዋጅ ፡ ላይ ፡ የተደረገውን ፡ የመግቢያ ፡ ጽሑፍ ፡ በአልክሳንድራ ፡ ሃማዊ ፡ የተደረሰውን ፡ "በ፲፱፻፴፪ ፡ ስለወጣው ፡ ስለፍ/ቤቶች ፡ የወጣ ፡ አዋጅ ።" ተመልከት ፤ ያልታተመ ፡ ፲፱፻፴፬—፭ ፡ በቀ. ኃ. ሥ. ዩ ፡ የሕግ ፡ ፋከልቲ ፡ አርሽቭ ፡ ቤት ፡ ይገኛል ።

78. ስለፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የወጣ ፡ (የተሻሻለው) አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፫ ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ. ም. ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፳፪ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፲፯ ።

በሥራ ፡ ላይ ፡ ውሎ ፡ ውጤት ፡ ያስከተለ ፡ አይመስልም ። ስለፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የወጣው ፡ አዋጅ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ በትክክል ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ የተደረገው ፡ ወዲያውኑ ፡ በአዋጅ ፡ እንደፀደቀ ፡ ነው ። የመጀመሪያው ፡ አዋጅ ፡ እንዳይሠራበት ፡ ያገደው ፡ አዋጅ ፡ በወጣበት ፡ ጊዜ ፡ በኤርትራ ፡ የሚገኙት ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ስለ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የወጣውን ፡ አዋጅ ፡ (የታገደውን ፡) እንዲሠሩበት ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ በሰርኩለር ፡ (በደብዳቤ ፡) ፈቅዶላቸው ፡ ነበር ።[79] ስለዚህ ፡ ጠቅላይ ፡ ን. ነ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የወጣውን ፡ አዋጅ ፡ ተመልክቶ ፡ መጥቀሷና ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በነባህታ ፡ ፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ የተሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡ መከተል ፡ ነበረበት ፡ ማለቱ ፡ በእርግጥ ፡ ትክክለኛ ፡ አባባል ፡ ይመስላል ። ስለፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የወጣውን ፡ አዋጅ ፡ የመሳሰሉ ፡ ሕጎች ፡ ወይም ፡ በተመሳሳይ ፡ ክስ ፡ ላይ ፡ በፊት ፡ የተሰጠውን ፡ ፍርድ ፡ የመከተል ፡ ቀዋሚ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ባይኖርም ፡ ቅሉ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ የበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በበላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የተሰጡ ፡ ውሳኔዎችን ፡ በቀላሉ ፡ ማግኘት ፡ ቢችሉ ፡ የበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ለመለየት ፡ ጥሩ ፡ ምክንያት ፡ እንዲኖራቸው ፡ ያስፈልጋል ። በእርግጥ ፡ ብዙ ፡ የበላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቅርንጫፎች ፡ በመስማማት ፡ በአንድ ፡ መንገድ ፡ ቢበይኑ ፡ የበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በተለየ ፡ መንገድ ፡ መበየን ፡ ፍሬቢስ ፡ ይሆናል ፤ ምክንያቱም ፡ በይግባኝ ፡ መለወጡ ፡ የማይቀር ፡ ነው ።[80]

## ፫. የጋራ ፡ ኃላፊነት

### ስለሽፍቶች ፡ በወጣው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፤

ስለሽፍቶች ፡ ወደወጣው ፡ ሕግ ፡ እንደገና ፡ መለስ ፡ ያልን ፡ እንደሆነ ፡ በነባህታ ፡ ፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ የሕጉ ፡ የመጀመሪያ ፡ ክፍሎች ፡ እንዲሠራባቸው ፡ ማድረግ ፡ በሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ረገድ ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ ሆነው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንዳላገኛቸው ፡ ይታወሳል ።[81]

ስለሽፍቶች ፡ ከወጣው ፡ ሕግ ፡ አንዳንድ ፡ ክፍሎች ፡ በሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ረገድ ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ ሆነው ፡ አለመገኘታቸው ፡ በእንደዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ትችት ፡ ከተነሳ ፡ ዘንድ ፡ ስለሕጉ ፡ አጠር ፡ ያለ ፡ ጠቃሚ ፡ ትንተና ፡ ማቅረብ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። የክፍሎች ፡ ፪ ፡ ፫ ፡ ፬ና ፡ ፭ ፡ በሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ረገድ ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ አለመሆን ፡ እንደሚታየው ፡ ብቻ ፡ የበረዶ ፡ ክምር ፡ ቅራፊ ፡ የሚመሳሰል ፡ ነው ። እነዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ አይደሉም ፡ ያላቸው ፡ ክፍሎች ፡ በአንዳንድ ፡ በሌሎች ፡

---

79. የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ያስተላለፈውን ፡ ደብዳቤ ፡ (ሰርኩለር) ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ. ም. ተመልከት ። አር. ኤ. ሴድለር ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፍትሐብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቀ. ኃ. ሥ. ዩኒቨርሲቲ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፷፰ ፡ ዓ.ም. በገጽ ፡ ፱ ፡ ላይ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ። በ፲፱፻፷፭ ፡ ዓ. ም. የወጣው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፍትሐብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ በመቅረቡ ፡ የተለያየ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የመኖር ፡ ችግር ፡ እንዲቀር ፡ ሆኗል ። ብዙዎቹ ፡ ችግሮች ፡ ይጥፉ ፡ እንጂ ፡ በእርግጥ ፡ ሁሉም ፡ አልጠፉም ። በአዋጁ ፡ በቁጥር ፡ ፲፭ ፡ የሚገኘው ፡ በተመሳሳይ ፡ ክሶች ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ውሳኔ ፡ የመከተልን ፡ ነገር ፡ በፍ/ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ አለመገኘቱ ፡ አንድ ፡ ምሳሌ ፡ ነው ።

80. በተመሳሳይ ፡ ክሶች ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ውሳኔ ፡ መከተል ፡ እንግሊዝና ፡ ተመሳሳይ ፡ የሕግ ፡ ሥርዓት ፡ በሚከተሉት ፡ አገሮችና ፡ (ኰመን ፡ ሎው ፡ ሲስተም) በፈረንሳይና በሕግ ፡ ሥርዓት ፡ በሚመሳሰሏት ፡ (ሲቪል ፡ ሎው ፡ ሲስተም) አገሮች ያለውን ፡ ከፍተኛነትና ፡ ጥቅም ፡ እያወዳደሩ ፡ ለመመራመር ፡ በሾን ፡ መኽረን ፡ የተጻፈውን ፡ ተመልከት ። ሲቪል ፡ ሎው ፡ ሲስተም ፡ ኒው ፡ ዮርክ ፡ ፲፱፻፵፯ ዓ. ም. ገጽ ፡ ፰፻፷፩—፰፻፶፬ ፡

81. እላይ ፡ ገጽ ፡ 267 ፡ ተመልከት ፡

የሕጉ ፡ ክፍሎች ፡ ሲታዩ ፡ ሊጎዱ ፡ የማይችሉና ፡ ስህተት ፡ የሌለባቸው ፡ ናቸው ። ፍርድ ፡ ቤቶቹ ፡ በነባህታና ፡ በነወራሲ ፡ የፍርድ ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ እነዚህን ፡ ሌሎቹን ፡ ክፍሎች ፡ እንዲመረምሩ ፡ ያሳሰባቸው ፡ አልነበረም ። ገባ ፡ ብለው ፡ ያልመረመሩበትም ፡ ምክን ያት ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በፊታቸው ፡ የቀረበላቸውን ፡ ክስ ፡ ለመወሰን ፡ ከሚፈለገው ፡ በላይ ፡ ማድረግ ፡ የለባቸውም ፡ በሚለው ፡ መሠረታዊ ፡ ዓላማ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ። ምንም ፡ እንኳን ፡ ፍርድ ፡ ቤቶቹ ፡ ሌሎቹ ፡ ክፍሎች ፡ ሕገ ፡ መንግሥ ታዊ ፡ አይደሉም ፡ ብለው ፡ ባይወስኑም ፡ ቅሉ ፡ ስለሽፍቶች ፡ የወጣውን ፡ አዋጅ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ማዋል ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ አይደለም ፡ሲሉ ፡ ሰፋ ፡ ባለ ፡ አገላለጽ ፡ ይህ ፡ አባባላቸው ፡ በክሶቹ ፡ ላይ ፡ በተነሱት ፡ በተለይም ፡ በክፍሎች ፡ ፪ ፡ ፫ ፡ ፬ና ፡ ፭ ፡ ላለው ፡ ድንጋጌ ፡ ብቻ ፡ የተወሰነ ፡ አይመስልም ።

ከሕገ ፡ መንግሥታዊም ፡ ሆነ ፡ ከወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በኩል ፡ ሲታይ ፡ ምናልባት ፡ ስለሽፍቶች ፡ በወጣው ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ ሁለቱ ፡ በጣም ፡ የሚ ያስደንቁት ፡ በጣም ፡ የሚያስቆጡትና ፡ ያልተለመዱት ፡ ሐሳቦች ፡ "የአገርየው (የመ ንደረተኞቹ) ፡ የጋራ ፡ ኃላፊነት" እና ፡ "የቦታ ፡ ኃላፊነት" እየተባሉ ፡ የሚጠሩት ፡ ናቸው ።[82] በወንጀል ፡ ራሱ ፡ ጥፋተኛ ፡ ሳይሆን ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ጥፋት ፡ ኃላፊ ፡ የማ ድረግን ፡ ሐሳብ ፡ ያመለክታሉ ። የአገርየው (የመንደረተኞቹ) ፡ የጋራ ፡ ኃላፊነት ፡ የሚ ለው ፡ ክፍል ፡ ግማሹ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡—

> የማናቸውም ፡ ዘላን ፡ ጐሣ ፡ ወይም ፡ ደንበኛ ፡ መኖሪያ ፡ የቆረቆረው ፡ እንደ/ዘር ትውልዱ/ወገን ፡ የሆነው ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ይህን ፡ አዋጅ ፡ በመተላለፍ ፡ ወን ጀል ፡ ፈጽሞ ፡ ቢገኝ ፡ ቢፈረድበትም ፡ ባይፈረድበትም ፡ ጐሣው ፡ ወንጀሉን ፡ ለማስቀረት ፡ አለመቻሉን ፡ ሆነ ፡ በራሱና ፡ በወገኖቹ ፡ ላይ ፡ ሊደርስ ፡ የሚችለ ውን ፡ ጉዳት ፡ ከቁጥር ፡ ሳያገባ ፡ ወንጀለኛውን ፡ ይዞ ፡ ለፖሊስ ፡ ለማስረከብ ፡ የሚቻለውን ፡ ያህል ፡ የደከመ ፡ መሆኑን ፡ ካላስረዳ ፡ በስተቀር ፡ እያንዳንዱ ፡ የቤተሰብ ፡ ኃላፊ ፡ ወንጀሉ ፡ ለቆየበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ በየወሩ ፡ እስከ ፡ አምሳ ፡ ብር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።[83]

ይኸው ፡ ክፍል ፡ በመቀጠል ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ "ማንኛውም ፡ በራሱ ፡ ጐሣ ፡ ወይም ፡ እንዳ ፡ ውስጥ ፡ ካልተገኘ ፡ አፍራሽ ፡ ማስረጃ ፡ ካልቀረበ ፡ በቀር ፡ በዚህ ፡ አዋጅ ፡ የተመለከተውን ፡ ሕግ ፡ በመተላለፍ ፡ ወንጀል ፡ በመሥራት ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ ይቆጠራል ፡"[84] "የአገርየው (መንደርተኞቹ) ፡ የጋራ ፡ ሃላፊነት ፡" የሚለው ፡ የተወ ረሰው ፡ ከቤተዘመዳም ፡ ሕብረተሰብ ፡ መካከል ፡ እንኳ ፡ እገሌ ፡ ጥፋተኛ ፡ ነው ፡ ቢባል በማስረጃ ፡ ቢረጋገጥበትም ፡ ባይረጋገጥበትም ፡ ሁሉም ፡ ለወንጀሉ ፡ ሃላፊዎች ፡ ይሆ ናሉ ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ አባሉ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ጥፋት ፡ ላለመፈጸም ፡ ማስረጃ ፡ የማቅረብ ፡ ግዴታ ፡ ያለው ፡ ከጐሣዎቹ ፡ ተለይቶ ፡ በነበረው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በመንግሥት ፡ ላይ ፡ አይደለም ።[85]

"የቦታ ፡ ኃላፊነት ፡" የሚለው ፡ ፅንስ ፡ ሐሳብ ፡ቀላልና ፡ አስገራሚ ፡ ነው ። የዝርፊያ ፡ ወንጀል ፡ ለአንድ ፡ ዳኛ ፡ (ማጀስትሬት) የክስ ፡ አቤቱታ ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡

82. እዚህ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ከተሞችን ፡ እንደማይመለከቱ ፡ ሆነው ፡ የተደረጉ ፡ ናቸው።
83. ስለሽፍቶች ፡ የወጣ ፡ ሕግ ፡ ክፍል ፡ ፲ ፡ (፩) ።
84. ስለሽፍቶች ፡ የወጣ ፡ ሕግ ፡ ክፍል ፡ ፲(፪) ፡
85. ማስረጃ ፡ የማቅረብ ፡ ግዴታ ፡ ስለሽፍቶች ፡ ከወጣው ፡ ሕግ ፡ የመጀመሪያ ፡ ክፍል ፡ ጋር ፡ ተመሳሳይነት ፡ እንዳለው ፡ መመልከት ፡ ያሻል ፡

"ወንጀሉ ፡ ከተፈጸመበት ፡ ቦታ ፡ እስከ ፡ ፲ ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ ርቀት ፡ ባለው ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ በሚኖሩት ፡ የቤተሰብ ፡ ሐላፊዎች ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ በተሰረቀው ፡ ንብረት ፡ ዋጋ ፡ ልክ ፡ የገንዘብ ፡ መቀጫ ፡ የመጣል ፡ ሥልጣን ፡ ይኖረዋል" ።[86] ይህም ፡ ማለት ፡ ማንኛውም ፡ ወንጀል ፡ ከተፈጸመበት ፡ በ፲ ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ ዙሪያ ፡ ላይ ፡ የሚኖሩት ፡ ነዋሪዎች ፡ ወንጀል ፡ ከተፈጸመበት ፡ ከ፲ ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ ዙሪያ ፡ ውጭ ፡ ባለመኖራቸው ፡ ብቻ ፡ ለወንጀሉ ፡ ኃላፊዎች ፡ በመሆን ፡ ለተሰረቀው ፡ ንብረት ፡ ግምት ፡ ድርሻቸውን ፡ እንዲከፍሉ ፡ ይቀጣሉ ።[87]

"የጋራ ፡ ኃላፊነት ፡ ሕግ ፡" (ኮሌክቲቭ ፡ ሊያብሊቲ ፡ አክት) ይህ ፡ በቂ ፡ እንዳልሆነ ፡ ሁሉ ፡ ከሦስት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ በ፲፱፻፳ ፡ ዓ.ም. "የጋራ ፡ ኃላፊነት ፡ ሕግ" የተሰኘ ፡ ሌላ ፡ ሕግ ፡ ወጣ ። የዚሁ ፡ ሕግ ፡ ዋና ፡ ክፍል ፡ እንዲህ ፡ ይላል ።[88]

> ከማንኛውም ፡ መንደር ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ ጽኑ ፡ ከሆነበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ በቤት ፡ በእንስሳት ፡ በዛፍ ፡ በእህል ፡ ወይንም ፡ ድርቆሽ ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ቢደርስና ፡ ጉዳት ፡ ከደረሰ ፡ቀን ፡ጀምሮ ፡ እስከ ፡ አሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ከመንደረተኛው ፡ ውስጥ ፡ ጉዳት ፡ የደረሰውን ፡ ለፖሊስ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ካመለከተና ፡ ፖሊሶችም ፡ ወንጀለኛውን ፡ ካላገኙት ፤ ጉዳቱ ፡ ወንጀል ፡ አለመሆኑን ፡ ካላረጋገጡ ፡ በስተቀር ፡ መንደረተኛው ፡ በጋራ ፡ ከ፭፻—፭ሺ ፡ ብር ፡ መቀጫ ፡ ይጣልበታል ።[89]

አሁንም ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ኃላፊነት ፡ ምንም ፡ ጥያቄ ፡ የለም ። ሕጉ ፡ ፍጹም ፡ የወንጀል ፡ ነው ። የሚወሰነውም ፡ መቀጮ ፡ ለወንጀሉ ፡ ጥፋት ፡ ቅጣት ፡ ነው ።[90] "ጥፋት ፡ ምንድነው?" ለሚለው ፡ ቀላል ፡ ጥያቄ ፡ መልሱ ፡ "ማን ፡ ጉዳት ፡ እንዳደረሰ" ፡ ለፖሊስ ፡ አለማስታወቅ ፡ ነው ። መንደሪቱ ፡ ወይም ፡ ነዋሪዎቹ ፡ ማን ፡ ጉዳቱን ፡ እንዳደረሰ ፡ ያውቁ ፡ እንደነበር ፡ ወይም ፡ ማወቅ ፡ እንደነበረባቸው ፡ በእርግጥ ፡ የማያስፈልግ ፡ ቀላል ፡ ያልሆነ ፡ ከሕግ ፡ የራቀ ፡ ጥያቄ ፡ እንደሆነ ፡ ይቆጥረዋል ። መጠየቅ ፡ የሚያስፈልገን ፡ ጥያቄ ፡ መንደሩ ፡ ውስጥ ፡ ስለወንጀሉ ፡ ያወቁ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ለፖሊስ ፡ ማስታወቃቸው ፡ ወይም ፡ አለማስታወቃቸው ፡ ነው ። የኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ከጋራ ፡ ኃላፊነት ፡ ሕግ ፡ ለየት ፡ በማለት ፡ ለተመሳሳይ ፡ ወንጀል ፡ "ለፍርድ ፡ ባለስልጣን ፡ ስላለመግለጽ ፡" ተከሳሹ ፡ "የሚያከራክር ፡ ሕጋዊ ፡ ምክንያት ፡ ሳይኖረው ፡ አድራጊውን ፡ ወንጀለኛ ፡ እያወቀ ፡" ለባለሥልጣኖች ፡ እንዳላስታወቀ ፡ ያስቆጥረዋል ።[91] ከጋራ ፡ ኃላፊነት ፡ ሕግ ፡ የሚገኘው ፡ አንድ ፡ አስደናቂ ፡ ውጤት ፡ በወንጀሉ ፡ የተበደለው ፡ ሰው ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የመንደሩ ፡ አባል ፡ ስለሚሆን ፡ ከመንደሩ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ እንደገና ፡ ድርሻውን ፡ ቅጣት ፡ ስለሚከፍል ፡ እንደገና ፡ በሕጉ ፡ ይበደላል ። የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ "ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በአንድ ፡ ወንጀል ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ አይቀጣም"[92] ሲል ፡ ይህ ፡ በጋራ ፡

---

86. ስለሽፍቶች ፡ የወጣ ፡ ሕግ ፡ ክፍል ፡ ፲፩ ።
87. አንድ ፡ ሰው ፡ በሚኖርበት ፡ ቀበሌ ፡ ቢዘረፍ ፡ መቀጫውን ፡ የመክፈል ፡ ኃላፊነት ፡ እንዳለበት ፡ ወይም እንደሌለበት ፡ ዳኞቹ ፡ ለማወቅ ፡ ፍላጐት ፡ ነበረው ።
88. የ፲፱፻፳ ፡ ዓ.ም. ስለጋራ ፡ ኃላፊነት ፡ የወጣ ፡ ሕግ ፡ በኤርትራ ፡ ጋዜጣ ፡ የታተመ ፡ ፲፪ኛ ፡ ፬ልዩም (፲፱፻፳ ዓ. ም.) ቁ. ፱ ፡ ከተቀጥላ ፡ ፩ሐ ፡ ላይ ፡ ተያይዟል ።
89. የጋራ ፡ ኃላፊነት ፡ ሕግ ፡ ክፍል ፡ ፪
90. "ጉዳቱ (ኪሣራው) በወንጀል ፡ አለመሆኑን ፡ ካላረጋገጠ ፡ በስተቀር ፡ በመንደሩ ፡ ላይ ፡ ቅጣት ፡ ይጣልበታል" ። ክፍል ፡ ፪ ።
91. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፩፻፴፰ ፡ ተመልከት ።
92. የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፶፯ ።

ኃላፊነት ፡ ሕግ ፡ ተበዳይ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ ላላጠፋው ፡ ጥፋት ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ እንዲቀጣ ፡ ይሆናል ።

የሰብሳ ፡ የፍርድ ፡ ጉዳይ ፡[93] በጋራ ፡ ኃላፊነት ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ አንዳንድ ፡ ከባድ ፡ ችግር ፡ በጣም ፡ አስደናቂና ፡ በጣም ፡ ቅርብ ፡ በሆነው ፡ በሰብሳ ፡ ክስ ፡ ላይ ፡ ተገልጧል ። የክሱ ፡ ፍሬ ፡ ጉዳይ ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ። ሰብሳ ፡ በኤርትራ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ በሠራዬ ፡ አውራጃ ፡ የምትገኝ ፡ አንዲት ፡ ትንሽ ፡ መንደር ፡ ናት ። ገብረሚካኤል ፡ ገብረአብ ፡ የሚባለው ፡ መንደረተኛ ፡ ከመንደሩ ፡ ጥቂት ፡ ራቅ ፡ ብሎ ፡ ከሚገኘው ፡ መሬት ፡ የጤፍ ፡ ሰብሉ ፡ ደርሶለት ፡ እህሉን ፡ ለማስገባት ፡ ይጠባበቃል ። የእርሻ ፡ መሬቱ ፡ ከመንደሩ ፡ ትንሽ ፡ ራቅ ፡ ይላል ። ጥቅምት ፡ ፲፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፬ ፡ ዓ. ም. ሌሊት ፡ ያልታወቁ ፡ ሰዎች ፡ እህሉን ፡ አጭደው ፡ ወሰዱት ።

ተበዳዩ ፡ ወዲያው ፡ ስለወንጀሉ ፡ ለፖሊስ ፡ አመልክቶ ፡ በዛ ፡ ያሉ ፡ ተጠርጣሪዎች ፡ ተመርምረው ፡ ነበር ። የመንደሩ ፡ ሽማግሌዎች ፡ የምስክርነት ፡ ቃላቸውን ፡ እንዲሰጡ ፡ ተጠይቀው ፡ ተጠርጣሪዎቹ ፡ ከአቤት ፡ ባዩ ፡ ጋር ፡ ጠብ ፡ እንደነበራቸው ፡ መሰከሩ ። ተጠርጣሪዎቹን ፡ ከወንጀሉ ፡ የሚያገናኝ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ማስረጃ ፡ ባለመኖሩ ፡ ፖሊስ ፡ እንዲለቃቸው ፡ ተገደደ ። ወዲያውኑ ፡ ወንጀሉ ፡ ከተፈጸመ ፡ አሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ስለአለፈ ፡ የመንደርዋ ፡ ሽማግሌዎች ፡ በአቃቤ ፡ ሕጉ ፡ በሰራዬ ፡ አውራጃ ፡ ለቀረበባቸው ፡ የወንጀል ፡ ክስ ፡ ተወካይ ፡ ተከሳሾች ፡ ሆነው ፡ ተገኙ። "ሁለት ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ አንድ ፡ የኢት. ብር ፡ ጉዳት ፡ ማን ፡ ኪሣራ ፡ እንዳደረሰበት ፡ ተከሳሾቹ ፡ ለፖሊስ ፡ ባለማመልከታቸው ፡ ፍ/ቤቱ ፡ ጥፋተኛ ፡ ሆነው ፡ ስለአገኛቸው ፡ በመንደሪቱ ፡ ላይ ፡ የአምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ቅጣት ፡ ጣለባት ። ወደ ፡ ከፍተኛው ፡ ፍ/ቤት ፡ ይግባኙን ፡ ወስደው ፡ ፖሊሶቹ ፡ በምርመራ ፡ ላይ ፡ እንዳሉ ፡ ሙሉ ፡ መተባበር ፡ እንዳደረጉላቸው ፡ ተከሳሾቹ ፡ አመለከቱ ። ከዚህም ፡ መሃል ፡ ተጠርጣሪዎቹ ፡ ሰዎች ፡ ከተበዳዩ ፡ ጋር ፡ ጠብ ፡ እንደነበራቸው ፡ መስክረዋል ። ከፍተኛው ፡ ፍ/ቤት ፡ በሰብሳ ፡ ፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ የአውራጃውን ፡ ፍ/ቤት ፡ ውሳኔ ፡ በድምፅ ፡ ብልጫ ፡" በማጽደቅ ፡ የአብዛኞቹ ፡ ዳኞች ፡ ውሳኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ደመደመ ።

"ይግባኝ ፡ ባዮቹ ፡ ግዴታቸውን ፡ ባለማሟላታቸውና ፡ በተከሰሱበት ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ጥፋተኞቹ ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፡ ብለው ፡ ባለማሳየታቸው ፡ ይግባኙን ፡ ተክልክለዋል ። ንጹህ ፡ ዜጎችን ፡ በነበራቸው ፡ ጠብ ፡ ምክንያት ፡ ጠርጥሮ ፡ መወንጀል ፡ ተገቢ ፡ አይደለም ።"

አንድ ፡ ዳኛ ፡ በውሳኔው ፡ ከሌሎቹ ፡ ዳኞች ፡ ተለይተዋል ።[94] በዚህም ፡ በፍርድ ፡ አሰጣጡ ፡ ከአብዛኛዎቹ ፡ በተለዩበት ፡ ሀሳብ ፡ "የጋራ ፡ ሐላፊነት ፡ ሕግ ፡" "ከባሕላዊ ፡ አውጫጭኝና ፡ የአፈርሳታ ፡ ሕግ ፡" ተመሳሳይ ፡ መሆኑን ፡ አመልክቷል ።[95]

93. የሰብሳ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ይግባኝ ፡ ባዮች ፤ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፤ የወንጀል ፡ ይግባኝ ፡ ፋይል ፡ ቁ. ፷፩/፷፬ ፡ በአሥመራው ፡ ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሰኔ ፡ ፳፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፬ ፡ ዓ.ም. ተወሰነ ። የአብዛኛውንና ፡ የአንስተኛውን ፡ ድምፅ ፡ ውሳኔ ፡ ሙሉ ፡ ቃል ፡ በተቀጥላ ፡ ፪ሐ ፡ ገጽ ፡ ፫፻፬ ፡ ላይ ፡ ተመልከት።

94. ከአብዛኛው ፡ የተለዬ ፡ የተቃውሞ ፡ ውሳኔ ፡ መጻፍ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በጣም ፡ የተለመደ ፡ የፍርድ ፡ ሥራ ፡ አይደለም ። ቢያንስ ፡ ሳይለያይ ፡ በአንድነት ፡ የሚሰጥ ፡ ውሳኔ ከሕግ ፡ ባህል ፡ ክፍል ፡ ነው ። እንግዲህ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ዳኞች ፡ ከአብዛኛው ፡ የተለዩበትን ፡ ተቃውሞ ፡ ሲጽፍ ፡ በጣም ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ የፍርድ ፡ ሐሳብ ፡ የመኖር ፡ ምልክት ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ሊወሰድ ፡ ይቻላል ።

95. ስ. ዚ. ፊሽር ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ተመልከት ። ቀ. ኃ. ሥ. ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፷፬ ፡ ዓ. ም. ፡ ገጽ ፡ ፳፬—፳፰ ፡

ጨመር ፡ አድርገውም ፡—"ምንም ፡ እንኳን ፡ ስለጋራ ፡ ኃላፊነት ፡ ሕግ ፡ ሕጋዊነት ፡ ክርክር ፡ ባይነሳም ፡ ቅሉ ፡ ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ጋር ፡ እንዴት ፡ እንደሚቃረን ፡ ማስ ገንዘቡ ፡ ለሚመጣው ፡ ጊዜ ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ፡" ብለዋል ። የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መን ግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፶፬ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በግልጽ ፡ ዘርዝሮ ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ የበላ ይነት ፡ በአንክሮ ፡ ተመልክተውታል ። እንዲሁም ፡ ውሳኔውን ፡ በለዩበት ፡ ሃሳባቸው ፡ ትእ ዛዝ ፡ ፳፺ ፡ አንቀጽ ፡ ስድስትን ፡ በማውሳት ፡ ቀጠል ፡ አድርገው ፡ "የሕግ ፡ አስፈጻ ሚው ፡ ክፍል ፡ በተሰጠው ፡ ስልጣን ፡ መሠረት ፡ ከሁሉ ፡ በፊት ፡ ከሕገ ፡ መንግ ሥቱ ፡ ጋር ፡ የሚቃረኑትን ፡ ሕጐችና ፡ የውስጥ ፡ ደንቦች ፡ የመሠረዝ ፡ ግዴታ ፡ አለ በት ።"

በመደምደሚያው ፡ ላይ ፡ ዳኛው ፡ በንዴት ፡ መልክ ፡ እንዲህ ፡ ብለዋል ፡ "ሽማግ ሌዎቹ ፡ [ከፖሊሶቹ ፡] የመረዳዳት ፡ መንፈስ ፡ ካሣዩ ፡ በኋላ ፡ ከአቅማቸው ፡ በላይ ፡ መጠየቅ ፡ ሕጋዊ ፡ አይደለም ።" የሰብሳ ፡ ፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ ፍጻሜ ፡ በዚህ ፡ አበቃ ።[96]

ለሌላ ፡ ሰው ፡ ሃላፊ ፡ የሚያደርጉት ፡ ስለ ፡ ሽፍቶቹ ፡ የወጣው ፡ ሕግና ፡ ስለ ፡ ጋራ ፡ ኃላፊነት ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ሁሉ ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ ባለመሆናቸው ፡ ብዙ ፡ ውይይት ፡ ስለማያስፈልግ ፡ በጣም ፡ ግልጽ ፡ ነው ። ለወንጀለኛ ፡ መቅጫው ፡ ሕግ ፡ አቋም ፡ ዘመናዊና ፡ ሊገቡ ፡ የሚችሉ ፡ ሕጋዊ ፡ ሃሳቦችን ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ እንደያዘ ፡ መግለጹ ፡ በቂ ፡ ነው ። ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ "ካልተረጋገጠ ፡ በቀር" ፡ ጥፋተኛ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ማንም ፡ እንዳይገምት ፡ ያረጋግጣል ።[97] ቀጥሎም ፡ "ቅጣት ፡ የሚፈጸመው ፡ በአጥፊው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ።" ይላል ፡[98] ቅጣት ፡ ለአገርየው (መንደርተኛው) ፡ ወይም ፡ ለቦታው ፡ አይደለም ። አንድ ፡ ሰው ፡ የሚቀ ጣው ፡ ላጠፋው ፡ ድርጊት ፡ ሲፈረድበት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡[99] እንጂ ፡ ከዘመዶቹ ፡ መካ ከል ፡ አንዱ ፡ ወይም ፡ ከጐረቤቱ ፡ ወይም ፡ በመንገድ ፡ ተላላፊ ፡ ተደረገ ፡ ለተባለው ፡ ጥፋት ፡ አይደለም ።

ስለሽፍቶች ፡ በወጣው ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ "የአገርየው (የመንደርተኞች) ፡ የጋራ ፡ ሃላፊነት ፡" እና ፡ "የቦታ ፡ ሃላፊነት" ፡ ስለጋራ ፡ ሃላፊነት ፡ በወጣው ፡ ሕግ ፡ "የጋራ ፡ ሃላፊነት" የሚሉት ፡ ሐሳቦች ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ተጠቃለው ፡ ከሚ ገኙት ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ዕንስ ፡ ሃሳቦች ፡ ጋር ፡ በፍጹም ፡ ተቃርነውና ፡ በቀጥታ ፡ ተጋጭተው ፡ ይገኛሉ ። ስለዚህ ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ ሊሆኑ ፡ አይችሉም ።

ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ ያልሆኑት ፡ ስለሽፍቶችና ፡ ስለጋራ ፡ ሃላፊነት ፡ በወጡት ፡ ሕጐች ፡ እንዲሠራባቸው ፡ ያለው ፡ ትክክለኛ ፡ መንገድ ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግ ሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፳፱ ፡ መሠረት ፡ ነው ። በአንቀጽ ፡ ፳፱ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ አገር ፡ የሚ ጠቀምበት ፡ የአስቸኳይ ፡ ጊዜ ፡ አዋጅና ፡ የመሳሰሉትን ፡ በማወጅ ፡ "አደጋ ፡ የሚያ

96. ምናልባት ፡ ይህን ፡ ጽሑፍ ፡ በሚጽፍበት ፡ ጊዜ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ መጽ ሐፍ ፡ ፮ ፡ መሠረት ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ችሎት ፡ እንዲመረመር ፡ ማመልከቻ ፡ ቀርቦ ፡ እንደሆን ፡ ደራ ሲው ፡ አያውቅም ። የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፲፻፹፪ ፡ ሲነበብ ፡ በማናቸ ውም ፡ ሁኔታ ፡ ሁለተኛ ፡ ይግባኝ ፡ የሚፈቅድ ፡ ቢመስልም ፡ ቁጥር ፡ ፲፻፷፭ (፫) ዝቅተኛ ፡ ፍ/ቤቶች ፡ በማይስማሙበት ፡ መስኮች ፡ ይግባኙን ፡ ለመመጠን ፡ የታቀደ ፡ መምሰሉን ፡ አስተውል ።

97. የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፶፫ ፡

98. የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፶፬ ፡

99. የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፶፬

መጣውን ፡ ነገር ፡ ለማስወገድና ፡ አስፈላጊውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ያደርጋል ፡፡"[100] ስለሽፍቶችና ፡ ስለ ፡ ጋራ ፡ ሃላፊነት ፡ ሕጐች ፡ በፌዴራሉ ፡ አስተዳደር ፡ ጊዜ ፡ ከነበረው ፡ የኤርትራ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ጋር ፡ ያላቸው ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊነት[101] ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ ከ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ. ም. በኋላ ፡ አገር ፡ የሚጠቀምበት ፡ የአስቸኳይ ፡ ጊዜ ፡ አዋጅን ፡ እንዲጨምር ፡ ወይም ፡ የሕጐች ፡ ክፍል ፡ እንዲሆኑ ፡ ስለአሻሻሉ ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ አለመሆናቸው ፡ መሠረት ፡ የለውም ፡ ብሎ ፡ ለመደምደም ፡ ያስችላል ፡፡[102]

## ፯. ሥርዓቱን ፡ ለማስተካከል ፡ በጥብቅ ፡ መመርመር ፡፡

እንደሕገ ፡ መንግሥታዊነት ፡ ሕጋዊነት ፡ ወይም ፡ የአንድ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ አሰፈላጊነት ፡ ካሉት ፡ ቀዋሚ ፡ ጥያቄዎች ፡ በላይ ፡ የሕግ ፡ ሥርዓትን ፡ ለማስተካከል ፡ የሚደረግ ፡ ጥልቅ ፡ ምርምር ፡ እንዴትና ፡ በማን ፡ መፍትሔያቸውን ፡ ለማግኘት ፡ እንደሚቻልና ፡ መደረግም ፡ እንዳለበት ፡ ያሉት ፡ ታላቅ ፡ የሕግ ፡ ችግሮች ፡ እንዲከተሉ ፡ ያደርጋል ፡፡ ይህ ፡ ወደ ፡ ትእዛዝ ፡ ቁ. ፳፯ ፡ ይመልሰናል ፡፡ ትእዛዝ ፡ ፳፯ ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ ጸንተው ፡ የሚሠራባቸው ፡ ሕጐች ፡ ሁሉ ፡ "ላለው ፡ የአስተዳደር ፡ ሥራ ፡ መቀጠል ፡ አስፈላጊ ፡ እስከሆነበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡"[103] "እንዳሉ ፡ ጸንተው ፡ የሚሠራባቸው ፡ ሆነው ፡ ይቆያሉ ፡ ይላል ፡፡" ነገር ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ሕግ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ፡ ወይም ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ የሚወስን ፡ ማን ፡ ነው?

<u>በስብሳ</u> ፡ ፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ በአነስተኛ ፡ ድምፅ ፡ የተወሰነው ፡ የጋራ ፡ ሃላፊነት ፡ ሕግ ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ አይደለም ፡ በማለት ፡ ከደመደመ ፡ በኋላ ፡ "የሕግ ፡ አስፈጻሚው ፡ ክፍሎች ፡ በተሰጣቸው ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ ከሁሉ ፡ በፊት ፡ ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ጋር ፡ የሚቃረኑትን ፡ ሐሳቦችና ፡ የውስጥ ፡ ደንቦች ፡ የመሰረዝ ፡ ግዴታ ፡ አለባቸው ፡፡" በማለት ፡ አመልክቷል ፡፡

ይህ ፡ ሃሳብ ፡ የሚያሳየው ፡ አንድን ፡ ሕግ ፡ አስፈላጊ ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ ለመሰረዝ ፡ በተቀዳሚ ፡ ግዴታ ፡ ያለበት ፡ የሕግ ፡ አስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ ነው ፡፡[104] ሆኖም ፡ ይህ ፡ ሃሳብ ፡ በብዛት ፡ የተወሰነ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ሌላው ፡ ቢቀር ፡ በዚህ ፡ ክስ ፡ ላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ራሱ ፡ ክሱ ፡ የተመሠረተበትን ፡ ሕግ ፡ የመሠረዝ ፡ እርምጃ ፡ ይወስድ ፡ እንደነበር ፡ መግለጽ ፡ አለበት ፡፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ለሕግ ፡ ተርጓሚው ፡ ክፍል ፡

---

100. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ እነዚህን ፡ ሥልጣንና ፡ ግዴታዎች ፡ በአንቀጽ ፡ ፳፬ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፤ አንቀጽ ፡ ፴፮ ፡ ብቻውን ፡ ደግሞ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ እነዚህን ፡ ሥልጣንና ፡ ግዴታዎች ፡ ይሰጡታል ፡ ተብሎ ፡ በክርክር ፡ ላይ ፡ ተነስቶ ፡ ነበር ፡ "የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ በሕግ ፡ አወጣጥ ፡ ረገድ ፡ የሚፈጽመው ፡ ተግባር ፡" ከክቡር ፡ አቶ ፡ ሥዩም ፡ ሐረጐት ፡ <u>በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት</u> ፡ ቮልዩም ፡ ፩ ፡ ቁጥር ፡ ፪ ፡ ገጽ ፡ ፪፻፹፩—፹፭ ፡ (፲፱፻፷፰ ፡ ዓ. ም.) ፤ ና ፡ "ስለ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሥልጣንና ፡ ሥራ ፡ የአስተዳደር ፡ ወኪሎች ፡ ሥልጣን ፡ መወሰን ፡" <u>በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት</u> ፡ ከክቡር ፡ አቶ ፡ አበራ ፡ ጀምበሬ ፤ ቮልዩም ፡ ፩ ፡ ቁጥር ፡ ፫ ፡ ገጽ ፡ ፩፳፩—፴፩ ፡ (፲፱፻፷፰ ፡ ዓ. ም.) ተመልከት ፡ አንቀጽ ፡ ፴፮ ፡ ብቻውን ፡ ሕግ ፡ ለማውጣት ፡ የሚያስችል ፡ ሥልጣንን ፡ አይሰጥም ፡ ብሎ ፡ ለመከራከር ፡ ይቻላል ፡፡

101. ስለሽፍቶች ፡ የወጣው ፡ ሕግ ፡ እንደ ፡ ኤርትራው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ልል ፡ (ሊበራል) ሆኖ ፡ አለመውጣቱ ፡ ያስደንቃል ፡፡ ስለሽፍቶች ፡ የወጣው ፡ ሕግ ፡ በግልፅ ፡ ከሚቃረነው ፡ ከተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፺፫ ፡ ና ፡ ፺፬ ፡ ለየት ፡ በማለት ፡ በኤርትራ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ እንደዚህ ፡ ዓይነቶች ፡ ግልፅ ፡ ድንጋጌዎች ፡ የሉም ፡፡ ቢሆንም ፡ ከፌዴራሉ ፡ ሕግ ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፯ ፡ የተወሰደው ፡ ያለ ፡ ሕግ ፡ የሚለው ፡ ፅንስ ፡ ሐሳብ ፡ በኤርትራው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፳፪ ፡ ላይ ፡ ተጨምሯል ፡፡

102. በግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፡ ተመልከት ፡፡

103. ትእዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፳፯ ፡ አንቀጽ ፡ ፯ ፡ ይህም ፡ "አስፈላጊ ፡ ሆነው ፡ እንዲሠራባቸው ፡ የሚያስፈልጉት ፡ ሁሉ ፡ ወደፊት ፡ በሚወጡ ፡ ሕጐች ፡ ተሰርዘው ፡ እስኪተኩ ፡ ድረስ ፡" መሆኑን ፡ አስብ ፡፡

104. አንድ ፡ ክስ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከመምጣቱ ፡ በፊት ፡ ሕጐችን ፡ የመሠረዝ ፡ ሃሳብ ፡ በእርግጥ ፡ ተቀዳሚ ፡ ግዴታ ፡ ብቻ ፡ መሆኑን ፡ ያመለክታል ፡፡

የተሰጠውን ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ ማንሳትና ፡ ፍ/ቤቱም ፡ አንድን ፡ ሕግ ፡ ሕገ ፡ መን ግሥታዊ ፡ ሆኖ ፡ አለማግኘቱ ፡ ትክክል ፡ ሥራ ፡ መሆኑን ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ማንሳት ፡ ምናልባት ፡ ያለቦታው ፡ ይሆናል ።[105]

ነገር ፡ ግን ፡ ፍ/ቤቶች ፡ ስለሱ ፡ ምን ፡ እንደሚሉ ፡ እንመለከት ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ከተጠቀሱት ፡ ክሶች ፡ መካከል ፡ ከነባሀታ ፡ ፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ በስተቀር ፡ ስለ ፡ አንድ ፡ ኤርትራ ፡ ሕግ ፡ አስፈላጊነት ፡ ይህንንም ፡ በቀዳሚነት ፡ የመወሰን ፡ ሥራ ፡ የማን ፡ እንደሆነ ፡ በክሱ ፡ ላይ ፡ የተነሳ ፡ ጭብጥ ፡ አልነበረም ። በእነባሀታ ፡ ፍርድ ፡ ጉዳይ፡ ስለሽፍቶች ፡ የወጣው ፡ ሕግ ፡ ለአስተዳደሩ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ እንዲሠራበት ፡ የሚ ያስፈልግ ፡ አይደለም ፡ በማለት ፡ የተከሳሾች ፡ ጠበቃ ፡ የተከራከረበትን ፡ ፍ/ቤቱ ፡ አንስቶት ፡ ነበር ። በቀጥታ ፡ በትእዛዝ ፡ በመግለጽ ፡ ፈንታ ፡ ፍ/ቤቱ ፡ ስለሽፍቶች ፡ የወጣው ፡ ሕግ ፡ አስፈላጊ ፡ ባለመሆኑ ፡ በተከለለ ፡ አኳኋን ፡ ሐሳቡን ፡ አሳውቋል ። የሕግ ፡ አውጪውን ፡ ወይም ፡ የሕግ ፡ አስፈጻሚውን ፡ ሥልጣን ፡ ያለአግባብ ፡ ተጠቅ መሃል ፡ በመባል ፡ እወቀሳለሁ ፡ ብሎ ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ መፍራት ፡ ያለምክንያት ፡ ነው ፡ ያሳሰበው ።[106]

ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ችግሩን ፡ የተመለከተው ፡ መጀመሪያ ፡ ኃላፊነቶችን ፡ በጠቅላላው ፡ በየመንግሥቱ ፡ ቅርንጫፎች ፡ መካከል ፡ ለመደልደል ፡ በመሞከር ፡ ነበር ። ፍ/ቤቱ ፡ "ለአስተዳደሩ ፡ ጥሩ ፡ አካሄድ ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ሕጎች ፡ ለሕግ ፡ አውጭ ዎቹ ፡ መርጦ ፡ ማቅረብ ፡ የሕግ ፡ አስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ ሃላፊነት ፡ ነው ፡" አለ ።[107]

ከዚህም ፡ በመቀጠል ፡ "ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ዓቃቤ ፡ ሕግ ፡ የሕግ ፡ አውጭውን ፡ ሥራ ፡ በመውሰድ ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ እሥራ ፡ ላይ ፡ መዋል ፡ አለበት ፡ ለማለት ፡ እንዴት ፡ ይቻላል?" በማለት ፡ የተጋነነ ፡ ጥያቄ ፡ ይዞ ፡ ቀረበ ። መልሱ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ነው ። "በኛ ፡ ሃሳብ ፡ ይችላሉ ፡ ብለን ፡ አንገምትም ፡" ቢሆንም ፡ ከሁለት ፡ ዓረፍተ ፡ ነገሮች ፡ በኋላ ፡ "የተከሳሾች ፡ ጠበቃ ፡ ስለ ፡ ሕጉ ፡ ያቀረበውን ፡ ክርክር ፡ ተቀብለነዋል ።" ሲል ፡ ፍ/ቤቱ ፡ ደምድሟል ። በእርግጥ ፡ ፍ/ቤቱ ፡ ያደረገው ፡ ራሱን ፡ በራሱ ፡ በፍ ጹም ፡ መገልበጥ ፡ (መለወጥ) ነበር ።[108]

የተከሳሹ ፡ ጠበቃ ፡ ክርክር ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ እንጂ ፡ ስለሽፍቶች የወ ጣውን ፡ ሕግ ፡ መጠቀም ፡ የለብንም ፡ በሚል ፡ ነበር ።[109] ፍ/ቤቱም አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡

---

105. ስለ ፡ "ፍርድ ፡ ምርመራ" (ጁዲሻል ፡ ሪቪው) ጂ. ፖውልና ፡ ሲ. ክለፐሃም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ እድገት ፡ የጽሑፍ ፡ መነሻ መጽሐፍ ፡ (ሶርስ ቡክ) ፡ በቀ. ኃ ፡ ሥ ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፷፯ ፡ ዓ. ም. ገጽ ፡ ፪፻፱—፪፻፵፯ ፡

106. ግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ቁ ፡ ፻፳ ፡ ተመልከት ፡

107. አስቀድሞ ፡ እንደተመለከተው ፡ የአቃቤ ፡ ሕግ ፡ ጽ/ቤት ፡ የተባለውን ፡ ዝርዝር ፡ አውጥቶ ፡ ነበር ። ሆኖም ፡ ለውስጥ ፡ አገልግሎት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

108. በሌላ ፡ አነጋገር ፡ ፍ/ቤቱ ፡ የትኞቹ ፡ ሕጎች ፡ አስፈላጊ ፡ እንደሆኑ ፡ ለመወሰን ፡ ሥልጣን ፡ የለውም ። እንደዚህ ፡ አድርጐ ፡ መናገሩ ፡ ምናልባት ፡ ሊያሳስት ፡ ይችላል ።

109. ዓቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ለተከሣሾች ፡ ጠበቃ ፡ ክርክር ፡ መልስ ፡ እንዲሰጥ ፡ ሲጠየቅ ፡ ሁለት ፡ የፍርድ ፡ ጉዳዮች ጠቅሷል ። አንደኛው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የወንጀል፡ ፋይል ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፷፰/፷፪ ፡ ከእነባሀታ ፡ የፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ ተመሳሳይ ፡ የሆነው ፡ ነበር ። በፋይል ፡ ቁ. ፫፻፷፰/፶፱ ፡ ስለሽፍቶች ፡ የወጣ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ክሶች ፡ ቀርበው ፡ የከፍተኛው ፡ ፍ/ቤት ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ተከሳሾቹ ፡ ጥፋተኞች ሆነው ፡ ስላገኛቸው ፡ የሰባት ፡ ዓመት ፡ እሥራት ፡ በይኖባቸዋል ። ቢሆ ንም ፡ የጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በይግባኝ ፡ የተከሰሱበትን ፡ ሕግ ፡ ወደ ፡ ወንጀለኛ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፭፻፴፪ ና ፡ ፭፻፴፪(፩) በመለወጥ ፡ ቅጣቱን ፡ ወደ ፡ አሥር ፡ ዓመት ፡ አርዝሞታል። በዓቃቤ ፡ ሕጉ ፡ የቀረበው ፡ መሪ ፡ ክስ ፡ በጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የተወሰነው ፡ ከአሥር፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ በእነመስፍን ፡ የፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ ነበር ።

ሕግ ፡ መወሰንና ፡ በአዋጅ ፡ ማጽደቅ ፡ የሕግ ፡ አውጭው ፡ ክፍል ፡ ሥራ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ጀምሮ ፡ ነበር ፤ ይህንንም ፡ ሲል ፡ ስለሽፍቶች ፡ የወጣው ፡ ሕግ ፡ የሚጸና ፡ ሕግ ፡ መሆኑና ፡ አለመሆኑን ፡ የሚወስነው ፡ የሕግ ፡ አውጭው ፡ ክፍል ፡ ነው ፡ ማለቱ ፡ ነው ። ፍ/ቤቱ ፡ ከዚህም ፡ አልፎ ፡ ፍ/ቤት ፡ የሕግ ፡ አውጭውን ፡ የራሱን ፡ ሥራ ፡ በመውሰድ ፡ ይህን ፡ ሕግ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ መዋል ፡ አለበት ፡ ለማለት ፡ ይችላል ፡ ወይ? የሚለውን ፡ የራሱን ፡ ጥያቄ ፡ ወዲያውኑ ፡ በአሉታ ፡ (በተቃራኒ) መልሶታል ። በዚህ፡ ላይ ፡ ለማተኮር ፡ መልሱን ፡ ከበታች ፡ አስምሮበታል ። ሊገባ ፡ በሚችል ፡ ከባድ ፡ ወጥመድ ፡ በሃሣብና ፡ በግብር ፡ በሚውል ፡ ቀንዶች ፡ መካከል ፡ ስለተያዘ ፡ ፍ/ቤቱ ፡ በአጭሩ ፡ በሃሳቡ ፡ መግባት ፡ የለብኝም ፡ ብሎ ፡ ወዳሰበው ፡ ነው ፡ እንዳይገባ ፡ ያደረገው ። በሕግ ፡ አውጭው ፡ ቦታ ፡ በመሆን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫው ፡ ሕግ ፡ እንጂ ፡ ስለሽፍቶች ፡ የወጣ ፡ ሕግ ፡ ጥቅም ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዳይውል ፡ ወሰነ ።

ትዕዛዝ ፡ ቁ. ፳፯ ፡ ጵኑ ፡ ሕግ ፡ ከሆነ ፡ ወዲህ ፡ ስለሽፍቶች ፡ የወጣው ፡ ሕግ ፡ አስፈላጊ ፡ ሕግ ፡ መሆኑና ፡ አለመሆኑ ፡ በሕግ ፡ አውጪው ፡ መደረግ ፡ እንዳለበት ፡ ተወስኖ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ይህ ፡ ጥያቄ ፡ የፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ማስተዋል ፡ እስከዚህም ፡ በጣም ፡ ባልሳበ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ፍ/ቤቱ ፡ የሕግ ፡ አውጭውን ፡ ሥራ ፡ የመውሰድ ፡ ችግር ፡ በገጠመው ፡ በእንደዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ሁኔታ ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ ይኖርበታል? ፍ/ቤት ፡ ራሱን ፡ በመጥፎ ፡ ሁኔታ ፡ ገምቶ ፡ የሚያገኘው ፡ እንደዚህ ፡ ፍ/ቤቶች፡ ያለማቋረጥ ፡ ሲጐተቱ ፡ ሲያገኘው ፡ ነው ።

ከዚህም ፡ በላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሕግ ፡ አውጭዎች ፡ አለመሆናቸውን ፡ ለመስማት ፡ የፈጠኑ ፡ ናቸው ። ቢሆንም ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ከሚሉት ፡ ውጭ ፡ ለማድረግ ፡ ይገደዳሉ ። በብዙ ፡ በፊታችን ፡ ያለው ፡ ጥሩ ፡ ምሳሌ ፡ እንደሚሆነው ፡ ፍ/ቤቱ ፡ እንደ ፡ ሕግ ፡ አውጭ ፡ ከመሥራት ፡ ሌላ ፡ ምርጫ ፡ የለውም ። በየትኛውም ፡ መንገድ ፡ ቢወጣ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ፍ/ቤት ፡ እንደ ፡ ሕግ ፡ አውጭ ፡ መሥራት ፡ ይኖርበታል ።

በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግም ፡ ሆነ ፡ ስለሽፍቶች ፡ በወጣው ፡ ሕግ ፡ በመሠረቱ ፡ ውሳኔው ፡ መደረግ ፡ የነበረበት ፡ በሕግ ፡ አውጭው ፡ ክፍል ፡ ነበር ። እውነተኛው ፡ ጭብጥ ፡ ስለሽፍቶች ፡ የወጣ ፡ ሕግ ፡ በትእዛዝ ፡ ፳፯ ፡ መሠረት ፡ ሕግ ፡ መሆኑ ፡ ወይም ፡ አለመሆኑ ፡ እንዲሁም ፡ ይህ ፡ በተቀዳሚ ፡ የሕግ ፡ ማውጣት ፡ ተግባር ፡ ነው ።[110]

የሥራ ፡ መከፋፈል ፡ በመንግሥትና ፡ ሕዝብ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ግንኙነት ፡ በሚመሳሰለው ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ መሪ ፡ አስተሳሰብ ፡ ነው ። የተለያዩ ፡ የመንግሥት ፡ ክፍሎች ፡ የተለያዩ ፡ ተግባሮች ፡ እንዲያከናውኑ ፡ ስለተደለደሉ ፡ በጠቅላላው ፡ አነጋገር ፡ አንዱ ፡ ክፍል ፡ የሌላውን ፡ ክፍል ፡ ሥራ ፡ መጠቀም ፡ የለበትም ። ቢሆንም ፡ የመንግሥት ፡ ቅርንጫፎች ፡ እንደታሸጉ ፡ አካሎች ፡ መቁጠር ፡ ያልተለመደና ፡ ያላዋቂነት ፡ ያሰኛል ። ሲያስፈልግ ፡ እርስ ፡ በእርሳቸው ፡ መተባበር ፡ ይኖርባቸዋል ።[111] በተዘዋዋሪ ፡ መንገድ ፡ የፍርድ ፡ ቤቶችም ፡ በሕግ ፡ አሠራር ፡ ተግባር ፡ ጣልቃ ፡ መግባት ፡ የማይቀር ፡ ነው ። ይህንን ፡ የሚያደርጉት ፡ ያለማቋረጥ ፡ በመተርጐም ፡ የጐደለውን ፡ ሕግ ፡ በማሟላትና ፡ የትኛው ፡ ሕግ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ መዋል ፡

110. ከላይ ፡ ግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ቁ ፡ ፻፱ ፡ እንደተመለከተው ፡ ያው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለሽፍቶች ፡ ስላወጣው ፡ ሕግ ፡ የተለየ ፡ ውሳኔ ፡ ሰጥቶ ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ማድረግ ፡ ያለባቸው፡ ሌሎች ፡ የተለያዩ ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችና ፡ ብዙ ፡ ሕጐችን ፡ ብንመለከት ፡ ለምን ፡ ይህ ፡ የሕግ ፡ አውጭዎች ፡ ሥራ ፡ እንደሆነ ፡ ተመልከት ።

111. ክቡር ፡ አቶ ፡ ሥዩም ፡ ሐረጐት ፡ ተመሳሳይ ፡ የሐሳብ ፡ ነጥብ ፡ አድርገዋል ። ከላይ ፡ ግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ቁ ፡ ፯ ተመልከት ።

እንዳለበት ፡ በመወሰን ፡ ነው ። ይህ ፡ የሕግ ፡ አሠራር ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ መመደብ ፡ የቃላት ፡ አጠቃቀም ፡ ክርክር ፡ ብቻ ፡ ነው ። ይህም ፡ ፍ/ቤቶች ፡ የሕግ ፡ ማውጣቱን ፡ ሥራ ፡ እንዲሻሙ ፡ ወይም ፡ ሕግ ፡ አውጭውን ፡ ለመቅደም ፡ እንዲሞክሩ ፡ ይጋብዛ ቸዋል ፡ ተብሎ ፡ መታሰብ ፡ የለበትም ። ፍ/ቤቶች ፡ ከዚህ ፡ ራቅ ፡ ብለው ፡ በፊታቸው፡ በቀረበላቸው ፡ ልዩ ፡ በሆኑ ፡ ክሶች ፡ ላይ ፡ ያተኩራሉ ፡ እንጂ ፡ የሕብረተሰቡን ፡ የች ግር ፡ መስኮች ፡ ሄደው ፡ አይመለከቱም ። በሌላ ፡ በኩል ፡ በነባህታ ፡ ፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ እንዳደረጉት ፡ ሁሉ ፡ ፍ/ቤቶች ፡ ለነሱ ፡ በደንብ ፡ ያልተሰጠውን ፡ ሥልጣን ፡ መጠቀማቸውንና ፡ ከዳኝነት ፡ ሥልጣናቸውም ፡ ውጭ ፡ መውጣታቸውን ፡ የሚያመ ለክት ፡ ሃሳብ ፡ መስጠት ፡ የለባቸውም ። ለጊዜው ፡ እንደ ፡ ሕግ ፡ አውጭ ፡ ሆኖ ፡ ከመ ሥራትና ፡ ስለሽፍቶች ፡ የወጣውን ፡ ሕግ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ይውል ፡ ወይም ፡ አይውል ፡ እንደሆነ ፡ ከመወሰን ፡ በስተቀር ፡ ሊሠራበት ፡ የሚቻል ፡ ሌላ ፡ አማራጭ ፡ የለም ።

የሕግ ፡ አውጭው ፡ ክፍል ፡ በአንዳንድ ፡ ምክንያት ፡ ይህን ፡ ዓይነቱን ፡ የሕግ ፡ ማውጣት ፡ ሥራውን ፡ ማካሄድ ፡ ከተሳነው ፡ ፍ/ቤቶች ፡ የሱን ፡ ሥራ ፡ ለመውሰድ ፡ ይገደዳሉ ። ሕግ ፡ አውጭው ፡ ላልተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ውሳኔ ፡ እስኪሰጥ ፡ ድረስ ፡ እንዲጠ በቅ ፡ የሚያስችሉና ፡ ፍ/ቤቶች ፡ በተቻላቸው ፡ መጠን ፡ ውሳኔ ፡ መስጠት ፡ የሚኖር ባቸው ፡ ችግሮች ፡ ይነሳሉ ። በአሁኑ ፡ ሁኔታዎች ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙ ፡ ፍ/ቤቶች ፡ በነባህታ ፡ ፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ተነስተው ፡ እንደነበሩት ፡ ያሉ ፡ ሕጋዊ ፡ ችግሮችን ፡ ሊያስወግዱ ፡ አይችሉም ። መፍትሔ ፡ ያልተገኘለት ፡ የኤርትራ ፡ ሕግ ፡ ችግር ፡ መሠረትዊ ፡ ለውጥ ፡ እስከአልተደረገለት ፡ ድረስ ፡ ፍ/ቤቶች ፡ በተለዩ ፡ ክሶች፡ በተጠየቁ ፡ ጊዜ ፡ በትእዛዝ ፡ ፳፯ና ፡ በጠቅላላው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ በኩል ፡ በአ ንድ ፡ ሕግ ፡ "አስፈላጊነት" ላይ ፡ የተነሳውን ፡ ችግር ፡ ባለማቋረጥ ፡ መጋተር ፡ ይኖ ርባቸዋል ። ፍ/ቤቶች ፡ ሥርዓት ፡ በሌለው ፡ ሁኔታ ፡ ችግሮችን ፡ (እንደተሳሉ) መመ ልከትና ፡ አንድ ፡ ውሳኔ ፡ በተመሳሳይ ፡ ክሶች ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ውጤት ፡ ሳያውቁ ፡ ለያይቶ ፡ ማየት ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ ውጤት ፡ ሊያመጣ ፡ የሚችል ፡ ወይም ፡ ይበልጥ ፡ ተፈ ላጊ ፡ አይሆንም ። በሕጉ ፡ ላይ ፡ ባለመጠራጠርም ፡ ሆነ ፡ በመዘበራረቅ ፡ በኩል ፡ ችግር ፡ አለ ። የማያስፈልግ ፡ ጊዜና ፡ ኃይልን ፡ በሱ ፡ ላይ ፡ ማጥፋት ፡ ውድ ፡ አድርጎ ታል ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ በአንድ ፡ ጊዜ ፡ ለሁሉም ፡ ችግር ፡ መፍትሔ ፡ የመፈለግ ፡ አስፈላጊ ፡ ዘዴ ፡ አለ ።

## መደምደሚያ ።

የኤርትራን ፡ ሕግ ፡ ለማስተካከልና ፡ የተሟላ ፡ ጥልቅ ፡ ምርምር ፡ ለማድረግ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አልፎበታል ። የፌዴራሉ ፡ አስተዳደር ፡ ከተፈጸመ ፡ ከአሥር ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ የእንግሊዝ ፡ አስተዳደር ፡ ከቀረ ፡ ከሀያ ፡ ዓመት ፡ በኋላና ፡ የጣልያን ፡ ሥል ጣን ፡ ከአበቃ ፡ ከሰላሳ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ አንድም ፡ በቅኝ ፡ ጊዜ ፡ የነበረውን ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ሕግ ፡ እንዲቀጥል ፡ ማድረግና ፡ እሱም ፡ ካገሪቱ ፡ ሕግ ፡ ክፍል ፡ መሆኑና ፡ አለ መሆኑን ፡ አለማወቅ ፡ የማያስፈልግ ፡ ይመስላል ። ይህ ፡ የሕግ ፡ መዘበራረቅ ፡ መጣ ራት ፡ ያለበት ፡ አሁን ፡ ነው ። ትእዛዝ ፡ ቁ. ፳፯ ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ የሚሰጠው ፡ ጊዜ ያዊ ፡ መተኪያ ፡ መልስ ፡ ነው ። የማያስፈልጉ ፡ ውዝግቦችን ፡ ሳያስከትል ፡ ዘላቂ ፡ መፍትሔ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

ጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በነባህታ ፡ ፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ "ለአስተ ዳደር ፡ ሥራ ፡ ያስፈልጋሉ ፡ የሚባሉ ፡ ሕጎችን ፡ ጠቁሞ ፡ ለሕግ ፡ አውጭው ፡ ማቅ ረብ ፡ የሕግ ፡ አስፈጻሚ ፡ ክፍል ፡ ተግባር ፡ ነው ።" በማለት ፡ ትክክለኛውን ፡ መን

ገድ ፡ አመልክቷል ። ቀላል ፡ ሥራ ፡ ባይሆንም ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። የተመሰቃ
ቀለውን ፡ የኤርትራን ፡ ሕግ ፡ ወደ ፡ ተጠናቀረው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ሥርዓት ፡(ኮዲ
ፋይድ ፡ ሲስተም) ገብቶ ፡ ደንበኛ ፡ ቦታውን ፡ እንዲይዝ ፡ ለማድረግ ፡ የልብ ፡ ጥረት ፡
መደረግ ፡ አለበት ። በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ሕጐችን ፡ ሁሉ ፡ በሰፊው ፡
በመመርመርና ፡ ባንድነት ፡ በማቀነባበር ፡ የተገኘው ፡ ልምድ ፡ ምናልባት ፡ ለአንዳ
ንድ ፡ እቅድ ፡ ሊያገለግል ፡ ይችላል ።

የኤርትራን ፡ የሕግ ፡ ሁናቴ ፡ ለማስተካከል ፡ ብዙ ፡ እርምጃዎች ፡ መወሰድ ፡
አለባቸው ። በመጀመሪያ ፡ በግልጽ ፡ ያልተሻሩ ፡ ሕጐች ፡ በሞላ ፡ ተሰብስበው ፡ ወደ
አማርኛና ፡ ወደ ፡ እንግሊዝኛ ፡ መተርጐም ፡ አለባቸው ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ እርስ ፡ በር
ሳቸውና ፡ በጠቅላላው ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ሕጐች ፡ ጋር ፡ መጠቃለል ፡ (መስማማት ፡)
አለባቸው ። የማያስፈልጉ ፡ እንደ ፡ ጣሊያን ፡ ሊሬና ፡ የምሥራቅ ፡ አፍሪካ ፡ ሽልንግ ፡
ወይም ፡ የጣሊያን ፡ የሕግ ፡ አርዕስቶች ፡ የመሳሰሉት ፡ ጥቅሶች ፡ ተሰርዘው ፡ በትክ
ክል ፡ መተካት ፡ አለባቸው ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ ዋናው ፡ ጠቃሚ ፡ የሆነው ፡ ሕገ ፡ መን
ግሥታዊ ፡ ያልሆኑ ፡ ሕጐች ፡ ወይም ፡ ጊዜያዊ ፡ አስፈላጊነታቸው ፡ የቀረ ፡ ሕጐችን ፡ መሰ
ረዝ ፡ ነው ። እነዚህን ፡ ሕጐች ፡ እስራ ፡ ላይ ፡ ማዋል ፡ ለአገሪቱ ፡ የማይጠቅሙና ፡
አንዳንድ ፡ የማይፈለጉ ፡ የሕጉን ፡ ዘይቤ ፡ ለምን ፡ እንደወጣ ፡ የሚያመራምሩ ፡ ጥያቄ
ዎች ፡ ከማስነሳት ፡ በቀር ፡ የሚሰጡት ፡ ጥቅም ፡ ጥቂት ፡ ስለሚሆን ፡ ሕጐቹን ፡ ለማሻሻል ፡
ጊዜው ፡ አሁን ፡ ነው ። የተጠቃለሉትና ፡ ዘመናዊ ፡ የሆኑ ፡ የሕግ ፡ ረቂቆች ፡ ሕግን ፡
አፅድቀው ፡ በአዋጅ ፡ በሚያወጡ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ተለይተው ፡ መከፋፈል ፡ አለባ
ቸው ። የፓርላማ ፡ መቀበልና ፡ ወይም ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ፊርማ ፡ የሚያስፈልጋ
ቸው ፡ ሕጐች ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ መንገድ ፡ መሠራት ፡ አለባቸው ። ሌሎቹ ፡ የሚኒስ
ቴር ፡ የጠቅላይ ፡ ግዛትና ፡ የማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ፡ ጠባይ ፡ ያላቸው ፡ ሕጐች ፡
በደንብ ፡ መከፋፈል ፡ አለባቸው ።[112]

አንዳንድ ፡ የማያስፈልግ ፡ የሥራ ፡ ዕቅድ ፡ (ፕሮጄክት ፡) ጉዳዩን ፡ በሚመለከታ
ቸው ፡ ባለሥልጣኖች ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ከተጀመረ ፡ ሥራውን ፡ ለመፈጸም ፡ ምንም ፡
እክል ፡ ሊያጋጥም ፡ አይችልም ። የሥራው ፡ መሪ ፡ ውሳኔን ፡ የሚጠቅስ ፡ ከመሆኑ ፡
ይልቅ ፡ ቴክኒካል ፡ መሆኑ ፡ ስለሚበልጥ ፡ ጉዳዩ ፡ ከሚመለከታቸው ፡ መንግሥታዊ ፡
ድርጅቶች ፡ (ኢንስቲትዩቶች) የተማሩ ፡ የሕግ ፡ አዋቂዎች ፡ የአማካሪ ፡ ኮሚሽን ፡
መሾም ፡ የሥራውን ፡ ጥራት ፡ በእርግጥ ፡ ያስተማምነዋል ። በ፲፱፻፷፪ ፡ ዓ. ም. የዚህ ፡
ዓይነት ፡ መንገድ ፡ (ዘዴ) ተወስዶ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ስለሽፍቶች ፡ የወጣው ፡ ሕግ ፡ ቀዋ
ሚነት ፡(ጽኑነት ፡) ወይም ፡ በነባህታ ፡ ፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ የተነሱ ፡ የሕግ ፡ ጭብጦች ፡
ወይም ፡ በሰብሳ ፡ ፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ ብስጭት ፡ የመላበት ፡ የአነስተኛው ፡ ድምፅ ፡ የፍ
ርድ ፡ አስተያየት ፡ ወይም ፡ ይህ ፡ የመጀመሪያ ፡ የጽሑፍ ፡ ትችት ፡ አስፈላጊ ፡ ባል
ሆነ ፡ ነበር ። የኤርትራ ፡ ሕግጋት ፡ እንቆቅልሽ ፡ መስተካከል ፡ ሰፊ ፡ ጥናት ፡ የተደረ
ገበት ፡ የሕግ ፡ ሥርዓት ፡ እንዲኖር ፡ መፍትሔ ፡ እንዲገኝለት ፡ ያሳስባል ። ትግሉ ፡
አሁንም ፡ እንዳለ ፡ ነው !

---

112. ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ ባገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ የማዘጋጃ ፡ ቤቶች ፡ ክፍ
ልና ፡ የኤርትራ ፡ የማዘጋጃ ፡ ቤቶች ፡ ክፍል ፡ አብረው ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የፓብሊክ ፡
አድሚኒስትሬሽን ፡ ኢንስቲቱት ፡ ጋር ፡ በመተባበር ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤቶችን ፡ ስለሚመለከቱ ፡ የፓርት
ራን ፡ ሕጎች ፡ ችግሮች ፡ ለማቃለል ፡ በመሥራት ፡ ላይ ፡ ናቸው ። ይህ ፡ ጥሩ ፡ እርምጃ ፡ ነው ። ዳሩ ፡
ግን ፡ ይህ ፡ ሥራ ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ የማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ ጠባይ ፡ በሌላቸው ፡ የሕግ ፡ ክፍሎች ፡ ምን ፡
ዓይነት ፡ ለውጥ ፡ እንደሚያመጣ ፡ አይታወቅም ።

## ኢ. አ. ኢ. በ፲፱፻፶፯ ፡ ስለሽፍቶች የወጣ ሕግ ፡ (ከነማሻሻያዎቹ ፡)

(የኤርትራ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ነሐሴ ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ የተቀበለውና ፡ የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ እን ደራሴ ፡ መስከረም ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ያጸደቁት ፡ ሕግ ፡)

አሁን ፡ ጸንቶ ፡ በሚሠራበት ፡ ሕግ ፡ በደንብ ፡ የተደራጁ ፡ ሽፍቶችና ፡ ቀማኞችን ፡ ለመከላከልና ፡ ለማ ጥፋት ፡ ሳላልተቻለ ፤

ቅጣቱ ፡ እንዲከብድና ፡ የአጥፊዎች ፡ መንደሮችም ፡ የወል ፡ ቅጣት ፡ እንዲደርስባቸው ፡ ማድረግ ፡ ሽፍ ቶቹንና ፡ ቀማኞቹን ፡ የሚያጠፉ ፡ መስሎ ፡ ስለታየ ፤

ቀጥሎ ፡ የተመለከተው ፡ ሕግ ፡ ወጥቶአል ፤

### አርእስትና ፡ ሕጉ ፡ የሚጸናበት ፡ ጊዜ ፡

፩. ይህ ፡ ሕግ ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፶፰ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ በ፲፱፻፶፯ ፡ ስለሽፍቶች ፡ የወጣ ፡ ሕግ ፡ ተብሎ ፡ ሊጠቀስ ፡ ይቻላል ፤ ከጸደቀበት ፡ ወይም ፡ እንደነገሩ ፡ ሁናቴ ፡ ታትሞ ፡ ከወጣበት ፡ ቀን፡ ጀምሮ ፡ የጸና ፡ ይሆናል ።

### የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ስለያዙ ፡ ሽፍቶች ፡

፪. ሁለት ፡ ወይም ፡ ከዚያ ፡ የበለጡ ፡ ሰዎች ፡ የጋራ ፡ ዓላማቸው ፡ ማናቸውንም ፡ የኃይል ፡ ወንጀል ፡ ሥራ ፡ ለመፈጸም ፡ ከሆነና ፡ ቢያንስ ፡ ቢያንስም ፡ አንዳቸው ፡ ጠብመንጃ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ፈንጂ ፡ መሣሪያ ፡ ከያዘ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ቅጣቱን ፡ የሚያቃልልበት ፡ በጣም ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ ምክንያት ፡ ካላገኘ ፡ በቀር ፡ እያንዳ ንዳቸው ፡ በአምስት ፡ ዓመት ፡ በማያንስ ፡ እሥራት ፡ ይቀጣሉ ።

### አንደኛ ፡ የቅጣት ፡ ማክበጃ ፡

፫. በአንቀጽ ፡ ሁለት ፡ የተመለከተውን ፡ ወንጀል ፡ በመፈጸም ፡ ጥፋተኛ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘው ፡ ማንኛ ውም ፡ ሰው ፡ ከአሥር ፡ ዓመት ፡ በማያንስ ፡ እሥራት ፡ የሚቀጣው ፡ የሽፍቶች ፡ አባል ፡ ሆኖ ፡ ከምግብ ፡ ዝር ፊያ ፡ ሌላ ፡ ኃይልን ፡ በመጨመር ፡ ማናቸውንም ፡ ወንጀል ፡ ፈጽሞ ፡ በተገኘ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

### ሁለተኛ ፡ የቅጣት ፡ ማክበጃ ፡

፬. በአንቀጽ ፡ ፪ ፡ የተመለከተውን ፡ ወንጀል ፡ በመፈጸም ፡ ጥፋተኛ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘው ፡ ማንኛውም ሰው ፡ በአሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ በማያንስ ፡ እሥራት ፡ የሚቀጣው ፤

(፩) የሽፍቶች ፡ አባል ፡ ሆኖ ፡ ከምግብ ፡ ዝርፊያ ፡ ሌላ ፡ ሁለት ፡ የኃይል ፡ ወንጀሎችን ፡ መፈጸሙ ፡ የተረጋገጠበት ፡ እንደሆነ ፡ ወይም

(፪) የኃይል ፡ ወንጀሉ ፡ ከመፈጸሙ ፡ በፊት ፡ ጥቂት ፡ አስቀድሞ ፡ ሆነ ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ከሽፍ ቶቹ ፡ አንዱ ፡ ጠብመንጃ ፡ የተኰሰ ፡ ወይም ፡ ፈንጂ ፡ መሣሪያ ፡ ያፈነዳ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ።

### ሦስተኛ ፡ የቅጣት ፡ ማክበጃ ፡

፭. በአንቀጽ ፡ ፪ ፡ የተመለከተውን ፡ ወንጀል ፡ በመፈጸም ፡ ጥፋተኛ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘው ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በሞት ፡ የሚቀጣው ፤

(፩) አስቀድሞ ፡ በቁጥር ፡ ፺፬/፲፱፻፶፩ በወጣው ፡ አዋጅ ፡ አንቀጽ ፡ ፰ ፡ በቁጥር ፡ ፩/፲፱፻፶፭ ፡ በወጣው ፡ አዋጅ ፡ አንቀጽ ፡ ፩ ፡ ወይም ፡ በዚሁ ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፪ ፡ የተመለከተውን ፡ ሕግ ፡ በመተላለፍ ፡ ጥፋተኛ ፡ ሆኖ ፡ ተገኝቶ ፡ ተፈርዶበት ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ ጠቅላላ ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ በሆነ ፡ የምህ ረት ፡ አዋጅ ፡ ምክንያት ፡ እጁን ፡ በመስጠቱ ፡ ከመከሰስ ፡ የዳነ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፤

(፪) የሽፍቶች ፡ አባል ፡ ሆኖ ፡ ከምግብ ፡ ዝርፊያ ፡ ሌላ ፡ ከሁለት ፡ ጊዜ ፡ በላይ ፡ የኃይል ፡ ወንጀሎ ችን ፡ የፈጸመ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፤

(፫) ማናቸውም ፡ የኃይል ፡ ወንጀል ፡ በሚፈጸምበት ፡ ጊዜ ፡ ከሽፍቶቹ ፡ አንዱ ፡ ጠብመንጃ ፡ የተኰሰ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ፈንጅ ፡ መሣሪያ ፡ ያፈነዳ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ ተኩሶ ፡ ከኃይል ፡ ወንጀል ፡ አንዱ ፡ ክፍል ፡ ከሆነ ፡ ወይም ፡ የተባለው ፡ የኃይል ፡ ወንጀል ፡ በቶክስ ፡ ብቻ ፡ ሲፈጸም ፡ ነው ።

(በ፲፱፻፳፩ ፡ የወጣውን ፡ የሽፍቶች ፡ ሕግ ፡ ማሻሻያ ፡ መመልከት ፡ ነው ፡)

<u>ውርስ ፡</u>

፰. —ሀ—(፩) በዚሁ ፡ አዋጅ ፡ አንቀጽ ፡ ፪ ፡ የተመለከተውን ፡ ሕግ ፡ በመተላለፍ ፡ ወንጀል ፡ በምሥራት ፡ ላይ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ የተጠረጠረ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ እንዲቀርብ ፡ ለማስገደድ ፡ ዓቃቤ ፡ ሕጉ ፡ በሚያቀርበው ፡ ጥያቄ ፡ መሠረት ፡ አንድ ዳኛ (ማጂስትሬት ፡) የተጠርጣሪውን ፡ ሰው ፡ ተንቀሳቃሽ ንብረት ፡ በሙሉ ፡ ከሌሎች ፡ ጋር ፡ የሚካፈለውንም ፡ ድርሻ ፡ ጭምር ፡ እንዲከበር ፡ ለማዘዝ ፡ ሥልጣን ይኖረዋል ፡ ትእዛዙንም ፡ የሚያስፈጽመው ፡ ፖሊስ ፡ ነው ።

(፪) ንብረቱ ፡ እንዲከበር ፡ ማመልከቻ ፡ ከመቅረቡ ፡ በፊት ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ አስቀድሞ ፡ በተጠርጣሪው ፡ ሰው ፡ ይዞታ ፡ የነበረው ፡ ማናቸውም ፡ ሀብት ፡ ለዳኛው ፡ አፍራሽ ፡ ማስረጃ ፡ ካልቀረበለት በስተቀር ፡ የተጠርጣሪው ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡ እንደሆነ ፡ ይገመታል ።

(፫) ንብረት ፡ በተከበረ ፡ በአንድ ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ተጠርጣሪው ፡ ሰውዬ ፡ እጁን ፡ ካልሰጠ ፡ ወይም ፡ ካልተያዘ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ሳይቀርብ ፡ የቀረው ፡ በቂ ፡ በሆነ ፡ ምክንያት ፡ መሆኑን ፡ ለዳኛው ፡ ማስረጃ ፡ ካልቀረበለት ፡ ዳኛው ፡ የተከበረውን ፡ ንብረት ፡ በውርስ ፡ ስም ፡ ለመንግሥት ፡ ገቢ ፡ እንዲሆን ፡ ማዘዝ ፡ አለበት ።

(፬) ተጠርጣሪው ፡ ሰው ፡ ንብረቱ ፡ በተከበረ ፡ በአንድ ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ እጁን ፡ ከሰጠ ፡ ወይም ፡ ከተያዘ ፡ ግን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጥፋተኛነቱን ፡ እስኪያረጋግጥ ፡ ወይም ፡ በነፃ ፡ እስኪለቀው ፡ ወይም ፡ እስኪያሰናብተው ፡ ድረስና ፡ ማናቸውም ፡ ይግባኝ ፡ ውሳኔ ፡ እስኪያገኝ ፡ ድረስ ፡ ዳኛው ፡ የጀመረውን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ያቋርጣል ።

(፭) በ፲፱፻፶፱ ፡ የወጣው ፡ የሽፍቶች ፡ አዋጅ ፡ ማሻሻያ ፡ እሥራ ፡ ላይ ፡ ከዋለ ፡ በኋላ ፡ በዚሁ ፡ አዋጅ ፡ አንቀጽ ፡ ፪ ፡ የተመለከተውን ፡ ሕግ ፡ ተላልፎአል ፡ በማለት ፡ ተከሶ ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ የሚገኘው ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ንብረቱ ፡ ይጠፋል ፡ የሚል ፡ ሥጋት ፡ መኖሩን ፡ ለማመን ፡ ዳኛው ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ካገኘ ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ (፪) እና ፡ (፬) በተመለከተው ፡ ዓይነት ፡ ንብረቱ ፡ እንዲከበር ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

(፮) ተጠርጣሪው ፡ ሰው ፡ በነፃ ፡ የተለቀቀ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ያሰናበተው ፡ እንደሆነ ፡ የተከበረው ፡ ንብረት ፡ ይመለስለታል ፡ ጥፋተኛነቱ ፡ የተረጋገጠ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከፈረደበት ፡ በማናቸውም ፡ ቅጣት ፡ ሌላ ፡ ዳኛው ፡ በተጨማሪ ፡ የተከበረው ፡ ንብረት ፡ በሙሉ ፡ ለመንግሥት ፡ ውርስ ፡ ሆኖ ፡ እንዲገባ ፡ ይወስንበታል ።

(፯) አንድ ፡ ዳኛ ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ መሠረት ፡ በሚሰጠው ፡ ማናቸውም ፡ ትእዛዝ ፡ ላይ ፡ ይግባኝ ፡ የሚቀርበው ፡ ለጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ።

(፰) በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ንዑስ ፡ ክፍል (፫) ወይም (፮) በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ንብረቱ ፡ እንዲወረስ ፡ የተፈረደበት ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ንብረቱ ፡ የተወረሰበት ፡ በማይገባ ፡ መሆኑን ፡ አስረድቶ ፡ እንዲመለስለት ፡ በጠየቀ ፡ ጊዜ ፡ መንግሥት ፡ ንብረቱን ፡ የመመለስ ፡ ግዴታ ፡ አለበት ።

(በ፲፱፻፶፱ ፡ የወጣውን ፡ የሽፍቶች ፡ ሕግ ፡ ማሻሻያ ፡ መመልከት ፡ ነው ፡)

፰. —ለ—(፩) ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በዚህ ፡ አዋጅ ፡ አንቀጽ ፡ ፲(፪) ፡ የተመለከተውን ፡ ሕግ ፡ ተላልፎ ፡ ወንጀል ፡ ሠርቶአል ፡ ተብሎ ፡ የተጠረጠረ ፡ እንደሆነ ፡ ፖሊስ ፡ የአባቱን ፡ የወንድሞቹን ፡ የአጐቶቹን ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረትና ፡ ከተጠርጣሪው ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ የጋራ ፡ ንብረት ፡ አለው ፡ የተባለ ፡ እንደሆነም ፡ የእማቹ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረት ፡ ጭምር ፡ ይይዛል ።

(፪) ንብረቱ ፡ በተያዘ ፡ በአንድ ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ተጠርጣሪው ፡ ሰው ፡ እጁን ፡ ከሰጠ ፡ ወይም ፡ ከተያዘ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ከሞተ ፡ የተያዘው ፡ ንብረት ፡ ይመለሳል ፡ በተረፈ ፡ ዳኛው ፡ ንብረቱ ፡ ለመንግሥት ፡ ውርስ ፡ ሆኖ ፡ እንዲገባ ፡ ማዘዝ ፡ አለበት ።

(በ፲፱፻፳፩ ፡ የወጣውን ፡ የሽፍቶች ፡ ሕግ ፡ ማሻሻያን ፡ መመልከት ፡ ነው ፡)

<u>ሽፍቶችን ፡ ስለማነሣሣትና ፡ ማበረታታት ፡</u>

፱. ማንኛውም ፡ ሰው ፡ የሽፍቶች ፡ አባል ፡ ሳይሆን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በአንቀጽ ፡ ፪ ፡ በዝርዝር ፡ እንደተመለከተው ፡ ያሉትን ፡ ሽፍቶች ፡ ያነሣሣ ፡ ወይም ፡ ያደራጀ ፡ እንደሆን ፡ ከ፭ ፡ ዓመት ፡ በማያንስ ፡ እሥራት ፡ ይቀጣል ።

ሽፍቶችን ስለመርዳት ፡

፯. ማንም ፡ ሰው ፡ በአንቀጽ ፡ ፪ ፡ እንደተመለከተው ፡ ያሉትን ፡ ሽፍቶች ፡ ወይም ፡ ከነርሱ ፡ አንዱን ፡ የደበቀ ፡ ወይም ፡ የረዳ ፡ እንደሆነ ፡ ከአሥር ፡ ዓመት ፡ በማያንስ ፡ እሥራት ፡ ይቀጣል ።

ሽሺውን ስለመርዳት ፡

፰. በአንቀጽ ፡ ፪ ፡ እንደተመለከተው ፡ ያሉትን ፡ ሽፍቶች ፡ አባል ፡ መኖሩንና ፡ ከቅጣት ፡ ለመዳን ፡ መሸሹን ፡ ለማመን ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ እያለው ፡ ሽሺውን ፡ ሰው ፡ የደበቀ ፡ ወይም ፡ የረዳ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ከአምስት ፡ ዓመት ፡ በማያንስ ፡ እሥራት ፡ ይቀጣል ።

ለባለሥልጣኖች ስላለማስታወቅ ፡

፱. (፩) ማንም ፡ ሰው ፡ በአንቀጽ ፡ ፪ ፡ እንደተመለከተው ፡ ያሉት ፡ ሽፍቶች ፡ መኖራቸውን ፡ ሥራቸውን ፡ ያቀዱዋቸውን ፡ ሐሳቦች ፡ ወይም ፡ ያሉበትን ፡ ሥፍራ ፡ እያወቀ ፡ ወይም ፡ የእነዚህ ፡ ሽፍቶች ፡ አባል ፡ ነው ፡ ወይም ፡ ከነርሱ ጋር ፡ ለመቀላቀል ፡ ሐሳብ ፡ አለው ፡ ብሎ ፡ የሚጠረጥረው ፡ ሰው ፡ መኖሩን ፡ እያወቀ ፡

ጉዳዩ ፡ በተቻለ ፡ ፍጥነት ፡ በቅርብ ፡ ለሚገኘው ፡ ፖሊስ ፡ ወይም ፡ የአስተዳደር ፡ ባለሥልጣን ፡ ለማስታወቅ ፡ የተቻለውን ፡ ያህል ፡ ያልደከመ ፡ እንደሆነ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ እሥራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) ይኸንኑ ፡ ወሬ ፡ እራሱ ፡ ያገኘ ፡ ወይም ፡ ከሌሎች ፡ ሰዎች ፡ የሰማ ፡ ማንኛውም ፡ ያስተዳደር ፡ ባለሥልጣን ፡ ጉዳዩ ፡ በተቻለ ፡ ፍጥነት ፡ ለፖሊስ ፡ እንዲደርስ ፡ የተቻለውን ፡ ያህል ፡ ያልደከመ ፡ እንደሆነ ፡ ከሁለት ፡ ዓመት ፡ በማያንስ ፡ እሥራት ይቀጣል ።

የአገሬው (የመንደርተኞቹ) ፡ የጋራ ፡ ኃላፊነት ፡

፲. (፩) የማናቸውም ፡ ዘላን ፡ ጐሣ ፡ ወይም ፡ ደንበኛ ፡ መኖሪያ ፡ የቆረቆረው ፡ እንዳ (ዘር—ትውልድ) ወገን ፡ የሆነው ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ይህን ፡ አዋጅ ፡ በመተላለፍ ፡ ወንጀል ፡ ፈጽሞ ፡ ቢገኝ ፡ ቢፈረድበትም ፡ ባይፈረድበትም ፡ ጐሣው ፡ ወንጀሉን ፡ ለማስቀረት ፡ አለመቻሉን ፡ ሆነ ፡ በራሱና ፡ በወገኖቹ ፡ ላይ ፡ ሲደርስ ፡ የሚችለውን ፡ ጉዳት ፡ ከቁጥር ፡ ሳያገባ ፡ ወንጀለኛውን ፡ ይዞ ፡ ለፖሊስ ፡ ለማስረከብ ፡ የሚቻለውን ፡ ያህል ፡ የደከመ ፡ መሆኑን ፡ ካላስረዳ ፡ በስተቀር ፡ እያንዳንዱ ፡ የቤተሰብ ፡ ኃላፊ ፡ ወንጀሉ ፡ ለቆየበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ በየወሩ ፡ እስከ ፡ አምሳ ፡ ብር ፡ ሲደርስ ፡ በሚችል ፡ የገንዘብ ፡ መቀጫ ፡ ይቀጣል ።

(፪) ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በራሱ ፡ ጐሣ ፡ ወይም ፡ እንዳ ፡ ውስጥ ፡ ካልተገኘ ፡ አፍራሽ ፡ ማስረጃ ፡ ካልቀረበ ፡ በቀር ፡ በዚህ ፡ አዋጅ ፡ የተመለከተውን ፡ ሕግ ፡ በመተላለፍ ፡ ወንጀል ፡ በመሥራት ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ ይቆጠራል ።

(፫) ከተከሰሰው ፡ ጐሣ ፡ ጋር ፡ ወይም ፡ በተከሰሰው ፡ እንዳ መንደር ፡ ውስጥ ፡ መኖሩን ፡ ያቋረጠ ፡ ማንኛውም ፡ የቤተሰብ ፡ ኃላፊ ፡ በጠየቀ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መቀጫውን ፡ ከመክፈል ፡ ነፃ ፡ ሊያደርገው ፡ ይችላል ።

(፬) በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ በዝርዝር ፡ የተመለከተውን ፡ ጥፋት ፡ በመፈጸም ፡ የክስ ፡ ማመልከቻ ፡ የሚቀርበው ፡ በጐሣው ፡ ወይም ፡ በእንዳው ፡ ሕጋዊያን ፡ ወኪሎች ፡ ስም ፡ ነው ። ለክሱ ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ ፊት ፡ መቅረብ ፡ ያለባቸውም ፡ ወኪሎች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።
—ሀ—ጐሣው ፡ ወይም ፡ እንዳው ፡ ወይም ፡ በነርሱ ፡ ማንኛውም ፡ የቤተሰብ ፡ ኃላፊ ፡ የተከሰሱትን ፡ ሰዎች ፡ አልወክልም ፡ ብሎ ፡ የተቃወመ ፡ እንደሆነ ፡

(ሀ) ማንኛውም ፡ ተቀዋሚ ፡ የቤተሰብ ፡ ኃላፊ ፡ በክሱ ፡ ማመልከቻ ፡ ውስጥ ፡ በተጨማሪ ፡ እንዲገባ ፡ ማድረግ ፡ ወይም ፡

(ለ) ጐሣው ፡ ወይም ፡ እንዳው ፡ ወኪሎቹን ፡ እንዲመርጥ ፡ ማስታወቅ ፡ ነው ፡
ማስታወቂያው ፡ ለጐሣው ፡ ሹም ፡ ወይም ፡ ለመንደሩ ፡ ሹም ፡ በደረሰ ፡ በሀያ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ የወኪሎቹ ፡ ምርጫ ፡ ካልተደረገ ፡ ጐሣው ፡ ወይም ፡ እንዳው ፡ በክሱ ፡ ማመልከቻው ፡ የተመለከቱትን ፡ ሰዎች ፡ ወኪል ፡ እንደመረጠ ፡ ይቆጠርበታል ።

(በ፲፱፻፶፰ ፡ የወጣውን ፡ የሽፍቶች ፡ ሕግ ፡ ማሻሻያውን ፡ መመልከት ፡ ነው ፡)

፲፩. መቀጫውን ፡ የሚወስን ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ ፡ ጊዜውን ፡ መለየት ፡ አለበት ፡ ገንዘቡ ፡ የሚከፈልበት ፡ ጊዜም ፡ ከሁለት ፡ ወር ፡ መብለጥ ፡ የለበትም ፡

እንደዚህም ፡ ትእዛዙ ፡ ከመቀጫው ፡ ነፃ ፡ ያልሆነውና ፡ የመቀጫውን ፡ ገንዘብ ፡ በተወሰነ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ያልከፈለ ፡ ሰው ፡ እስከ ስድስት ፡ ወር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ እሥራት ፡ እንዲቀጣ ፡ መወሰን ፡ አለበት ።

<u>የቦታ ፡ ኃላፊነት</u>

፲፩. (፩) አንድ ፡ ዳኛ ፡ (ማጂስትሬት ፡) ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በአንቀጽ ፡ ፪ ፡ በዝርዝር ፡ እንደተመለከተው ፡ ያሉት ፡ ሽፍቶች ፡ በዳኝነቱ ፡ ሥልጣን ፡ ክልል ፡ ውስጥ የወንበዴነት ወንጀል ፡ ፈጽመውበት ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ፡ የቀረበለት ፡ እንደሆነና ፡ የተዘረፈውም ፡ ሀብት ፡ ያልተገኘ ፡ እንደሆነ ፡ ወንጀሉ ፡ የተፈጸመው በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ በዳኝነቱ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ቢሆንም፡ ባይሆንም ፡ ወንጀሉ ፡ ከተፈጸመበት ፡ ቦታ ፡ እስከ ፡ ፲ ፡ ኪሎሜትር ፡ እርቀት ፡ ባለው ፡ ክልል ውስጥ በሚኖሩት ፡ የቤተሰብ ኃላፊዎች ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ በተሰረቀው ፡ ንብረት ፡ ዋጋ ፡ ልክ ፡ በአንቀጽ ፡ ፲(፩) በተመለከተው ፡ አኳኋን ፡ ተፈጻሚ ፡ የሚሆነውን ፡ የገንዘብ ፡ መቀጫ ፡ የመጣል ፡ ሥልጣን ፡ ይኖረዋል ።

(፪) ከላይ ፡ የተጠቀሱት ፡ የቤተሰብ ፡ ኃላፊዎች ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚቀርቡት ፡ በወንጀል የተከሰሰ ፡ ሰው ፡ በሚቀርበው ፡ ዓይነት ፡ ነው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ከዳኛው ፡ ፊት ፡ እራሱ ፡ ባልቀረበውና መቃወሚያ ፡ የማቅረብ ፡ ዕድል ፡ ባልተሰጠው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ትእዛዝ ፡ አይሰጥም ።

(፫) ዳኛው ፡ በወንጀል ፡ ክስ ፡ እንደሚደረገው ፡ ሁሉ ፡ የገንዘብ ፡ መቀጫ ፡ እንዲከፍሉ ፡ የሚፈርድባቸው ፡ ሰዎች ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ በንዑስ ፡ ክፍል ፡ (፩) እንደተመለከተው ፡ መሆናቸውን ፡ ማረጋገጥ ፡ አለበት ።

(፬) አቤት ፡ ባዩ ፡ በመሃላ ፡ የሚሰጠው ፡ ቃል ፡ ለተሰረቀው ፡ ሀብት ፡ ብዛት ፡ ቀዳሚ ፡ ማስረጃ ፡ ይሆናል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ዳኛው ፡ የገንዘብ ፡ መቀጫ ፡ እንዲከፍሉ ፡ የሚፈረድባቸው ፡ ሰዎች ከሚያደርጉት መስቀለኛ ፡ ጥያቄ ሌላ ፡ አቤት ፡ ባዩ ፡ የሰጠው ፡ የመሃላ ፡ ቃል ፡ እውነተኛ ፡ መሆኑን ፡ ለማረጋገጥ ፡ የተቻለውን ፡ ያህል ፡ መጣርና ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ንዑስ ፡ ክፍል (፮) የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ የሚፈጸምበት ፡ መሆኑን ፡ ለአቤት ፡ ባዩ ፡ ማስጠንቀቅ ፡ ይገባል ።

(፭) ዳኛው ፡ በሚሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ ጥፋቱን ፡ ለመከላከል ፡ ወይም ፡ ወንጀለኛውን ፡ ለመያዝ የነበረውን ፡ የያንዳንዳቸው ፡ አጋጣሚና ፡ ይኸንኑ ፡ ለመፈጸምም ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ያደረጉትን ፡ ጥረት ፡ በማመዛዘን ፡ የመቀጫው ፡ ገንዘብ ፡ በቀረቡለት ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ መካከል ፡ ወይም ፡ ከነሱ ፡ በጥቂቶቹ ፡ መካከል ፡ እንዲከፋፈል ፡ ማድረግ ፡ አለበት ።

(፮) የመቀጫው ፡ ገንዘብ ፡ ገቢ ፡ እንደሆነ ለአቤት ፡ ባዩ ፡ መከፈል ፡ አለበት ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ገንዘቡ ፡ ከተከፈለ ፡ በኋላ ፡ አቤት ፡ ባዩ ፡ ከጠፋበት ፡ ገንዘብ ፡ በላይ ፡ የጠየቀ ፡ ለመሆኑ፡ ማስረጃ ፡ ለዳኛው ፡ ከቀረበ ፡ በሐሰት ፡ በመመስከሩ ፡ ከሚደርስበት ፡ የወንጀል ፡ ቅጣት ፡ ሌላ ፡ ዳኛው ፡ በብልጫ ፡ የወሰደውን ፡ ገንዘብ ፡ በአምስት ፡ አባዝቶ ፡ መቀጫ ፡ እንዲከፍል ፡ ይፈርድበታል ።

(፯) ይህንኑ ፡ የመቀጫ ፡ ውሳኔ ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ዳኛው ፡ የተለመደውን ፡ የወንጀል ፡ ክስ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ መከተል፡ አለበት ።

(፰) በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ መሠረት ፡ በሚሰጠው ፡ በማናቸውም ፡ ትእዛዝ ፡ የመቀጫ ፡ ገንዘብ ፡ በማከፋፈል፡ ሆነ ፡ አቤቱታን ፡ በማሰናበት ፡ ትእዛዝ ፡ ጭምር ፡ ላይ ፡ የሚቀርበው ፡ ይግባኝ ፡ በወንጀል ፡ ነገር ፡ በሚሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ ወይም ፡ ፍርድ ፡ ላይ ፡ በሚቀርበው ፡ ዓይነት ፡ ነው ።

ነገር ፡ ግን ፡ የይግባኝ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አቤቱታውን ፡ ካላሰናበተ ፡ በቀር ፡ በማንኛውም ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ የተወሰነው የገንዘብ ፡ መቀጫ ፡ በሚቀነሰው ፡ ልክ ፡ በሌላው ፡ ወይም ፡ በሌሎች ፡ ሰዎች ፡ እንደዚሁም ፡ መቀጫ ፡ እንዳይከፍሉ ፡ በተወሰነላቸው ፡ ሰዎች ፡ ጭምር ፡ ላይ ፡ እንዲጨመር ፡ ሳያደርግ ፡ የገንዘብ ፡ መቀጫ ፡ እንዲከፍል ፡ ለተፈረደበት ፡ ሰው ፡ መቀጫውን ፡ ሊቀንስበት ፡ አይችልም ፡ ለሚጨመርበት ፡ ሰውም ፡ የመቃወም ፡ ዕድል ፡ ሳይሰጠው ፡ ሊጨመርበት ፡ አይችልም ።

(፱) የይግባኝ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ምናልባት ፡ አቤቱታው ፡ በመሰናበቱ ፡ ምክንያት ፡ ይግባኝ ፡ እንዲቀርብ ፡ የፈቀደ ፡ እንደሆነ ፡ የይግባኝ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እራሱ ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ንዑስ ክፍል ፡ (፭) የተመለከተውን ፡ የዕዳ ፡ ማከፋፈል ፡ ጉዳይ ፡ አይፈጽምም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በጉዳዩ ፡ ውሳኔ ፡ እንዲሰጥ፡ ነገሩን ፡ ለዳኛው ፡ (ማጂስትሬት ፡) ይመልሳል ፡ ዳኛው ፡ በሚሰጠው ፡ የዕዳ ፡ አከፋፈል ፡ ውሳኔ ፡ ላይም ፡ ይግባኝ ፡ ለማቅረብ ፡ ይቻላል ።

(፲) በዚህ ፡ አንቀጽ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ አቤት ፡ ባዩ ፡ የጉዳት፡ ካሣውን ፡ ከተቀበለ ፡ (ከተካሰ) በኋላ ፡ የተሰረቀው ፡ ሀብት ፡ በሙሉ ፡ ወይም በከፊል ፡ የተገኘ ፡ እንደሆነ ፡ ጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ ያልሆነው ፡ ንብረት ፡ ቢቻል ፡ አስቀድሞ ፡ በተገመተው ፡ ዋጋ ፡ ለአቤት ፡ ባዩ ፡ ይመለስለታል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ንብረቱ ፡ ተበላሽቶ ፡ ቢገኝ ፡ የብልሽቱ ፡ ዋጋ ፡ ግምት ፡ መቀነስ ፡ አለበት ።

(፲፩) ከጠፋው ፡ ሀብት ፡ የተገኘው ፡ ጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ እና ፡ ከዚህ ፡ ላይ ፡ በተመለከተው ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ መሠረት ፡ ከአቤት ፡ ባዩ ፡ የተገኘው ፡ ገንዘብ ፡ እንደዚሁም ፡ ለአቤት ፡ ባዩ ፡ ሊመለስ ፡ ያልተቻለ ፡ ዕቃ ፡ ሁሉ ፡ ዕዳውን ፡ በከፈሉ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ እንደየድርሻቸው ፡ መጠን ፡ ይከፋፈላል ።

## የማይከለከል ።

በአንቀጽ ፡ ፲ ፡ የተመለከተው ፡ ቅጣት ፡ በአንቀጽ ፡ ፲፩ የተመለከተውን ፡ የገንዘብ፡ መቀጫ ፡ እንዳይታዘዝ ፡ አይከለክልም ፡ የገንዘብ ፡ መቀጫም ፡ የእስራት ፡ ቅጣትን ፡ አያስቀርም ።

## የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ጠቅላላ ፡ ክፍል ፡

(፲፫) (፩) ከወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፶፯(፪) ፡ ፸፱—፹—፹፩—፹፪—፹፫ ፡ እና ፡ ከቁጥር ፡ ፪፹፰ እስከ ፡ ፪፲፫ ፡ በስተቀር ፡ ይህ ፡ ሕግ የወንጀለኛ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ጠቅላላ ፡ ክፍልን ፡ ይከተላል ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ የሚወስነው ፡ ማናቸውም ፡ አነስተኛ ፡ ቅጣት ፡ ከአንድ ፡ ሲሶ ፡ በታች ፡ መቀነስ ፡ የለበትም ።

(፪) በዚህ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የተሰጠው ፡ ማንኛውም ፡ ፍርድ ፡ በገደብ ፡ አይታገድም ።

(በ፲፱፻፵፱ ፡ የወጣውን ፡ የሽፍቶች ፡ ሕግ ፡ (ሁለተኛ ፡ ማሻሻያን) መመልከት ፡ ነው ።)

## የተሻሩ ሕጎች ፡

፲፬. ይህ ፡ሕግ ፡ ከመጽናቱ ፡ በፊት ፡ የተፈጸሙት ወንጀሎችን ፡ ክስ ቀርቦ በውዝፍ ፡ ያሉ ፡ ነገሮችንና ፡ ፍርድ ፡ የተሰጠባቸው ፡ ነገሮች ፡ የሚመለከት ፡ ጉዳይ ፡ ካልሆን ፡ በስተቀር ፡ በ፲፱፻፵፩ ፡ በቁጥር ፡ ፪፬ እና ፡ ፪፲፩ ፡ እንደዚሁም ፡ በ፲፱፻፵፪ ፡ በቁጥር ፡ ፪፰፱ ፡ የወጡት ፡ አዋጆች ፡ ተሽረዋል ።

### ተቀጥላ ፡ ፩ ፡ ለ

### የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ (ማሻሻያ) ፡ ሕግ ፡ (፲፱፻፶፯)

### የኤርትራ ፡ ጋዜጣ ፡ ቮልዩም ፡ ፲፯ ፡ ቁጥር ፡ ፯

(ሚያዝያ ፡ ፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ የኤርትራ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ እንዳጸደቀውና ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ እንደራሴ ፡ ሚያዝያ ፡ ፳፩ ፡ ቀን፡ እንዳወጀው)

መሳሪያዎችና ፡ ጥይቶች ፡ መያዝ ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ በቅርቡ ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ የተለመደ ፡ ተግባር ፡ ስለሆነ ፤ ያለፈቃድ ፡ መሣሪያና ፡ ጥይቶች ፡ የሚይዙትና ፡ ይህንን የመሳሰለ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ድርጊት ፡ የሚፈጽሙትን ፡ የሚቀጣ ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ሕግ ፡ ወንጀሉን ፡ ለማጥፋት ፡ በቂ ፡ ስላልነ ፤

የሚከተለው ፡ ሕግ ፡ ታውጇል ፡—

## አርእስትና ፡ ተፈጻሚ ፡ የሚሆንበት ፡ ቀን ፡

፩. ይህ ፡ ሕግ ፡ "የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ (ማሻሻያ) ሕግ ፡ (፲፱፻፶፯)" ተብሎ ፡ ሊጠራ ፡ ይቻላል ፡ በሕገ፡ መንግሥቱ ፡ ቁጥር ፡ ፺፰ ፡ መሠረት ፡ እንደነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ በሚታወጅበት ፡ ወይም ፡ በሚታተምበት ፡ ጊዜ ፡ ጸኑ ፡ ሆኖ ፡ ይሠራበታል ።

### የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ ስለ ፡ መሻር ፡

፪ (ሀ) ከቁጥር ፡ ፯፻፺፩ ፡ እስከ ፡ ቁጥር ፡ ፯፻ ፡ እነሱም ፡ ጭምርና ፡ ቁጥር ፡ ፯፻፬ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ተሽረዋል ።

(ለ) ቁጥር ፡ ፩ ንዑስ ፡ ቁጥር ፡ (በ) የቁጥር ፡ ፲፰ ፡ አዋጅ ፡ (ጥር ፡ ፲ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱) ፡ ተሽሯል ፡ ሆኖም ፡ በማንኛውም ፡ ቋሚ ፡ ሕግ ፡ ደንብ ፡ ወይም ፡ አዋጅ ፡ ውስጥ ፡ ሊገኝ ፡ የሚችል ፡ ወደ ፡ ተባለው ፡ ቁጥር ፡ ፲፰ ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፩ ንዑስ ፡ ቁጥር ፡ (በ) የሚመራ ፡ ነገር ቢኖር፡ በዚሁ ፡ ሕግ ፡ ምዕራፍ ፡ ፫ ፡ በአዲሱ ፡ ቁጥር ፡ ፬፻፴፯ ፡ (ሀ) እንደተደነገገው መነበብ አለበት ።

## መሣሪያ ፡ ጥይቶች ፡ ወዘተ ፡ የያዙትን የሚቀጣ አዲስ ፡ ድንጋጌ ፡

አዲስ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሁለተኛ ፡ መጽሐፍ ፡ አንቀጽ ፡ ፯ ፡ ምዕራፍ ፡ አንድ ፡ (ሀ) ተብሎ ፡ የሚጠራ ፡ በሰው ፡ ሕይወትና ፡ ደኅንነት ፡ ላይ ፡ ጥፋት ፡ እንዳይደርስ ፡ መከላከልን ፡ የሚመለከት ፡ ቁጥር ፡ ፬፻፴፯ (ሀ) ተጨምሯል ፡ አንቀጹም ፡ እንደሚከተለው ፡ ይላል ፡

ቁጥር ፤ ፩፻፴፯ (ሀ) ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ማንኛውም ፡ ዓይነት ፡ መሣሪያ ፡ ቦምብ ፡ ፈንጂዎች ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ዓይነት መሣሪያ ፡ ያለው ፡ የሚጠቀምበት ፡ (በእጁ ፡ የያዘም ፡ ሆነ ፡ ያስቀመጠ) የሚነግድ ፡ ወይም ፡ የሚለውጥ ፡ ከተገቢው ባለሥልጣን ፡ ደንበኛ ፡ ፈቃድ ፡ ካልኖረውና ፡ የተሰጠውን ፡ ፈቃድ ፡ በሚፈቅደው ፡ መሠረት ፡ ካልሆነ ፡ በስተቀር ፡ ጥፋተኛ ፡ ሆኖ ፡ ከተገኘ ፡ እስከ ፡ ፭ ፡ ዓመት ፡ እሥራት ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ፪ሺ፭፻ ፡ ብር ፡ በሚደርስ ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ በሁለቱም ፡ ይቀጣል ።

## ተቀጥላ ፡ ፩ ፡ ሐ

ስለጋራ ሓላፊነት ፡ የወጣ ፡ ሕግ ፡ (፲፱፻፳ ፡ ዓ.ም.)

የኤርትራ ፡ ጋዜጣ ፡ ቮልዩም ፡ ፲፪ (፲፱፻፳ ፡ ዓ. ም.) ቁጥር ፡ ፱.

(ሐምሌ ፡ ፲፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳ ፡ ዓ. ም. የኤርትራ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ እንዳፀደቀውና ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ እንደራሴ ፡ ሐምሌ ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳ ፡ ዓ. ም. እንዳወጀው ።)

በአንዳንድ ፡ ገጠር ፡ ቀበሌዎች ፡ ሆነ ፡ ተብሎ ፡ የተፈጸሙ ፡ ብዙ ፡ ጥፋቶች ፡ (ጉዳቶች) ምስክሮች ፡ ለፖሊስ ፡ ለማመልከት ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ፡ ምክንያት ፡ ሳይቀጡ ፡ ስለሚሄዱ ፤
የሚከተለው ፡ ሕግ ፡ ወጥቷል ፡—

አርዕስት

፩. ይህ ፡ ሕግ ፡ "ስለጋራ ፡ ኃላፊነት ፡ የወጣ ፡ ሕግ ፡ (፲፱፻፳ ፡ ዓ. ም. )" ተብሎ ፡ ሊጠቀስ ይቻላል ፤ በጋዜጣ ፡ ከወጣ ከአንድ ወር ፡ በኋላም ፡ ጽኑ ፡ ሆኖ ፡ ይሠራበታል ።

የጋራ ፡ ኃላፊነት ፡

፪. ይህ ፡ ሕግ ፡ ጸንቶ ፡ በሥራ ፡ ላይ ከዋለ በኋላ ፡ አንድ ፡ መንደር ክልል ፡ ውስጥ ፡ በቤት ፡ በከብት ፡ በዛፍ ፡ በእህል ፡ ወይም ፡ በድርቆሽ ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ቢደርስና ፤

ይህም ፡ ጉዳት ፡ በደረሰ ፡ በአሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ጉዳቱን ፡ ማን ፡ እንዳደረሰው ፡ ማንም ፡ ሰው፡ ለፖሊስ ፡ ሳያመለክት ፡ ቢቀር ፤ ፖሊስም ፡ ጥፋተኛውን ፡ ለማወቅ ፡ ካልቻለ ፤

በመንደሪቱ ፡ የደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ወንጀል ፡ አለመሆኑን ፡ ካላረጋገጠ ፡ በስተቀር ፤ የመንደሪቱ ፡ ነዋሪዎች፡ አንድ ፡ ላይ ፡ከአምስት ፡ መቶ ፡ እስከ አምስት ፡ ሺ ፡ ብር ፡ በሚደርስ ፡ ይቀጣሉ ።

ሥነሥርዓት ፡

፫. ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ (ማጅስትሬት) የሥልጣን ፡ ዝቅተኛ ፡ ወሰን ፡ ቢኖረውም ፤ በሌላ ፡ በኩል ፡ በየጊዜው፡ ወጥተው ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የዋሉት ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓቶች ፡ እንደተጠበቁ ሆነው ፡ ከሚከተሉት ፡ በስተቀር ፡ ከላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አንቀጽ ፡ የተገለጸውን ፡ ቅጣት ፡ ይወስናል ።

(ሀ) የተከሰሰው መንደር ፡ ለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ በተመረጡ ፡ ሰዎች ፡ ይወከላል ፡ ወይም ፡ የክሱ ፡ ወረቀት ፡ ለመንደሩ ፡ አለቃ ፡ ከተሰጠ ፡ ከአንድ ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ ሰዎቹ ፡ ተመርጠው ፡ ካልተወከሉ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ወኪሎችን ፡ ይሾማል ።

(ለ) እራሳቸው ፡ በተለይ ፡ እንደተከሰሱ ፡ ተቆጥሮ ፡ ወኪሎቹ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መቅረብ ፡ አለባቸው ።

(ሐ) ቅጣቱ ፡ በተወሰነ ፡ በ፪ ወሮች ፡ ውስጥ ፡ ካልተከፈለ ፡ በ፲፱፻፺፯ ፡ ዓ. ም. በወጣው፡ ስመሪ ፡ ሪካቮሪ ፡ አክት ፡ መሠረት ፡ እንደአልተከፈለ ፡ ግብር ፡ ተቆጥሮ ፡ እንደገና ፡ ማስከፈል፡ ይቻላል ።

## ተቀጥላ ፡ ፩ ፡ መ

የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በኤርትራ ፡ እንዲሠራ ፡ ስለመደረጉ ፡ የወጣ ፡ ሕግ ፡ (፲፱፻፺፬ ፡ እ.ኤ.አ.) ፤
የኤርትራ ፡ ጋዜጣ ፡ ቮልዩም ......

(ይህ ፡ ሕግ ፡ እ.አ.አ. መስከረም ፡ ፲ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፺፱ ፡ የኤርትራ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ተቀብሎ ፡ አውጆታል ..)
(እ.ኤ.አ. በ፲፱፻፺፯ ፡ በአዋጅ ቁጥር ፡ ፶፰ ፡ የታወጀው ፡ የኢትዮጵያ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ ሕግ ፡ ሆኖ ፡ ይሠራበታል ።)

የሚከተሉት ፡ ሕጎች ፡ ተሽረዋል ፡—

(፩) እ.አ.አ. ሰኔ ፡ ፲፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፯ ፡ በወጣው ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፹፯ ፡ የተለወጠ ፡ እ.አ.አ. ሰኔ ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፯ ፡ በድንጋጌ ፡ ቁጥር ፡ ፻፲፱ ፡ አንቀጽ ፡ ፶፫ መሠረት ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡..............

(፪) እ. አ. አ. ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ በአዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፻፶፰ ፡ የወጣ ፡ ሕግ ፡

(፫) እ. አ. አ. በ፲፱፻፶፫ ፡ ስለስቅላት ፡ ሞት ፡ ቅጣት ፡ የወጣ ፡ ሕግ ።

<u>ተቀጥላ ፡ ፪ ሀ</u>

የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡
የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡
አሥመራ ፡

የይግባኝ ፡ ወንጀል ፡ ቁ. ፷፩/፲፱፻፷፬
(ያዲ ፡ ውግሪ ፡ ከ/ፍ/ቤት ቁ. ፷፩/፲፱፻፷፪)

ዳኞች ፡—

ብላታ ፡ ማታያስ ፡ ሀለተወርቅ ፡ ም/አፈንጉሥ ፡

ዶክተር ፡ ዮሐንስ ፡ ብርሃነ ፡

ዶክተር ፡ ጃንካርሎ ፡ ፖሊራ ፡

<u>እነ ፡ መስፍን ፡ ተስፋዬ ፡ ይግባኝ ፡ ባዮች ፤ አቃቤ ፡ ሕግ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡</u>

በዚህ ፡ ነገር ፡

፩ኛ ተከሳሽ ፡ መስፍን ፡ ተስፋዬ

፪ኛ ” ሳልሀ ፡ አመር

፫ኛ ” ዘሚካኤል ፡ ይልፋ

ከሌሎች ፡ ብዙ ፡ ያልተያዙ ፡ ሽፍቶች ፡ ጓደኞቻቸው ፡ ጋር ፡ ሁነው ፡ እተያዙበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ባደረጉት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ወንጀሎች ፡

፩ኛ በዘውታሪ ፡ ሽፍትነት ፡

፪ኛ ዘረፋና ፡ ቅሚያ ፡

፫ኛ በመደጋገም ፡ ከፖሊሶች በመታኮስ ፡

፬ኛ ሰው ፡ በማቁሰል ፡

፭ኛ ሰው ፡ በመዝረፍና ፡ በመግደል ።

በ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ. ም. እንደ ፡ ኤውሮፓ ፡ አቆጣጠር ፡ ስለሽፍቶች ፡ በወጣው ፡ የኤርትራ ፡ ውስጥ አስተዳደር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ በከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ክስ ፡ ቀርበባቸው ፡ ጥፋተኛ ፡ አይደለንም ፡ ብለው ፡ ክደዋል ።

የክስ ፡ ማመልከቻው ፡ በሁለት ፡ ገጽ ፡ ሰፋ ፡ ብሎ ፡ ተብራርቶ ፡ የወንጀሎች ፡ ዓይነትና እነኘሁ ፡ ወንጀሎች ፡ እንዴት ፡ እንደተሠሩ ፡ እንዲሁም ፡ ወንጀሎቹ ፡ የተሠሩበትን፡ ቀንና ፡ ወር ፡ ዓመት፡ ምሀረት ፡ ዘርዝሮ ፡ ስለሚያስረዳ ፡ ደግሞ፡ መጻፍ ፡ ጊዜ ፡ የሚወስድ ፡ በመሆኑ ፡ የክሱ ፡ ማመልከቻ እንደ ፡ አውሮፖ አቆጣጠር ፡ ፬/፲፪/፶፪ ፡ ተጽፎ ፡ የተፈረመውን ፡ ማየት ፡ ይበቃል ፡ በማለት ፡ አልፈነዋል ። የክሱም ፡ ማመልከቻ በዚህ ፡ ፋይል ፡ ውስጥ ፡ ተያይዟል ።

በዚሁ ፡ ክስ ፡ ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ምስክሮች ፡ ሰምቶ ፡ በሦስቱም ፡ ተከሾሳች ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ስለ ፈረደባቸው ፡ በማይገባ ፡ የተፈረደብን ፡ ፍርድ ፡ ይሰረዝልን ፡ ሲሉ ፡ ለጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ቤት ፡ ይግባኝ ፡ አቅርበዋል ።

<u>የይግባኙ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ባጭሩ ።</u>

የይግባኝ ፡ ባዮች ፡ ጠበቃ ፡ እንደሚከተለው ፡ ስለደንበኞቻቸው ፡ አመልክተዋል ፡ ፩ኛ—፪ኛ ፡ ይግባኝ ፡ ባዮች ፡ ከመጀመሪያ ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ሽፍቶች ፡ እንደነበሩ ፡ አልተካደም ፡ አምነዋል ።

ነገር ፡ ግን ፡ በሌሎቹ ፡ በክሱ ፡ ማመልከቻ ፡ ላይ ፡ በተጻፉት ፡ ክሶች ፡ ተከሳሾች ፡ አላመኑም ፡ በቂ ፡ የሚ ሆን ፡ ማስረጃና ፡ ምስክር ፡ አልቀረበባቸውም ። አቃቤ ፡ ሕግ ፡ በበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፲፫ ፡ ምስክሮች ፡ ማቅ ረቡና ፡ ማስመስከሩ ፡ እርግጥ ፡ ነው ። ከነኝሁ ፡ ስምንት ፡ ፖሊሶች ፡ ሁለት ፡ የማጅስትሬት ፡ መርማሪ ፡ ዳኞች ፡ ሦስት ፡ ፖሊስና ፡ ከማጅስትሬት ፡ ያልሆኑ ፡ የውጭ ፡ ሰዎች ፡ ማስመስከሩ ፡ እውነት ፡ ነው ።

ቢሆንም ፡ ይግባኝ ፡ ባዮች ፡ በፖሊስ ፡ እንደተያዙ ፡ እንደበደባለን ፡ ብለው ፡ ያልሠሩትን ፡ አምነው ፡ ተና ግረው ፡ ወደ ፡ ማጅስትሬትም ፡ በፖሊሶች ፡ እጅ ፡ ተይዘው ፡ በቀረቡ ፡ ጊዜ ፡ ፈርተው ፡ አምነዋል ።

በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ከፍተኛ ፡ ወንጀል ፡ ክስ ፡ በመገደድ ፡ ያመኑት ሲጸናባቸው አይገባም ። የእምነት ፡ ቃል ፡ በፈቃድ ፡ የተሰጠ ፡ ሲሆንና ፡ በሌላም ፡ በቂ ፡ ምስክርና ፡ ማስረጃ ፡ ሲደገፍ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በመገደድ ፡ ስለሆነ ፡ ነገር ፡ (አይደለም) አይጸናም ።

እነኝህ ፡ ይግባኝ ፡ ባዮች ፡ በከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በመሐላ ፡ ቃላቸውን ፡ ሲሰጡ ፡ የተናገሩት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ሊታመን ፡ የሚገባው ።

በ፫ኛው ፡ ክስ ፡ ወይዘሮ ፡ ትማር ፡ ገብረግዚ ፡ የቆሰለች ፡ ጊዜ ፡ ፩ኛ ፡ ተከሳሽ ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ ሁለት ፡ ነበሩ ፡ ፩ኛ ፡ ተከሳሽን ፡ አይቸዋለሁ ፡ ፪ኛውን ፡ ሰው ፡ ጨለማ ፡ ስለነበረ ፡ አላየሁትም ፡ ብሎ ፡ የመሰከረው ፡ ፩ኛው ፡ ሐ. አ. ም. ለተከሰሰችው ፡ ሴት ፡ ባሉዋ ፡ ነው ፡ በጨለማ ፡ አንደኛውን ፡ ተከሳሽ ፡ እንደምን ፡ ለይቶ ፡ አየ ፡ በማለት ፡ የሁሉንም ፡ ምስክሮች ፡ ቃል ፡ በመዘርዘር ፡ የነቀፋበትን በሰፊው ገልጸው ፡ በማብራራት ፡ ተናግረዋል ።

<u>ስለ ፡ ሕግ ፡ ክርክር ፡ የቀረቡት ።</u>

ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተከሳሾቹ ተመስክሮባቸዋል - ያለ ፡ እንደሆነ ሊቀጡ ፡ የሚገባቸው ፡ በዚህ ፡ በተከሰሱ በትና ፡ በከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በተፈረደባቸው ፡ የኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ አስተዳገር ስለ ሽፍቶች ፡ ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. በወጣው ፡ አስቸኳይ ፡ ትእዛዝ ፡ ሳይሆን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ነው ፡ በማለት ።

የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ በቁጥር ፡ ፳፯/፶፭ ፡ አንቀጽ ፡ ፫ኛ ፯ ፡ በወጣው ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ከኢት ዮጵያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ጋር ፡ በመጥቀስ ፡ የኢት. ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፯ ፡ በመጥቀስ ፡ በሰ ፊው ፡ አብራርተው ፡ ከተናገሩ ፡ በኋላ ፡ ፩ኛ—፪ኛ ፡ ይግባኝ ፡ ባዮች ፡ ጥፋተኛ ፡ ናቸው ፡ ቢባልም ፡ በነኝህ ፡ በጠቀስኩዋቸውና ፡ አብራርቼ ፡ ባስረዳሁት ፡ ሁኔታ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ይቀጣሉ ፡ እንጂ ፡ በተከሰሱበት ፡ በወንበዴዎች፡ አዋጅ ፡ አይቀጡም ።

በ፫ኛ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ ምንም ፡ ማስረጃ ፡ ስላልተገኘበት ፡ በሰላም ፡ እቤቱ ፡ እየሠራ ፡ የሚኖር ፡ መሆኑን፡ ስላስመሰከረ ፡ በነፃ ፡ ይለቀቅልኛል ፡ ሲሉ ፡ አመለከቱ ።

<u>አቃቤ ፡ ሕጉ ፡ የመለሱት ።</u>

በሦስቱም ፡ ይግባኝ ፡ ባዮች ፡ ላይ ፡ ክስ ፡ ሲቀርብባቸው ፡ በክሱ ፡ ማመልከቻ ፡ ላይ ፡ ተዘርዝሮ ፡ ተገልጾ ፡ ከተነበበላቸው ፡ በኋላ ፡ ጥፋተኛ ፡ አይደለንም ፡ ስላሉ ፡ አቃቤ ፡ ሕግ ፡ ፲፫ ፡ ምስክሮች ፡ አቅርቦ ፡ ባይነት ፡ ባይነቱ ፡ አጣርቶ ፡ አስመስክሩዋል ። የምስክሮች ፡ ዝርዝር ፡ ቃል ፡ በከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ ተገልጾ ፡ ተጽፎ ፡ ስለሚገኝ ፡ መድገሙ ፡ የፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ጊዜ ፡ ማጥፋት ፡ ይሆናል ፡ ያንኑ ፡ የተጻፈውን ፡ ተመልከቱልኝ ።

የይግባኝ ፡ ባዮች ፡ ጠበቃ ፡ በተከሳሾች ፡ ላይ ፡ የቀረበ ፡ ማስረጃ ፡ ምስክርነት ፡ በፖሊስ ጣቢያና ፡ በማጅ ስትሬት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ያመኑበት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ይላሉ ፡ እንጂ ፡ እሳቸው ፡ እንዳሉት ፡ ሳይሆን ፡ በሌሎችም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ምስክሮች ፡ አቃቤ ፡ ሕግ ፡ ነገሩን ፡ አስረድተዋል ። እንዲሁም ፡ በተከሳሾች ፡ የቆሰሉና ፡ የተዘረፉ ፡ አስረድተዋል ።

ተከሳሾች ፡ በመገደድ ፡ የሰጡት ፡ ቃል ፡ አይጸናባቸውም ፡ ለሚሉት ፡ እነሱ ፡ የሰጡት ፡ ቃል ፡ ያለመገደድ በፈቃድ ፡ ነው ። ለዚሁም ፡ አስረጅ ፡ እነሱ ፡ በፖሊስና ፡ በማጅስትሬት ፡ ፍ/ቤት ፡ ፊት ፡ የሰጡት ፡ ቃልና ፡ ከያይነቱ ፡ ወንጀል ፡ ምስክሮች ፡ የመሰከሩባቸው ፡ የተያያዘና ፡ የተመሳሰለ ፡ ሆኖ ፡ ተገኝቷል ።

ስለዚህ ፡ በፖሊስም ፡ ሆነ ፡ በማጅስትሬት ፡ አንዳች ፡ መገደድ ፡ የሌለበት ፡ በትክክል ፡ የተመሰከረ ፡ ነው ። ለከፍተኛ ፡ ፍ/ቤትም ፡ ይህንኑ ፡ አመልክተው ፡ ነገሩን ፡ መርምሮ ፡ ትክክለኛ ፡ መሆኑን ፡ ካወቀ ፡ በኋላ ፡ ነው ፡ የፈረደባቸው ።

ስለ ፡ ፫ኛው ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ ጠበቃው ፡ አልተመሰከረበትም ፡ በመከላከያም ፡ ሰላማዊ ፡ ሰው ፡ ለመሆኑ፡ አስመስክሯል ፡ ላሉት ፡ ይህም ፡ ተመዛዝኖ ፡ የተመሰከረበት ፡ መሆኑ ፡ ታውቆ ፡ ተፈርዶበታልና ፡—ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መርምሮ ፡ ይረዳልኝ ፡ አሉ ።

ጠበቃው ፡ ስለ ፡ ሕግ ፡ ነጥብ ፡ ላቀረቡት ፡ ክርክር ፡ አቃቤ ፡ ሕጉ ፡ የመለሱት ፡ ባጭሩ ።

ይግባኝ ባዮቹ ፡ (ወንበዴዎቹ) ይህን ፡ ወንጀል ፡ የሠሩት ፡ በኤርትራ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ጊዜ ፡ ነው ። የኢትዮጵያ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፳፯/፶፭ ፡ ትእዛዝ ፡ አንቀጽ ፡ ፯ኛ ፡ ስለነበሩትና ፡ ስለ

ሚሠራባቸው ፡ ሕጎች ፡ ዘርዝሮ ፡ ያስረዳል ። የይግባኝ ፡ ባዮች ፡ ጠበቃ ፡ እንዳመለከቱት ፡ በፊት ፡ ይሠራበት ፡ የነበረውን ፡ ሕግ ፡ ዋጋ አይሰጠውምና ፡ በዚሁ ፡ በተከሰሱበት ፡ የወንበዴዎች ፡ አዋጅ በ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ. ም. የወጣው ፡ አዋጅ ፡ ከተግቢው ፡ ሥራው ፡ ላይ ፡ አውለነዋል ።

በወንጀለኛ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፯ ፡ የተሻረውን ፡ ሕጉ ፡ ተፈጻሚ ፡ ስለማድረግ ፡ ለተጠቀሰው ፡ ስለጠቅላላ ፡ ሕግና ፡ ስለ ፡ ልዩ ፡ ሕጉ ፡ ያለውን ፡ ልዩነት ፡ አብራርተው ፡ በሰፊው ፡ ተናግረዋል ።

ይግባኝ ፡ ባዮች ፡ የተከሰሱበት ፡ የሽፍቶች ፡ አዋጅ ልዩ ፡ አዋጅ ፡ መሆኑን ፡ አስረድተው ፡ የመከላከያ ፡ ጠበቃ ፡ የጠቀሱት ፡ ሕግ ፡ ለዚህ ፡ ወንጀል ፡ ተገቢነት ፡ ስለሌለው ይግባኝ ፡ ባዮች ፡ ላይ ፡ የቀረበውን ፡ ክስ ከፍተኛ ፡ ፍርድ ቤት በሚገባ ፡ መርምሮ ፡ ውሳኔ የሰጠበት ፡ ስለሆነ ፡ የተፈረደባቸው ፡ ፍርድ ፡ እንዲጸናና ፡ ይግባኙ ፡ እንዲሰረዝ ፡ ሲሉ ፡ ፍርድ ፡ ጠይቀዋል ።

<u>የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ትችትና ፡ የመዝገቡ ፡ ምርመራ ።</u>

በይግባኝ ፡ ባዩና ፡ በመልስ ሰጪ - መካከል ፡ የቀረበው ፡ ክርክር ፡ ባጭሩ ፡ ከላይ ፡ እንደተገለጸው ፡ ካመለከቱ ፡ በኋላ ፡ ስለምስክሮች ፡ ሁኔታ ፡ በመዝገቡ ፡ ውስጥ ፡ መርምረን ፡ ያገኘነውን ፡ እንደሚከተለው ፡ እና ብራራለን ።

፩ኛ—፪ኛ ፡ ይግባኝ ፡ ባዮች በክሱ ፡ ማመልከቻ ፡ በ፩ኛው ፡ ቁጥር ፡ በ(ሀ) ፊደል ፡ ለተከሰሱበት ፡ የሽፍትነት ፡ ወንጀል ፡ አስቀድመው ፡ ከማመናቸውና ፡ የተመሰከረባቸውም ፡ ከመሆናቸው ፡ በላይ አሁንም ፡ የይግባኝ ፡ ባዮች ፡ ጠበቃ ፡ ከሸፈቱበት ፡ ጊዜ ፡ አንስቶ ፡ እተያዙበት ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ሽፍቶች ፡ እንደነበሩ ፡ አረጋግጠው ፡ አምነዋል ።

የይግባኝ ባዮች ፡ ጠበቃ ፡ በምስክሮች ፡ በኩል ዋና ፡ ፍሬ ፡ አለው ፡ ብለው ፡ የሚከራከሩት ፡

፩ኛ በመገደድ ፡ ያመኑት እምነት አይጸናባቸውም ።

፪ኛ የመሰከሩባቸው ፡ እምነቱን ፡ ነው ፡ እነኝህም ፡ ፖሊሶችና ፡ የማጅስትሬት ፡ ፍ/ቤት ፡ ዳኞች ፡ ናቸው ።

፫ኛ ሌላ ፡ ለነገሩ ፡ አጥጋቢ ፡ የውጭ ምስክር ፡ አልተመሰከረባቸውም ።

፬ኛ በንዲህ ያለ ፡ ከባድ ፡ ወንጀል ፡ ሌላ ፡ በቂ ፡ አስረጂ ፡ ካልተገኘ ፡ በፖሊስና ፡ በማጅስትሬት ፡ እምነዋል ፡ በማለት ፡ ብቻ ፡ ሊፈረድባቸው ፡ አይገባም በማለት ፡ ነው ።

ስለሁሉም ፡ ተከሳሾች ፡ ሲከራከሩ ፡ በተለይ ፡ ደግሞ ፡ በክሱ ፡ ማመልከቻ ፡ በ፫ኛው ፡ ተራ ፡ ፊደል ፡(ሸ) በተጻፈው ክስ ወይዘሮ ፡ ትማር የቆሰለች ፡ ጊዜ ፡ ፩ኛ ፡ የሕግ ፡ አስከባሪ ፡ ምስክር ፡ የሱዋ ፡ ባል ፡ ሲመሰክር ፡ ያንለት ፡ ሌሊት ፡ ፩ኛ ፡ ተከሳሽና ፡ ሌላ ፡ ፪ኛ ሰው ፡ እንደነበር ፡ ሲመስክር ፡ ፩ኛ ፡ ተከሳሽን ፡ ለይቼ፡ አይቻለሁ ። ከሱ ፡ ጋር ፡ የነበረውን ፡ ፪ኛውን ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ጨለማ ፡ ስለነበረ ፡ አላየሁም ፡ ብለዋል ። እንዴት— ፩ኛ ፡ ተከሳሽን ፡ በጨለማ ፡ መለየት ፡ ቻለ በማለት ፡ የማይታመን ፡ ምስክር ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

እዚህም ፡ ላይ ፡ የመከላከያ ፡ ጠበቃ ዘንግተው ፡ ይሆናል እንጂ ፡ ፩ኛ ፡ የሕግ ፡ ምስክር ፡ ፩ኛ ተከሳሽን፡ ሊለይና ሊያውቀው ፡ የቻለው ፩ኛ ፡ በፊትም ፡ ስለሚያውቀው ፡ ፪ኛ ፡ ያንለት ሌሊት ፡ ሚስቱ ፡ የቆሰለች ቤት ፡ እቤት ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ምግብ ፡ አምጡ ፡ ባለ - ጊዜ ፡ እሳት ፡ ነዶ ፡ ስለነበር ፡ በዚያ ፡ ብርሃን ያየው ፡ ለመሆኑ ፡ ተረጋግጦ ፡ ታውቋል ።

እንዲሁም ፡ ፩ኛ—፪ኛ ፡ ተከሳሾች ፡ የተያዙ ፡ ለት ፡ እጫካ ፡ ተኝተው ፡ ከነመሣሪያቸው ፡ ተያዙ ፡ እንጂ፡ አልተታኮሱም ፡ ከፖሊሶች ፡ ጋር ፡ ተታኩሰው ፡ ተያዙ ፡ የተባለው ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ የይግባኝ ፡ ባዮች ፡ ጠበቃ ፡ ለተከራከሩት ፡ ፫ኛ ፡ ሕ. አስከባሪ ፡ ምስክር ፡ የፖሊሶች ፡ መሪ ፡ ሆኖ ፡ ሔዶ ፡ የነበረው ፡ መጀመሪያ ፡ እነሱ ፡ ተኵሱብን ፡ ተኵሰን ፡ ያዝናቸው ፡ ብሎ ፡ መስክሮበታል ።

በተቀረው ፡ ወንጀል ፡ ግን ፡ ከላይ ፡ በዚህ ፡ መዝገብ ፡ በ፲፪ኛው ፡ ገጽ ፡ ባንድ ፡ ፩. ፪. ፫. ፬. ተራ ፡ ቁጥር ፡ በመዘርዘር ፡ ተከሳሾች ፡ የምነት ፡ ቃል የሰጡ ጠበቃው ፡ ባሉት ፡ ዓይነት ፡ ሳይሆን ፡ በፈቃዳቸው ፡ ለመሆኑ ፡ በፖሊሶቹ ፡ ከመመሰከሩም ፡ በላይ ፡ የማጅስትሬት ፡ ዳኞች ፡ አረጋግጠው ፡ መስክረውባቸዋል ። በሌላ ፡ ምስክር ፡ አልተደገፈም ለተባለውም ፡ በየክሶቹ ፡ ዝርዝር ፡ ለተደረገው ፡ ወንጀል ፡ ከመከራውና፡ ካደጋው ፡ ተካፋይ ፡ የነበሩት ፡ ሰዎች ፡ በመሐላ ፡ የመሰከሩት ፡ ከተከሳሾች ፡ የእምነት ፡ ቃል ፡ ጋር ፡ የተያያዘና ፡ የተመጣጠነ ፡ ሆኖ ፡ በመገኘቱ ፡ በበቂ ፡ ምስክር ፡ እምነታቸው ፡ አልተደገፉም ፡ በንደዚህ ፡ ያለ ፡ ከፍተኛ ፡ ወንጀል ፡ በምነት ፡ ብቻ ፡ ሊፈረድ ፡ አይቻልም ፡ ሲሉ ፡ የይግባኝ ፡ ባዮች ፡ ጠበቃ ፡ ያቀረቡትን ፡ ክርክር ፡ አልተቀበልናቸውም ፡ የምስክሮችን ዝርዝር ፡ ቃል ፡ እንዳንተች ፡ በከፍተኛ ፡ ፍ/ርድ ፡ ቤት ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ በሚገባ ፡ ስለተገለጸ ፡ አልፈነዋል ። እሱኑን ማየት ፡ ብቻ ፡ ያስረዳል ።

፬ኛ—፭ኛ ፡ የመከላከያ ፡ ምስክሮችም ፡ ወንጀለኞች ፡ አብረው ፡ የታሰሩ ፡ ስለሆኑ ፡ ይህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አላመናቸውም ፡—ብለን ፡ ቃላቸውን ውድቅ አድርገነዋል ።

፫ኛ ፡ ተከሳሽ ፡ ዘሚካኤል ፡ ይልፉ ፡ ምንም ስላልተመሰከረበት ፡ በነፃ ፡ እንዲለቀቅ ፡ ብለው ፡ ለተከራከሩት ፡ በክሱ ፡ ማመልከቻ ፡ በ፪ኛ ፡ በ፫ኛ ፡ ተራ ፡ በ(ለ)ና ፡ በ(ሐ)፡ ፊደል በተዘረዘረው ፡ ከ፩ኛ ፡ ተከሳሽና፡ ካልተያዙት ፡ ሌሎች ፡ ጓደኞቹ ፡ ጋር ፡ ሆኖ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ጠብመንጃ ፡ ይዘው ፡ አዲኩዋላ ፡ መንገድ ፡

በመተባበር ፡ ተኩሰው ፡ ሲኞሪና ፡ ማሪያ ፡ ገሪዚያ ፡ ማሬኩ ፡ የምትባለው ፡ በዚሁ ፡ ተኩስ ፡ ውስጥ ፡ ተመታ ፡ ሞታለች ።

እንዲሁም ፡ ፩. ፖሎ ፡ ማሬንኩ ፡ ፍራንኩ ፡ ቴረሲ ፡ እና ፡
፪. ማሪያ ፡ እንተኒኤታ ፡ ማንሲኒ ፡ በመቁሰላቸው ፡ ገንዘብም ፡ ለመዘረፋቸው ፡ እራሳቸው፡ ተከሳሾቹ ፡ በፈቃዳቸው ፡ ከማመናቸውም ፡ በላይ በ፪. ፫. ፮. ፯ና ፲፪. የሕግ ፡ አስከባሪ ፡ ምስክሮች ፡ ተመ ስክሮባቸዋል ፡ ይህም ፡ የተመሰከረባቸው ፡ ቃልና ፡ የእምነት ፡ ቃላቸው ፡ የተመሳሰለና ፡ የተያያዘ ፡ ስለሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አምኖ ፡ ተቀብሎታል ።

የይግባኝ ፡ ባዮች ፡ ጠበቃ ፡ ዋና ፡ ክርክራቸው ፡ ይግባኝ ፡ ባዮች ፡ ተገድደው ፡ (ከመሠከሩት) ከሰጡት ፡ ቃል ፡ ይልቅ ፡ በከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ምለው ፡ የሰጡት ፡ ቃል ፡ የሚታመን ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ደጋግመው ፡ በጽሑፍም ፡ በቃልም ፡ አሳስበዋል ።

ለመገደዳቸው ፡ አንዳች ፡ ማስረጃ ፡ ወይም ፡ ምስክር ፡ አላቀረቡም ፡ ሕግ ፡ አስከባሪ ፡ ግን ፡ በፈቃዳቸው ፡ ያመኑ ፡ ለመሆናቸው ፡ ከማስመስከሩም በላይ ፡ የይግባኝ ፡ ባዮችን ፡ እምነት ፡ የሚደግፉ ፡ ምስክሮች ፡ በያ ይነቱ ፡ አቅርቦ ፡ አስመስክሩዋል ።

እንዲህ ፡ ነገሩ ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ የተጣራ ፡ ሲሆን ፡ ጠበቃው ፡ የተከሳሾች ፡ ቃል ፡ በመሐላ ፡ የተሰ ጠው ፡ በፊት ፡ በእምነት ፡ ተሰጠ ፡ ከተባለው ፡ ቃል ፡ ብልጫ ፡ አለውና ፡ የተከሳሾችን ፡ የመሐላ ፡ ቃል ፡ ፍ/ ቤት ፡ ይመንልኝ ፡ ለሚሉት ።

ከነኝህ ፡ ወንጀለኞች ፡ ቃል ፡ በሕግ ፡ አስከባሪ በኩል የቀረበውን ፡ የምስክሮች ፡ ቃል ፡ አምነን ፡ ልን ቀበለው ፡ ስለቻልን ፡ ፫ኛ ፡ ተከሳሽም ፡ በተከሰሰበት ፡ ወንጀል ፡ በሚገባ ተመስክሮበታል ብለናል ።

<u>ስለ ፡ ሕግ ፡ ክርክር ፡ ለቀረበው ።</u>

የይግባኝ ፡ ባዮች ፡ ጠበቃ ፡ አዋጅ ፡ ፳፯/፶፭ ፡ የወጣው ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ይህ ፡ አዋጅ ፡ እንደወጣ ፡ በኤርትራ ፡ ውስጣዊ ፡ አስተዳደር ፡ ይሠራበት ፡ የነበረው ፡ ሕግና ፡ አዋጅ ፡ ወድቅ ፡ እንደሆነ ፡ ታውቋዋል።

በዚህ ፡ በ፳፯/፶፭ ፡ አዋጅ ፡ በተለይ ፡ ያስፈልጋሉ ፡ ብሎ ፡ ካላወጀው ፡ በተቀር ፡ ውድቆች ፡ ናቸው ።/ ምክንያቱም ፡ ይህን ፡ የወምበዴዎች ፡ አዋጅ ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ የወጣውን ፡ ሕግ ፡ በዚህ ፡ በ፳፯/፶፭ ፡ ትእዛዝ ፡ አስ ፈላጊ ፡ ሕግ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ጸንቶ ፡ እንዲሠራበት ፡ የወጣ ፡ አዋጅ ፡ ስለሌለ ፡ በዚህ ፡ በወንበዴዎች ፡ አዋጅ ፡ ይግባኝ ፡ ባዮች ፡ ሊቀጡ ፡ አይገባቸውም ። የ፳፯/፶፭ ፡ አዋጅ ፡ ትእዛዝ ፡ ከህዳር ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፭ ፡ ዓ. ም. ጀምሮ ፡ የጸና ፡ ስለሆነ ፡ የሚሠራበት ፡ በዚሁ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ስላሉት ።

አቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ስለ ፡ ፳፯—፶፭ ፡ (አዋጅ) ትእዛዝ ፡ አንቀጽ ፡ ፯ ፡ ስለነበሩትና ፡ ስለሚሠራባቸው ፡ ሕጎች ፡ የሚያስረዳ ፡ መሆኑን ፡ ገልጸው ፡ ጠበቃው ፡ እንዳቀረቡት ፡ ክርክር ፡ በዚሁ ፡ ትእዛዝ ፡ በኤርትራ ሕገ መን ግሥት ፡ ጊዜ ፡ የተሠራውን ፡ ሕግ ፡ ዋጋ ፡ አይሰጠውም ፡ ብለዋል ። እንዲሁም ፡ በዚሁ ፡ ሕግ ፡ በ፯ኛው ፡ አን ቀጽ ፡ ስለነበሩት ፡ አዋጆች ፡ ሕጐች ፡ ደንቦች ፡ በሙሉም ፡ ሆነ ፡ በከፊል ፡ ላስተዳደሩ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆነው ፡ እንዲሠራባቸው ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ ሁሉ ፡ ወደፊት ፡ የሚወጡ ፡ ሕጐች ፡ ተሰርዘው ፡ እስኪተኩ ፡ ድረስ ፡ እንዳሉ ፡ ጸንተው ፡ የሚሠራባቸው ፡ ይሆናሉ ፡ ስለሚል ። በሕግ ፡ አስፈላጊ ፡ የተባሉት ፡ ሕጐች ፡ ካልተለዩ ፡ በኤርትራ ፡ አስተዳደር ፡ ጊዜ ፡ ይሠራባቸው ፡ የነበሩት ፡ ሕጐች ፡ ሁሉ ፡ ከህዳር ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፭ ፡ ዓ. ም. ወዲህ ፡ በሙሉ ፡ ውድቆች ፡ ናቸው ፡ ያሉትን ፡ ልንቀበላቸው ፡ አልቻልንም ።

ምክንያቱም ፡ በዚህ ፡ ትእዛዝ ፡ ፳፯/፶፭ ፡ ባንቀጽ ፡ ፯ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑት ፡ ሁሉ ፡ እንዲሠራባቸው ፡ ደን ግጓል ። ከዚህም ፡ በተቀር ፡ አስፈላጊ ፡ የሚሆኑትን ፡ ሕጐች ፡ በሕግ ፡ ለይቶ ፡ ካላወጣ ፡ በኤርትራ ፡ አስተዳ ደር ፡ ጊዜ ፡ የሚሠራባቸው ፡ ሕጐች ፡ አዋጆች ፡ ደንቦች ፡ ውድቅ ፡ ናቸው ፡ ብለው ፡ ጠበቃው ፡ ለሚከራከ ሩት ፡ ይህ ፡ የወምበዴዎች ፡ አዋጅ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ መንግሥት ፡ በውንብድና ፡ ምክንያት ፡ በሚከ ከሰሱ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ አዋጅ ፡ እየጠቀሰ ፡ ክስ ፡ አቅርቧል ።

እንግዲህ ፡ ስለ ፡ ትእዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፳፯/፶፭ ፡ አንቀጽ ፡ ፯ ፡ እና ፡ ስለ ፡ ወምበዴዎች ፡ አዋጅ ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ሁኔታ ፡ ከላይ ፡ እንደተገለጸው ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ የኤርትራ ፡ አስተዳደር ፡ በጊዜው ፡ ይሠራበት ፡ የነበረው ፡ አዋጅ ፲፱፻፶፯ ፡ ውድቅ ፡ ነው ፡ አስፈላጊ ፡ አይደለም ፡ ማለት ፡ አይቻልም ።

የይግባኝ ፡ ባዮች ፡ ጠበቃ ፡ በኢ. ወ. መ. ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፯ ፡ ይግባኝ ፡ ባዮች ፡ የሚቀጡበትን ፡ ሕግ ፡ የመ ምረጥ ፡ ጥያቄ ፡ ለማቅረብ ፡ መብት ፡ አላቸው ፡ ከዚህም ፡ ሌላ ፡ ተከሳሾች ፡ በዚህ ፡ ወንጀል ፡ በተከሰሱ ፡ ጊዜ ፡ በኤርትራ ፡ አስተዳደር ፡ በዚሁ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ስለሚሠራ ፡ ይህ ፡ ወንጀል ፡ የሚያስቀጣቸውም ፡ ቢሆን ፡ በዚሁ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ቅጣታቸውን ፡ በሚያቃልልላቸው ፡ ይቀጣሉ ፡ እንጂ ፡ ይህ ፡ የወንበዴዎች ፡ አዋጅ ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ማመዛዘኛ ፡ በሌለው ፡ ለፈራጅ ፡ ዳኛ ፡ አስተያየት ፡ በማይሰጥበት ፡ ሕግ ፡ አይቀጡም ።

ድሮውንም ፡ ይህ ፡ አዋጅ ፡ ባስቸኳይ ፡ የወጣ፡ነው ፡ እንጂ ፡ ለሁልጊዜ ፡ እንዲሠራበት ፡ አይደለም ፡ ላሉት፤ አቃቤ ፡ ሕጉም ፡ በመልሳቸው ፡ እንደገለጹት ፡ ሁሉ ፡ ቁጥር ፡ ፯ ፡ የኢት. ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ።

ከሕጉ ፡ ስለመለየት ፡ የተሻለውን ፡ ሕግ ፡ ተፈጻሚ ፡ ስለማድረግ ፡ የወጣው ፡ ስለ ፡ ጠቅላላ ፡ ሕጐች ፡ እንጂ ፡ ስለልዩ ፡ ሕጐች ፡ አይደለም ።

ስለ ፡ ልዩ ፡ ሕጐች ፡ በዚሁ ፡ የኢት. ወ. መ. ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፫ ፡ ለወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ጠቅላላ ፡ ሕግ ፡ ማሟያ ፡ የሚሆኑት ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ደንቦችና ፡ ልዩ ፡ ሕጐች ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው ።

እነዚህም ፡ የተለዩ ፡ መሆናቸው ፡ ባልተገለጠ ፡ ጊዜ ፡ የዚህ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መሠረታዊ ፡ ደንቦች ፡ ይፈጸሙባቸዋል ፡ ስለሚል ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ደንቦችና ፡ ልዩ ፡ ሕጐች ፡ የተጠበቁ ፡ መሆናቸው ፡ ያልተለዩ ፡ ሕጐች ፡ ቢሆኑ ፡ እንኳ ፡ የጠበቃውን ፡ ጥያቄ ፡ በተቀበልን ፡ ነበር ።

ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ አዋጅ ፡ የተለየ ፡ መሆኑ ፡ ታውቆ ፡ እንዲሁም ፡ ይኸው ፡ (የወረበሎች) የወምበዴዎች ፡ አዋጅ ፡ በቁጥር ፲፫ ፡ የወጣው ፡ እንደዚሁ ፡ ያለ ፡ ክርክር ፡ እንዳይፈጠር ፡ ታስቦበት ፡ በ፪ ፡ ማሻሻያ ፡ ሲያ ወጣ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ በዚሁ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ይሠራ ፡ ስለነበር ፡ ቁጥር ፡ ፶፯ ፡ በንዑስ ፡ ቁጥር ፡ ፪ ፡ በቁ ጥር ፡ ፭፱—እስከ ፡ (፹፫) ቁ. ፲፹፭—እና ፡ ፪፻፲፭ ፡ ለይተዋቸዋል ። የለያቸውም ፡ በጠቅላላው ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ነው ። ለዚሁም ፡ በኤርትራ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ አውሮፓ ፡ አቆጣጠር ፡ ታህሣሥ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ. ም. ተወስኖ ፡ በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ እንደራሴ ፡ እንደ ፡ አውሮፓ ፡ አቆጣጠር ፡ ጥር ፡ ፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷ ፡ ዓ. ም. ጸድቆ ፡ በ፪ኛ ፡ ማሻሻያ ፡ ሆኖ ፡ በወጣው ፡ በ፪ኛ ፡ አንቀጽ ፡ ተመልክቷ ።

ይህንና ፡ ይህን ፡ የመሳሰሉ ፡ ሕጐች ፡ ሁሉ ፡ እሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውሉ ፡ በቁጥር ፡ ፳፯/፶፭ ፡ ባንቀጽ ፡ ፮ ፡ የወጣውን ፡ ትእዛዝ ተቀብሎ ፡ እንዲሠራበት ፡ ስለተደረገ ፡ ይህ ፡ የወረበሎች ፡ የወንበዴዎች ፡ አዋጅ ፡ ዛሬም ፡ የሚሠራበት ፡ ነው ፡ ብለናል ።

ስለዚህ ፡ የጠበቃውን ፡ ክርክር ፡ የምንቀበልበት ፡ መንገድ ፡ በሕግም ፡ ሆነ ፡ በማስረጃና ፡ በምስክር ፡ በኩል ፡ ስላላገኘን ፡ ልንቀበለው ፡ ባለመቻላችን ፡ አቃቤ ፡ ሕጉ ፡ በማስረጃም ፡ ሆነ ፡ በሕግ ፡ ላቀረቡት ፡ ክር ክር ፡ ብልጫ ፡ በመስጠት ፤

የከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በሚገባ አጣርቶና ፡ መርምሮ ፡ የፈረደውን ፡ አጽንተን ፡ ይግባኙን ፡ አሰናብ ተናል ።

ይህ ፡ ፍርድ ፡ ዛሬ ፡ ሰኔ ፡ ፳፮ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፮ ፡ ዓ. ም. ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ባሉበት ፡ በችሎት ፡ ተነቦ ፡ ተሰምቷል ።

ተቀጥላ ፡ ፪ ፡ ለ ፡

የይግባኝ ፡ መዝገብ ፡ ቁጥር ፡ ፴፮/፷፬
የከፍተኛ ፡ ፍ/ቤት ፡ መዝገብ ፡ ቁጥር ፡ ፶፱/፷፪
መጋቢት ፡ ፲፪ ቀን ፡ ፲፱፻፷፬ ፡ ዓ. ም.

ዳኞች ፡—

ዶክተር ፡ ኢዮብ ፡ ገብረክርስቶስ ፤
አቶ ፡ በረኸ ፡ ስቋር ፤
ሸክ ፡ ጊዕደር ፡ መሐመድ ፡ ካሚል ።
እነወራሲ ፡ ዑቁባጋብር ፡ ተስፋሚካኤል ፡ ይግባኝ ፡ ባዮች ፡ ዓቃቤ ፡ ሕግ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ።

## ፍርድ

የነገሩ ፡ ሁኔታ ፤

፩. ነገሩ ፡ ሲጀመር ፡ ጥቅምት ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፪ ፡ ዓ. ም. በቀረበው ፡ የክስ ፡ ማመልከቻ ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ክሱ ፡ ተሻሽሎ ፡ መጋቢት ፲፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፪ ፡ ዓ. ም. ስለቀረበ ፡ እላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ ክስ ፡ በዚህ ፡ ተተክቷል ።

ክሱ ፡ በአምስት ፡ ክፍሎች ፡ የተከፋፈለ ፡ ሲሆን ፡ ፩ኛ ፡ ሦስት ፡ ተከሳሾች ፡ እ. አ. አ. በ፲፱፻፶፯ ፡ ስለ ሽፍቶች ፡ የወጣ ፡ አዋጅ ፡ ቁ. . ፪. ፫. የተመለከተውን ፡ በመተላለፍ ፤

ሀ/ ፩ኛ ተከሳሽ ፡ ከጥር ፡ ወር ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ. ም. እስከ ፡ ተያዘበት ፡ ቀን ፡ መስከረም ፡ ፲፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፪ ፡ ዓ. ም. ድረስ ፡ ከ፪ኛና ፡ ፫ኛ ፡ ተከሳሾች ፡ እንዲሁም ፡ ሌሎች ፡ ያልተያዙ ፡ ግብረ ፡ አበ ሮቹ ፡ ሁሉም ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ የያዙ ፡ ዓላማቸው ፡ የኃይል ፡ ወንጀል ፡ ለመፈጸም ፡ ከተቋቋሙ ፡ በኤርትራ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ቦታዎች ፡ በመዘዋወሩ ፡ ተከሷል ።

ለ/ ፪ኛ ፡ ተከሳሽ ፡ ከመስከረም ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፪ ፡ ዓ.ም. እስከ ፡ ተያዘበት ፡ ቀን ፡ መስከረም ፡ ፲፭ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፪ ፡ ዓ. ም. ድረስ ፡ ከ፩ኛና ፡ ፫ኛ ፡ ተከሳሾች ፡ እንዲሁም ፡ ሌሎች ፡ ያልተያዙ ፡ ግብረ ፡ አበሮቹ ፡ ሁሉም ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ የያዙ ፡ ዓላማቸው ፡ የኃይል ፡ ሥራ ፡ ለመፈጸም ፡ ከተቋቋሙ ፡ በምዕራባዊ ፡ ቆላና ፡ በሐማሴን ፡ በኤርትራ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ በመዘዋወሩ ፡ ተከሷል ።

ሐ/ ፫ኛ ፡ ተከሳሽ ፡ ከመስከረም ፡ ፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፪ ፡ ዓ. ም. እስከ ፡ ተያዘበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ መስከረም ፡ ፲፭ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፪ ፡ ዓ.ም. ከ፩ኛና ፡ ፪ኛ ፡ ተከሳሾች ፡ እንዲሁም ፡ ከሌሎች ፡ ያልተያዙ ፡ ግብረ ፡ አበሮቹ ፡ ሁሉም ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ የያዙ ፡ ዓላማቸው ፡ የኃይልና ፡ ወንጀል ፡ ለመፈጸም ፡ ከተቋቋሙ ፡ በምዕራባዊ ፡ ቆላና ፡ በሐማሴን ፡ የኤርትራ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ በመዘዋወር፡ ተከሷል።

፪ኛ ክስ ፡ ስለ ፡ አንደኛ ፡ ተከሳሽ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ከላይ ፡ የተጠቀሰውን ፡ አዋጅ ፡ በመተላለፍ፡ ተከሳሽ ፡ ግንቦት ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፩ ፡ ዓ. ም. በ15.03 ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ በኪሎ ፡ ሜትር ፡ ፶፰ ከአሥመራ ፡ ወደ ፡ ከረን ፡ በሚወስደው ፡ መንገድ ፡ ከሌሎች ፡ ግብረ ፡ አበሮቹ ፡ ወረበሎች ፡ ገና ፡ ያልተያዙ ፡ ሁሉም ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ የያዙ ፡ አንድ ፡ የሳታዬ ፡ አውቶቡስና ፡ አንድ ፡ መኪና ፡ አውቶቡስ ፡ አቁመው ፡ በኃይልና ፡ በማስፈራራት ፡ የኢት. ብር ፡ $ 45.15 የሳታዬ ፡ ማኅበር ፡ እንዲሁም ፡ ከተሳፋሪዎች ፡ ገንዘብና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዕቃዎች ፡ ስለ ፡ ዘረፉዋቸው ፡ ተከሷል ።

፫ኛ ክስም ፡ ስለ ፡ አንደኛ ፡ ተከሳሽ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እላይ ፡ የተጠቀሰውን ፡ አዋጅ ፡ በመተላለፍ፡ ተከሳሽ ፡ ግንቦት ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፩ ፡ ዓ. ም. ከ04.00 እስከ ፡ 07.00 ሰዓት ፡ በኪሎ ፡ ሜትር ፡ ፻፮ ፡ አሥመራ ፡ ወደ ፡ አቆርዳት ፡ በሚወስደው ፡ መንገድ፡ ከ፫ ፡ ወረበሎች ፡ ገና ፡ ያልተያዙ ፡ ግብረ፡ አበሮቹ ፡ ሁሉም ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ የያዙ ፡ ፯ ፡ የጭነት ፡ መኪናዎች ፡ በኃይልና ፡ በማስፈራራት፡ አቁመው ፡ ገንዘብ ፡ ሰዓቶች ፡ የወርቅ ፡ ጌጣጌጥና ፡ ሌሎች ፡ ዕቃዎች ፡ ዘርፈው ፡ ስለወሰዱባቸው ፡ ተከሷል ።

፬ኛ ክስም ፡ በተጨማሪ ፡ ስለ ፡ አንደኛ ፡ ተከሳሽ ፡ ብቻ ፡ ነው ። እ. ኤ. አ. በ፲፱፻፶፯ ፡ ሐምሌ ፡ ፲፯ ፡ ቀን፡ ፲፱፻፷፩ ፡ ዓ. ም. በ15.30 ሰዓት ፡ ገደማ ፡ ሲሆን ፡ በ፶፰ ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ አሥመራ ፡ ከረን ፡ በሚወስደው ፡ መንገድ ፡ ከሌሎች ፡ ፩ ፡ ወረበሎች ፡ ገና ፡ ካልተያዙ ፡ ግብረ ፡ አበሮቹ ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡ ሁሉም ፡ የጦር ፡ መሣሪያ፡ የያዙ ፡ የሳታዬ ፡ አውቶቡስ ፡ አቁመው ፡ ከተሳፋሪዎቹ ፡ አንዱ ፡ የመቶ ፡ አለቃ ፡ መኰንን ፡ መብራሀቱን ፡ ገድለው ፡ እንዲሁም ፡ በኃይልና ፡ በማስፈራራት ፡ ከሌሎች ፡ ተሳፋሪዎች ፡ ገንዘብና ፡ ሰዓቶች ፡ ሬድዮ ፡ ጭምር ፡ ስለወሰዱባቸው ፡ ተከሷል ።

፭ኛ ክስ ፡ ስለሦስቱ ፡ ተከሳሾች ፡ ነው ። እ. አ. አ. በ፲፱፻፶፯ ፡ ስለሽፍቶች ፡ የወጣ ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፪. ፫. ፮. ፫ . የተመለከተውን ፡ በመተላለፍ ፡ ተከሳሽ ፡ መስከረም ፡ ፲፭ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፪ ፡ ዓ. ም. በ07.00 ሰዓት ፡ ገደማ ፡ ሲሆን ፡ ከአሥመራ ፡ አቆርደት ፡ በሚወስደው ፡ መንገድ ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ ፻፮ ፡ ከሌሎች ፡ ሁለት ፡ ገና ፡ ያልተያዙ ፡ ወረበሎች ፡ ሁሉም ፡ ባለ ፡ ጦር ፡ መሣሪያ ፡ የሆኑ ፡ ለመዝረፍ ፡ ሲጠባበቁ ፡ ቆይተው ፡ በኮማንደስ ፡ ወታደሮች ፡ ተኩስ ፡ ስለከፈቱባቸው ፡ ተከሰዋል ።

በተኩሱ ፡ መካከል ፡ ፫ቱም ፡ ተከሳሾች ፡ ተይዘው ፡ ፪ኛ ፡ ቆስለዋል ። በ፩ኛ ፡ ተከሳሽ ፡ አንድ ፡ ረጅም ፡ ምንሽር ፡ ከ፪ኛ ፡ ተከሳሽ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሠራሽ ፡ ረሽ ፡ ጠብመንጃ ፡ ዓይነት ፡ ከ፫ኛ ፡ ተከሳሽ ፡ ደግሞ ፡ አንድ የእጅ ፡ ቦምብ ፡ ተይዘዋል ። ከተዘረፈው ፡ ገንዘብ ፡ ከ፩ኛ ተከሣሽ ፡ ፶፭ ፡ ብር ፡ ተገኝቶባቸዋል ፡ የሚል ፡ ክስ ፡ ነበር ።

፪. ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተከሳሾች ፡ የቀረበባቸውን ፡ ክስ ፡ የሚያምኑ ፡ ወይም ፡ የሚክዱ ፡ መሆናቸው ፡ ተጠይቆ ፡ ፩ኛው ፡ ተከሳሽ ፡ ፩ኛውን ፡ ፪ኛውን ፡ ፫ኛውን ፡ ክስ ፡ አምኖ ፡ የቀረውን ፡ ክስ ፡ ክዶ ፡ ጥፋተኛ ፡ አይደለሁም ፡ ብሏል ። ፪ኛውና ፡ ፫ኛው ፡ ተከሳሾች ፡ ወንበዴዎች ፡ አስገድደው ፡ ወስደውን ፡ እነሱ ፡ ዘንድ ፡ በምንገኝበት ፡ ጊዜ ፡ የኮማንደስ ፡ ወታደሮች ፡ ደርሰው ፡ ተኩስ ፡ ከፈቱ—ወንበዴዎች ፡ ጠብመንጃቸውን ፡ ትተው ፡ ሸሹ—ወንበዴዎች ፡ ትተው ፡ የሸሹትን ፡ ጠብመንጃ ፡ ከእኛ ፡ ዘንድ ፡ ስለአገኙት ፡ የእኛ ፡ አደረጉት ፡ እንጂ ፡ የእኛ ፡ ጠብመንጃ ፡ አልነበረም ፤ ጥፋተኞች ፡ አይደለንም ፡ ብለው ፡ በመከራከራቸው ፡ አቃቤ ፡ ሕግ ፡ ክሱን ፡ ለማስረዳት ፡ የሕግ ፡ ምስክሮች ፡ አቅርበው ፡ አሰምተዋል ።

ከአንደኛ ፡ ተከሳሽ ፡ በስተቀር ፡ ሁለተኛና ፡ ሦስተኛ ፡ ተከሳሾች ፡ የመከላከያ ፡ ምስክሮች ፡ አቅርበው ፡ አሰምተዋል ።

ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ምስክሮች ፡ ሰምቶ ፡ ነገሩ ፡ ለውሳኔ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ጥቅምት ፡ ፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፬ ፡ ዓ. ም. በዋለው ፡ ችሎት ፡ በወን/መዝ/ቁ. ፺፱/፷፪ ፡ በሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ፩ኛ ፡ ተከሳሽ ፡ ወራሲ ፡ ሁቁባጋብር ፡ ከአመለጡት ፡ ግብረ ፡ አበሮቹ ፡ ጋር ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ይዘው ፡ በበረሃ ፡ ሽፍተው ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ እያደፈጡ ፡ ተላላፊውን ፡ ሕዝብ ፡ ሲዘርፉ ፡ ከቆዩ ፡ በኋላ ፡ በመጨረሻው ፡ በዚሁ ፡ ዓይነት ፡ የዘረፋ ፡ ወንጀል፡ በሚፈጸምበት ፡ ጊዜ ፡ የ፻ አለቃ ፡ መኰንን ፡ መብራቱን ፡ በመተባተር ፡ መግደላቸው ፡ ስለተመሰከረባቸው፡ እ. አ. አ. በ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. ስለሽፍቶች ፡ በወጣው ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪. ፫. ፮. /፪. ፫./ እና ፡ እንዲሁም ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፭፻፳፪/፩ሀ/ መሠረት ፡ ጥፋተኛ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ በስቅላት ፡ እንዲሞት ፡ ፈርደዋል ።

፪ኛ ፡ ተከሳሽ ፡ ሕድሪንኪኤል ፡ ወልደኃይማኖት ፡ እና ፡ ፫ኛ ፡ ተከሳሽ ፡ ጊላይ ፡ ተወልደብርሃን ፡ ሁለቱ ፡ ከአንደኛ ፡ ተከሳሽ ፡ እና ፡ ካልተያዙ ፡ ግብረ ፡ አበሮቻቸው ፡ ጋር ፡ ሆነው ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ይዘው ፡ ከወንበ

ዱዎች ፡ ጋር ፡ በማበር ፡ የኃይል ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ አስበው ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ አድፍጠው ፡ መኪና ፡ አቁመው ፡ ለመዝረፍ ፡ ሲጠባበቁ ፡ ፖሊሶች ፡ ሲደርሱባቸው ፡ በፖሊሶች ፡ ላይ ፡ ተኩስ ፡ ከፍተው ፡ ሲተኩሱ ፡ ከነመሣሪያቸው ፡ የተያዙ ፡ መሆኑን ፡ ስለተመሰከረባቸው ፡ እ. አ. አ. በ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. ስለሽፍቶች ፡ የወጣውን ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፪ና. ፫. ስለተላለፉ ፡ ጥፋተኞች ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ በ፳ ፡ ዓመት ፡ ጽኑ ፡ እሥራት ፡ እንዲቀጡ ፡ ፈርደዋል ።

፫. ሦስቱ ፡ ተከሳሾች ፡ ይግባኝ ፡ ብለው ፡ አሁን ፡ በመመርመር ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ መዝገብ ፡ አስከፍተዋል ። ሁለተኛና ፡ ሦስተኛ ፡ ተከሳሾች ፡ ይግባኝ ፡ ያሉበት ፡ የጽሑፍ ፡ ማመልከቻ ፡ እንደሚገልጠው ፡ ቅጣቱ ፡ በዛብን ፡ በማለት ፡ ሲሆን ፡ እኛ ፡ ዘንድ ፡ ከቀረቡ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ክሱ ፡ ጥፋተኞች ፡ አይደለንም ፡ ብለው ፡ ተከራክረዋል ።

አንደኛ ፡ ተከሳሽ ፡ ግን ፡ በጠበቃው ፡ ባቀረበው ፡ ክርክር ፡ መሸፈቱን ፡ እና ፡ መዝረፉን ፡ አምኖ ፡ የመቶ ፡ አለቃ ፡ መኰንንን ፡ አልገደልኩምና ፡ ባልፈጸምኩት ፡ ወንጀል ፡ ልቀጣ ፡ አይገባም ፡ ከማለት ፡ በላይ ፤

፩ኛ እ. ኤ. አ. በ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. የወጣ ፡ የሽፍቶች ፡ አዋጅ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በመዝገብ ፡ ቁጥር ፡ ፫፻፬/፷፫ ሰኔ ፡ ፳፩ ቀን ፡ ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ. ም. በዋለው ፡ ችሎት ፡ በተሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ቀሪ ፡ ሆኖዋል ።

የበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በአዋጅ ፡ ቁ. ፪፻፷፪/፶፪ አንቀጽ ፡ ፲፩ ፡ መሠረት ፡ የበላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ውሣኔዎች ፡ መከተል ፡ እንዳለባቸው ፡ ተደንግጓል ።

፪ኛ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ ወራሲ ፡ ሁቀባጋብር ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ መቶ ፡ አለቃ ፡ መኰንን ፡ መብራቱን ፡ ገድለሃል ፡ ተብሎ ፡ በአንቀጽ ፡ ፭፻፳፪/፩/ሀ/ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ክቶ ፡ በእቃቤ ፡ ሕግ ሳይከሰስ ፡ ሳይወቀስ ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በአንቀጽ ፡ ፭፻፳፪/፩/ሀ/ ወ. መ. ሕግ ፡ ጥፋተኛ ፡ ነህ ፡ መባሉ ፡ ሳይገርመን ፡ አልቀረም ።

፫ኛ እ. ኤ. አ. በ፲፱፻፶፯ ፡ ስለሽፍቶች ፡ የወጣ ፡ አዋጅ ፡ አድርጎ ፡ ከመፍረድ ፡ በላይ ፡ ቀሪውን ፡ አንቀጽ ፡ ፩/፪. ፫./ ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ጥፋተኛ ፡ ነህ ፡ መባሉ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ እጅ ፡ ከፍንጅ ፡ በተያዘ ፡ ጊዜ ፡ በወታደሮቹ ፡ ላይ ፡ መተኩሱን ፡ ከመካዱም ፡ በላይ ፡ ስላልተመሰከረበት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ተከራክረዋል ።

፬. ዓቃቤ ፡ ሕግ ፡ ሲመልሱ ፡ በጠቅላላው ፡ ምስክሮችና ፡ አንዳንድ ፡ ጽሑፎች ፡ ቀርበው ፡ ሁኔታው ፡ እንደተረጋገጠ ፡ እንዲሁም ፡ አንደኛው ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ ጥፋተኛ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘበት ፡ እ. ኤ. አ. በ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. ስለሽፍቶች ፡ የወጣ ፡ አዋጅ ፡ ቁ. ፪. ፫. ፩/፪. ፫/ እና ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፭፻፳፪/፩/ የሞት ፡ ቅጣት ፡ ስለሚወስን ፡ እንዲሁም ፡ ፪ኛና ፡ ፫ኛ ፡ ጥፋተኞች ፡ ሆነው ፡ ተገኙበት ፡ የተባለው ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፪. ፫. ከአሥር ፡ ዓመት ፡ የማያንስ ፡ ቅጣት ፡ ስለመወሰን ፡ ሦስቱም ፡ ይግባኝ ፡ ባዮች ፡ የተወሰነባቸው ፡ ቅጣት ፡ ጸንቶ ፡ እንዲሰናበቱ ፡ በትሕትና ፡ አሳባችንን ፡ እናቀርባለን ፡ ብሎ ፡ ተከራክሯል ።

፭. <u>በሕግ ፡ ረገድ</u>—እኛ ፡ መዝገቡን ፡ መርምረን ፡ ክርክሩን ፡ ሰምተን ፡ እንደተረዳነው ፤

፩ኛ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በዓቃቤ ፡ ሕግ ፡ መጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ጥቅምት ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፪ ፡ ዓ. ም የቀረበ ፡ የክስ ፡ ማመልከቻ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፭፻፳፪/፩/ሀ/ ፡ የሚጠቅስ ፡ የነበረው ፡ ቀርቶ ፡ ክሱ ፡ ተሻሽሎ ፡ መጋቢት ፡ ፲፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፪ ፡ ዓ. ም. አዲስ ፡ ክስ ፡ መቅረቡን ፡ ዘንግቶ ፡ ፩ኛ ፡ ተከሳሽ ፡ በወ. መ. ሕግ ፡ ቁ. ፭፻፳፪/፩/ሀ/ ጥፋተኛ ፡ ነው ፡ ማለቱ ፡ የሕግ ፡ ስሕተት ፡ ነው ።

፪ኛ ፩ኛ ፡ ተከሳሽ ፡ እንዲሁም ፡ ሁለተኛና ፡ ሦስተኛ ፡ ተከሳሾች ፡ በተያዙበት ፡ ቀን ፡ በፖሊሶች ፡ ላይ ፡ ተኩስ ፡ ከፍተው ፡ ሲተኩሱ ፡ ከነመሣሪያቸው ፡ የተያዙ ፡ መሆኑ ፡ ተመስክሯል ፡ ካለና ፡ እ. ኤ. አ. በ፲፱፻፶፯ ፡ ስለሽፍቶች ፡ የወጣ ፡ አዋጅ ፡ እግብ ፡ ለመዋል ፡ ካሰበ ፡ በቁጥር ፡ ፩ ፡ መሠረት ፡ ጥፋተኞች ፡ ስለሆኑ ፡ ሦስቱ ፡ በሞት ፡ ፍርድ ፡ ሲቀጡ ፡ ይገባል ። ነገር ፡ ግን ፡ ዓቃቤ ፡ ሕጉም ፡ በቁጥር ፡ ፩ ፡ አልከሰሰም ፡ የከሰሰው ፡ በቁ. ፪ እና ፡ ፫ ነበር ፡ ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ ጥፋተኞች ፡ ሆኖ ፡ ተከሳሽ ፡ ቁ. ፪ እና ፡ ፫ ሲቀጣቸው ፡ ሕጉ ፡ ከ፲ ፡ ዓመት ፡ የማያንስ ፡ እያለ ፡ በ፳ ፡ ዓመት ፡ ብቻ ፡ እንዲቀጡ ፡ ፍርድ ፡ በመስጠቱ ፡ ከሕጉ ፡ ወጥተዋል ።
የሆነ ፡ ሆኖ ፤

ሀ/ አንደኛ ፡ ተከሳሽ ፡ ፫ ዓመት ፡ የሚያህል ፡ ሸፍቶ ፡ የሰላማዊ ፡ ሕዝብ ፡ ንብረት ፡ በመዝረፍ ፡ መኖሩን ፡ ከማመኑም ፡ በላይ ፡ ስለተመሰከረበት ፡ የመቶ ፡ አለቃ ፡ መኰንንን ፡ ግን ፡ አልገደልኩም ፡ ከማለቱም ፡ በላይ ፡ በምስክሮቹ ፡ የተረጋገጠ ፡ ሁኔታ ፡ አውቶቡሱ ፡ ሽፍቶቹ ፡ ካቆሙት ፡ በኋላ ፡ ተሳፋሪዎቹ ፡ እንዲወርዱ ፡ ተደርጎ ፡ አንደኛ ፡ ተከሳሽ ፡ አውቶቡሱን ፡ ፈትሾ ፡ ሲወርድ ፡ የመቶ ፡ አለቃ ፡ መኰንን ፡ ከአውቶቡሱ በር ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡ ነበር ፡ እና ፡ ከተከሳሽ ፡ ጋር ፡ ተያያዙ ፡ እንደታያያዙ ፡ የመቶ ፡ አለቃ ፡ መኰንን ፡ ተከሳሹን ፡ በበትር ፡ እየመቱ ፡ እርዱን ፡ ይሉ ፡ ነበር ። የተከሳሹ ፡ ጠብመንጃ ፡ ወድቆ ፡ ነበር ፡ አንድ ፡ መምህር ፡ ጸሐየና ፡ አንድ ፡ የኮማንድስ ፡ ወታደር ፡ ጠብመንጃቸውን ፡ ሊተኩሱ ፡ ሞክሮ ፡ እምቢ ፡ ስላላቸው ፡ ይዘውት ፡ ሸሹ ፡ ከተከሳሹ ፡ ጓደኞች ፡ አንዱ ፡ የመቶ ፡ አለቃ ፡ መኰንንን ፡ በጥይት ፡ ወግቶ ፡

ገደላቸው ። አራቱ ፡ ወንበዴዎች ፡ የተወሰደውን ፡ የተከሳሽ ፡ ጠብመንጃ ፡ ለመመለስ ፡ በሩጫ ፡ ሄደው ፡ ጠብመንጃውን፣ ይዘው ፡ ከተመለሱ ፡ በኋላ ፡ ተከሳሽ ፡ የያዘኝ ፡ ይሄ ፡ ነው፣” ብሎ ፡ የሚቼን ፡ ሬሳ ፡ እንደወደቀ—ድንጋይ ፡ አንስቶ ፡ ከግምባሩ ፡ ላይ ፡ መታውና ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የዘረፉትን ፡ ሃብት ፡ ይዘው ፡ ሸሽተው ፡ ሄዱ ፡ የሚል ፡ ነው ።

ለ/ ሁለተኛና ፡ ሦስተኛ ፡ ተከሳሾች ፡ አንዱ ፡ ፲፩ ፡ ቀኖች ፡ ሌላው ፡ ደግሞ ፡ ፯ ፡ ቀኖች ፡ መሸፈታቸውን ፡ ባያምኑም ፡ በዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ በቀረበ ፡ ማስረጃ ፡ እጅ ፡ ከፍንጅ ፡ በተያዙበት ፡ ጊዜ ፡ ሁለተኛ ፡ ተከሳሽ ፡ ከጠመንጃውና ፡ ጥይቱ—ሦስተኛ ፡ ተከሳሽ ፡ ደግሞ ፡ የእጅ ፡ ቦምብና ፡ ጩቤ ፡ ይዘው ፡ ከመገኘታቸው ፡ በላይ ፡ ወንበዴዎች ፡ መሆናቸውን ፡ ለያዙዋቸው ፡ ወታደሮች ፡ እንዳመኑላቸው ፡ ተመስክሯል ፡ በወታደሮቹ ፡ ላይ ፡ መተኰሳቸው ፡ ግን ፡ ምንም ፡ አልተመሰከረም ። ስለ ፡ አንደኛው ፡ ተከሳሽም ፡ ሲያዝ ፡ መተኰሱ ፡ አልተመሰከረበትም ።

ሐ/ እ. ኤ. አ. በ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. የወጣ ፡ ስለ ፡ ሽፍቶች ፡ አዋጅ ፡ ለጊዜው ፡ የወጣ ፡ አዋጅ ፡ ነበር ። የታወጀው ፡ በፌዴሬሽን ፡ አስተዳደር ፡ ጊዜ ፡ ነበር ። አሁን ፡ በሞላው ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሚሠራበት ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ሽፍቶችም ፡ በቁ. ፭፻፳፪ ፡ የተደነገገው ፡ መኖሩ ፡ የማይካድ ፡ ነው ። እ. ኤ. አ. በ፲፱፻፶፯ ፡ የወጣ ፡ ስለሽፍቶች ፡ አዋጅ ፡ በቁ. ፪ እና ፡ ፫ መሠረት ፡ እንደ ፡ ሁለተኛና ፡ ሦስተኛ ፡ ተከሳሾች ፡ ቢያንስ ፡ በአሥር ፡ ዓመት ፡ ቅጣት ፡ እንዲቀጡ ፡ በቀጥታ ፡ ሲደነግግ ፡ በቁ. ፩ እንደ ፡ አንደኛ ፡ ተከሳሽ ፡ ያለ ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ ምርጫ ፡ ዳኞች ፡ ቅር ፡ ያላቸውም ፡ ቢሆን ፡ ለሞት ፡ እንዲፈረድ ፡ ይደነግጋል ።

መ/ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ በቁ. ፴፯ “ማንም ፡ ሰው ፡ በሕግ ፡ እኩል ፡ ሆኖ ፡ ይጠበቃል” ብሎ ፡ በቁ. ፴፰ “በብሔራዊ (ሲቪል) መብቶች ፡ ረገድ ፡ በኢትዮጵያዊያን ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ አይደረግም” ይላል ። ቀጥሎም ፡ በቁ. ፶፬ ፡ ቅጣት ፡ የሚፈጸመው ፡ በአጥፊው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ብቻ፣ ነው” ብሎ ፡ በቁ. ፻፳፪ ፡ “ይህ ፡ የተሻሻለው ፡ ሕግ ፡ መንግሥት ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ ይሆናል ። ወደፊትም ፡ የሚሠሩ ፡ ሕጎች ፡ ድንጋጌዎች ፡ ፍርዶች ፡ ውሳኔዎች ፡ ሁሉ ፡ ከዚህ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ጋር ፡ የማይስማሙ ፡ ሲሆኑ ፡ ዋጋ ፡ የሌላቸውና ፡ የማያገለግሉ ፡ ይሆናሉ” ይላል ።

ስለዚህ ፡ ተከሳሽ ፡ ቁ. ፩ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ በሽፍትነት ፡ መኖሩን ፡ የዝርፊያና ፡ የግፍ ፡ ወንጀል ፡ መፈጸሙ ፡ የሰው ፡ ሕይወት ፡ ግን ፡ አለማሳለፉን ፡ መዝገቡን ፡ መርምረን ፡ ስለተረዳን ፤

እንዲሁም ፡ ተከሳሾች ፡ ቁ. ፪ እና ፡ ፫ አንዱ ፡ ለ፲፩ ፡ ቀኖች ፡ አንዱ ፡ ደግሞ ፡ ለ፯ ፡ ቀኖች ፡ መሸፈታቸውን ፡ ከመዝገቡ ፡ ስላወቅን ፡ ተግባራቸው ፡ እ. ኤ. አ. በ፲፱፻፶፯ ፡ ስለሽፍቶች ፡ በወጣ ፡ አዋጅ ፡ ከማየት ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ማየቱን ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ መሠረት ፡ ሕጋዊና ፡ ፍትሐዊ ፡ ሆኖ ፡ ስለታየን ፡ እላይ ፡ በተዘረዘረው ፡ ምክንያት ፡ ሁሉ ፡ የሚከተለውን ፡ የፍርድ ፡ ውሣኔ ፡ሰጥተናል ።

. በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፭፻፳፪ ፡ ቁ. ፩/ሀ/ ይግባኝ ፡ ባዮች ፡ ቁ. ፪ እና ፡ ፫ ጥፋተኞች ፡ ናቸው ፡ ብለን ፡ በአምስት ፡ ዓመት ፡ እሥራት ፡ አጽንተናል ።

በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፭፻፳፪ ፡ ቁ. ፪ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ ቁ. ፩ ጥፋተኛ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ የዕድሜ ፡ ልክ ፡ ጽኑ ፡ እሥራት ፡ እንዲቀጣ ፡ ፈርደናል ።

ይህ ፡ ፍርድ ፡ ዛሬ ፡ መጋቢት ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፬ ፡ ዓ. ም. በድምጽ ፡ ብልጫ ፡ በግልጽ ፡ ችሎት ፡ ተሰጥቷል ።

ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የሚጻፈው ፡ በአነስተኛ ፡ ድምጽ ፡ [በአቶ ፡ በርሄ ፡] የተሰጠ ፡ አስተያየት ፡ ነው ።

ከፈረዱት ፡ ዳኞች ፡ የተለየሁበትና ፡ ያልተስማማሁበት ፡ ምክንያት ፡ ይግባኝ ፡ ባዮች ፡ ጥፋተኞች ፡ ተብለው ፡ ሊቀጡበት ፡ የሚገባ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ባቀረበው ፡ ክስና ፡ ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤትም ፡ ክሱን ፡ ተቀብሎ ፡ የወሰነባቸውን ፡ ቅጣት ፡ አልተሳሳተም ፡ በማለት ፡ ሲሆን ።

በድምጽ ፡ ብልጫ ፡ የፈረዱት ፡ ዳኞች ፡ ግን ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ሦስቱን ፡ ይግባኝ ፡ ባዮች ፡ በበረሐ ፡ ሆነው፣ የወንበዴነት ፡ ሥራ ፡ መፈጸማቸው ፡ ቢታወቅም ፡ ክሱ ፡ ለወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ እንጂ ፡ እ. ኤ. አ. በ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. በወጣው ፡ የሽፍቶች ፡ አዋጅ ፡ ሊሆን ፡ አይገባም ፡ በማለት ፡ በዓቃቤ ፡ ሕግ ፡ የቀረበ ፡ ክስና፣ ከፍ/ቤት ፡ ክሱን ፡ ተቀብሎ ፡ ወንጀል ፡ መፈጸማቸውን ፡ ካረጋገጠ ፡ በኋላ ፡ ፩ኛ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ በስቅላት ፡ በሞት ፡ እንዲቀጣ ፡ የፈረደው ፡ በዕድሜው ፡ ልክ ፡ እሥራት ፡ ለውጠ ፡ ፪ኛና፣ ፫ኛ ፡ ይግባኝ ፡ ባዮች ፡ ግን ፡ ቅጣታቸውን ፡ አጽንቶ ፡ ከሽፍትነት ፡ አዋጅ ፡ አንቀጽ ፡ ፪ና. ፫. በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፭፻፳፪፡ በመለወጣቸውና ፡ ስለሽፍቶች ፡ የወጣ ፡ አዋጅ ፡ ሊጠቀስ ፡ አይገባውም ፡ በማለታቸው ፡ ነው ።

<u>የነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ ባጭሩ ፡</u>

በክሱ ፡ ማመልከቻ ፡ ላይ ፡ እንደተዘረዘረውና ፡ አሁንም ፡ በድምጽ ፡ ብልጫ ፡ የፈረዱ ፡ ዳኞች ፡ እንደዘረዘሩት ፡ ይግባኝ ፡ ባዮቹ ፡ በከፍ/ፍ/ቤት ፡ ተከሰው ፡ እንደቀረቡ ፡ ፍ/ቤት ፡ ጥቅምት ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፪ ፡

ዓ. ም. ዓቃቤ ፡ ሕጉ ፡ በይግባኝ ፡ ባዮች ፡ ላይ ፡ ያቀረበውን ፡ ክስ ፡ ከአንድ ፡ ተራ ፡ ቁጥር ፡ እስከ ፡ አምስተኛው ፡ ቁጥር ፡ እ. ኤ. አ. ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ.ም. ስለሸፍቶች ፡ የወጣውን፡ አዋጅ ፡ ተላልፈዋል ፡ በማለት ፡ ሲሆን ፡ በ፯ኛ ፡ ተራ ፡ ቁጥር ፡ ግን ፡ ፩ኛን ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ ብቻ ፡ የሚመለከት ፡ ሲሆን ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ተ/ቁጥር ፡ ፭፻፳፪.(፩.)ሀ. በግፍ ፡ ሰውን ፡ መግደል ፡ የሚል ፡ ጨምሮበት ፡ ስለነበር ፡ ይህንኑ ፡ ፯ኛ ፡ ክስ ፡ ሰርዞ፡ ክሱን  ስለሸፍቶች ፡ ተብሎ ፡ በወጣው ፡ አዋጅ ፡ ብቻ ፡ ሆኖና ፡ ተሻሽሎ፡ እንዲያቀርበው ፡ አዞታል ። በዚሁ ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረትም ፡ ዓቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ክሱን ፡ አሻሽሎ ፡ መጋቢት ፡ ፲፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፱ ፡ ዓ. ም. ባቀረበው ፡ ጉዳዩ ፡ ወደ ፡ ማስረጃዎቹን ፡ መስማት ፡ ቀጠለ ፡ በመጨረሻም ፡ ለጉዳዩ ፡ ውሳኔ ፡ ሲሰጥ ፡ ሰኔ ፡ ፲፩ ፡ ቀን ፡ የተሻሻለውን ፡ ክስ ፡ ዘንግተን ፡ ያው ፡ በጥቅምት ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ በመጀመሪያው ፡ ጊዜ ፡ ቀርቦ ፡ የነበረውን ፡ ክስ ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ ሁሉንም ፡ ጥፋተኞች ፡ ሆነው፡ አግኝቶ ፡ ፩ኛው፡ ይግባኝ፡ ባይ ፡ ሦስት፡ ዓመት ፡ ሙሉ፡ ሽፍታ፡ ሆኖ ፡ በዱርና ፡ በገደል ፡ ሰፍሮ ፡ ገና ፡ ካልተያዙት ፡ ግብረ ፡ አበሮቹ ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡ የጋራ ፡ ዓላማቸው ፡ ማናቸውንም ፡ የኃይል ፡ ሥራ ፡ ወንጀል ፡ ለመፈጸም ፡ ተስማምተው ፡ በልዩ ፡ ልዩ፡ ቦታዎች ፡ እየሄዱ ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ሰዎችና ፡ ከመጓጓዣ ፡ መኪናዎች ፡ እንዲሁም ፡ አውቶቡሶችን ፡ እያቆሙ ፡ የዝርፊያ ፡ ወንጀል ፡ መፈጸሙ ፡ ከመረጋገጡ ፡ በላይ ፡ ሐምሌ ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፩ ፡ ዓ. ም. ከአሥመራ ፡ ወደ ፡ ከረን ፡ የሚወስደው ፡ አውራ ፡ ጐዳና ፡ በኪሎ ፡ ሜትር ፡ ፶፰ ላይ ፡ አንዲት ፡ የሰውን ፡ መጓጓዣ ፡ አውቶቡስ ፡ አቁመው ፡ ተሳፋሪዎቹን ፡ እንዲወርዱ ፡ አስገድዶ ፡ ከተጓዦዎች ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ የፖሊስ ፡ መቶ ፡ አለቃ ፡ መኰንን ፡ መብራቱ ፡ የተባለው ፡ የሲቪል ፡ ልብስ ፡ ለብሶ ፡ ይገኝ ፡ ስለነበር ፡ ሽጉጤን ፡ አሳልፌ ፡ አልሰጥህም ፡ በማለት ፡ ከ፩ኛ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ ሲታገል ፡ እንዳያይልበት ፡ ለሸፍቶቹ ጓደኞቹ ፡ እርዱኝ ፡ ብሎ ፡ ጨኸቱን ፡ ካሰማ ፡ ከወረበሎቹ ፡ አንዱ ፡ ተኩሶ · የተጠቀሰውን ፡ መቶ፡ አለቃ ፡ አቁስሎ ፡ እንደገደለው ፡ አሁንም፡ ፩ኛው ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ ትልቅ ፡ ደንጋይ ፡ አንስቶ ፡ በሟቹ ፡ ጭንቅላት ፡ ላይ ፡ ወርውሮ ፡ ሰብአዊ ፡ ርኅራኄ ፡ በሌለው ፡ በእንስሳዊ ፡ ጭካኔ ፡ ዓይነት ፡ ጨፍልቆትና ፡ የዘረፈውን ፡ ንብረት ፡ ይዞ ፡ በመሄዱ ፡ ተመስክሮበታል ፡ ብሎ ፡ በሞት ፡ እንዲቀጣ ፡ ፈርዶበታል ። ፪ኛና ፡ ፫ኛ ፡ ይግባኝ፡ባዮች፡ግን፡በተጠቀሰው፡አዋጅ፡ መሠረት ፡ በአንቀጽ፡ ፪ና ፫. ጥፋተኞች ፡ ሆነው ፡ አግኝቶ ፡ በአምስት ፡ በአምስት ፡ ዓመት ፡ እሥራት ፡ እንዲቀጡ ፡ ፈርዶ ፡ አሰናብቶአቸዋል ።

አሁን ፡ በዚሁ ፡ ጠቅላይ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት  በይግባኝ ፡ ቀርበው ፡ የተከራከሩት ፡ በጽሑፍ ፡ ሰፍሮ ፡ ስለሚገኝ ፡ መመልከት ፡ ይበቃል ፡ አተኩሮ ፡ መመልከት ፡ የሚያስፈልገው ፡ በድምጽ ፡ ብልጫ፡ የፈረዱት ፡ ዳኞች ፡ በ፩ኛ ፡ ይግባኝ፡ ባይ ፡ ጠበቃ ፡ የቀረበውን ፡ ክርክር ፡ ተቀብለው ፡ ጥፋተኞች ፡ ተብለው ፡ የተገኙበትን ፡ ስለሽፍቶች፡ የወጣ፡ አዋጅ ፡ ሽሮ ፡ በወንጀለኛ፡ መቅጫ ፡ ሕግ፡ ለውጦ፡ ቅጣቱን ፡ ከሞት፡ ወደ፡ ዕድሜህ ፡ ይፍታህ ፡ የለወጠውን ፡ ምክንያትና ፡ አተታው ፡ ነው ።

ክቡራን ፡ ዳኞች ፡ የሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፴፯ ፡ እና ፡ ፴፰ ፡ ጠቅሰው፡ "ማንም ፡ ሰው፡ በሕግ ፡ እኩል ፡ ሆኖ ፡ ይጠበቃል ፡ በብሔራዊ ፡ መብቶችን ፡ በኢትዮጵያዊያን ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ አይደረግም ፡" ይላል ፡ ቀጥሎም ፡ ቁ. ፶፬ ፡ "ቅጣት ፡ የሚፈጸመው ፡ በአጥፊው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው" ብሎ ፡ በቁ.፻፳፪ ይህ ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ ይሆናል ፡ ወደፊትም ፡ የሚሠሩ ፡ ሕጎች ፡ ድንጋጌዎች፡ ፍርዶች፡ ውሣኔዎች ፡ ሁሉ ፡ ከዚህ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ጋር ፡ የማይስማሙ ፡ ሲሆኑ ፡ ዋጋ ፡ የሌላቸውና ፡ የማያገለግሉ ፡ ይሆናሉ ፡ ይላል ፡ በማለት ፡ ጠቅሰው ፡ ፩ኛ ፡ ይግባኝ፡ ባይ ፡ ሦስት፡ ዓመት ፡ በሽፍትነት ፡ መኖሩን ፡ የዝርፊያና ፡ የግፍ ፡ ወንጀል ፡ መፈጸሙን ፡ እንዲሁ ፡ የሰውን ፡ ሕይወት ፡ ግን፡ አለማሳለፉን ፡ መዝገቡን ፡ መርምረን ፡ ስለተረዳን ፤ እንዲሁም፡ ፪ኛና. ፫ኛ ፡ ተከሳሾች ፡ አንዱ  ለ፲፩ ፡ ቀኖች ፡ አንዱ ፡ ለ፯ ፡ ቀኖች ፡ መሸፈታቸው ፡ ከመዝገቡ ፡ ስላወቅን ፡ ተግባራቸው ፡ እ. ኤ. አ. በ፲፱፻፶፯ ዓ. ም. ስለሽፍቶች ፡ በወጣ ፡ አዋጅ ፡ ከማየት ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ማየት ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ መሠረት ፡ ሕጋዊና፡ ፍትሐዊ ፡ ሆኖ ፡ ስለታየን ፡ በማለት ፡ ወ/መ/ሕግ ፡ ቁ. ፭፻፴፪.(፩.)ሀ. ይግባኝ ፡ ባዮች ፡ ፪ኛና ፡ ፫ኛ ጥፋተኞች ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ በ፭ ፡ ዓመት ፡ እሥራት ፡ እንዲቀጡ ፡ በወ/መ/ቁ. ፭፻፴፪/፪/ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ ቁ. ፩ ጥፋተኛ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ በዕድሜ ፡ ልክ ፡ ጽኑ ፡ እሥራት ፡ እንዲቀጣ ፡ ፈርደናል ፡ በማለታቸው ፡ ውሳኔ ፡ ሰጥተዋል ።

ክቡራን ፡ ዳኞች ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ቁ. ፴፯. ፴፰. ፶፬ እና ፡ ፻፳፪ን ፡ ጠቀሷዋቸው ፡ እንጂ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ ፍርዱን ፡ የሰጠው ፡ ከፍ/ፍ/ቤት ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ተላልፎ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ በተግባር ፡ ይህንና ፡ ይህን ፡ ፈጽመዋል ፡ አላሉም ። በዐቃቤ ፡ ሕግ፡ የቀረበው ፡ የክሱ፡ ማመልከቻ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ ከፍ/ፍ ቤት ፡ የሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ በአድሎ ፡ ወይም ፡ የተከሳሾቹን ፡ መብት ፡ በመንካት ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ በፈጸመው ፡ ወንጀል ፡ ተከሳሾች ፡ ተቀጥተው ፡ እንደሆን ፡ ለማለት ፡ ፈጽመዋል ፡ ወይም ፡ ተደርጓዋል ፡ አላሉም ፡ ስለዚህ ፡ የሕጉን ፡ አንቀጽ ፡ ብቻ ፡ መጥቀስ ፡ ማናቸውም ፡ ውጤት ፡ ሊያገኝ ፡ አይችልም ፡ ባይ ፡ ነኝ ።

በእውነቱ ፡ የሽፍቶች ፡ አዋጅ ፡ እንዴት ፡ እንደታወጀና ፡ ምክንያቱንና ፡ ጊዜውም ፡ ለማወቅ ፡ የተፈለገ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ አዋጁ ፡ የተደነገገው ፡ እንደ ፡ አውሮፓ ፡ አቆጣጠር ፡ በ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. ሲሆን ፡ ምክንያቱም ፡ ኤርትራ ፡ በፌዴሬሽን ፡ ትተዳደር ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የኤርትራ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ እየተባለ ፡ ይጠራ ፡ የነበረውን ፡ የድሮ ፡ የኢጣሊያን ፡ ወ/መ/ ፡ ሕግ ፡ በሙሉ ፡ ይሠራበት ፡ እንደነበረና ፡ በዚሁ ፡ ሕግ ፡ የሚወሰን ፡ ቅጣት ፡ ላሁኑ ፡ የኢትዮጵያችን ፡ የወንጀለኛ  ፡ መ/ ሕግ  ፡ ተመሳሳይ ፡ ቢሆን ፡ በኤርትራ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ በበረሃና ፡ በዱር ፡ ገደሉ ፡ ተሰማርተው ፡ የሽፍትነት ፡ ማሕበር ፡ እያቋቋሙ ፡ በሕዝብና ፡ በንብረቱ ፡ ላይ ፡ ከባድ ፡ ሽብርና ፡ ጉዳት ፡ በመፈጸማቸው ፡ አገሪቱን ፡ በማወካቸው ፡ በጸጥታ ፡ አስከባሪ፡ ፖሊስ፡ ታድነው፡ ተይዘው፡ በጠቀስኩት፡ የወንጀለኛ፡ መቀጫ፡ ሕግ፡ ቁ. ፭፻፷፰ ፡ ልክ፡እንዲሆን፡ወ/መ/ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፭፻፴፪ ፡(፩.) (፪.)ሀ. የሚያዘው፡ ቅጣት ፡ በሆነው፡ አንቀጽ፡ ተከሰው ፡ ፍ/ቤት ፡ ከቀረቡ ፡ በኋላ ፡ ጥፋተኞች፡ሆነው፡ ተገኝተው ፡ የሚወሰንባቸውን፡ ቅጣት፡ አብዛኛውን፡ የእሥራት፡ በመሆኑ፡ምንም፡የጠቅላይ ፡

ግዛቱን ፡ ሕዝብ ፡ ጸጥታና ፡ ሰላም ፡ ለማግኘት ፡ ካለመቻሉ ፡ በላይም ፡ የአገሪቱ ፡ ኤኮኖሚዋም ፡ ስለተጐዳ ባትና ፡ ችግሩን ፡ ሁሉ ፡ በመመልከት ፡ የኤርትራ ፡ ቺፍ ፡ ኤግዚኩቲቭ ፡ ለጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ የሕግ ፡ መምሪያ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ የአዋጁን ፡ ረቂቅ ፡ አቅርበውና ፡ ም/ቤቱ ፡ አጥንቶ ፡ ከተስማማበት ፡ የጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ ሕግ ፡ "ኮንስቲቱዊሽን" አንቀጽ ፡ ፲፩ ፡ በሚፈቅደው ፡ መሠረት ፡ በመጥቀስና ፡ አንቀጽ ፡ ፲፰ ፡ መሠረት ፡ አድር ገው ፡ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ስለአጸደቁት ፡ እ. ኤ. አ. ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. የሽፍቶች ፡ አዋጅ ፡ ተብሎ ፡ በመሠየም ፡ ከ፭ ፡ ዓመት ፡ እሥራት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዕድሜ ልክና ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ የሚወሰን ፡ በመሆኑ ፡ በየጊዜው ፡ ተይዘው ፡ በፍ/ቤት ፡ የሚቀርቡ ፡ ሽፍቶች ፡ እንደየዓይነቱ ፡ ገበናቸው ፡ በፍ/ቤት ፡ ቀርበው ፡ ጥፋተኞች ፡ ሆነው ፡ ከተገኙ ፡ በዚሁ ፡ እየተቀጡ ፡ ቆይተዋል ።

ኤርትራ ፡ በፌደሬሽን ፡ መተዳደርዋ ፡ ቀርቶ ፡ ከእናት ፡ አገርዋ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በፍጹም ፡ ከተወሀደችም ፡ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ አውጀው ፡ በቁጥር ፡ ሦስት ፡ ሀያሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ ኅዳር ፡ ፮ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፭ ፡ ዓ. ም. በትእዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፳፯/፶፭ ፡ በተራ ፡ ቁጥር ፡ ስድስት ፡ የተደነገገው ፡ እንደሚከተለው ፡ ስለሚ ያዝዝ ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ ጸንቶው ፡ የሚሠራባቸው ፡ ወይም ፡ የፌደራል ፡ አቋም ፡ በመኖሩ ፡ ምክንያት ፡ የወጡት ፡ ሕጎች ፡ አዋጆችና ፡ ደንቦች ፡ በሙሉም ፡ ሆነ ፡ በክፊል ፡ ለአስተዳደር ፡ አስፈላጊ ፡ ሆነው ፡ እንዲሠራባቸው ፡ የማያስፈልጉት ፡ ሁሉ ፡ ወደፊት ፡ በሚወጡ ፡ ሕጎች ፡ ተሠርዘው ፡ እስኪተኩ ፡ ድረስ ፡ እንዳሉ ፡ ጸንተው ፡ የሚሠራባቸው ፡ ይሆናሉ ፡ በማለት ፡ ከታወጀ ፡ በኋላም ፡ ይሄው ፡ አዋጁ ፡ በሙሉ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ በመዋል ፡ ይገኛል ።

እርግጥ ፡ ነው ፡ በ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. እንዳሁኑ ፡ ጉዳይ ፡ የጠቅላይ ፡ ፍ/ቤት ፡ ዳኞች ፡ በሃሳብ ፡ ተለያይተው ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የድምጽ ፡ ብልጫውን ፡ ውሳኔ ፡ የሽፍቶችን ፡ አዋጅ ፡ ተቀባይነት ፡ አለው ፡ የሚል ፡ ስለነ በረና ፡ በኋላም ፡ ም/አፈንጉሥም ፡ ያሉበት ፡ ችሎት ፡ በሙሉ ድምጽ ፡ ስላጸናው ፡ የሽፍትነት ወንጀል ፡ የፈጸሙ ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ አዋጅ ፡ ይከሰሳሉ ። ባለፈው ፡ ዓመት ፡ ምሕረትም ፡ በሽፍቶች ፡ አዋጅ ፡ ተከሰው ፡ የተፈረደባቸው ፡ ወንጀለኞች ፡ በይግባኝ ፡ ከቀረቡ ፡ በኋላ ፡ አዋጁን ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ለውጦ ፡ ቅጣታቸውን ፡ አጽንተዋል ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ከዚህ ፡ በኋላም ፡ ሌላው ፡ የጠቅላይ ፡ ፍ/ቤት ፡ ችሎት ፡ የሽፍቶች ፡ አዋጅን ፡ በማጽናት ፡ ውሳኔ ፡ ሰጥተዋልና ፡ ከፍ/ፍ/ቤት ፡ በአሁኑ ፡ ይግባኝ ፡ ባዮች ፡ ላይ ፡ የቀረበው ፡ በ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. የወጣው ፡ የሽፍቶች ፡ አዋጅ ፡ ተቀብሎ ፡ የወሰነው ፡ ቅጣት ፡ በሚገባ ፡ ስለሆነ ፡ ለሰጠው ፡ ፍርድ ፡ አዋጅ ፡ ቁ. ፲፱፩/፶፰ ተላልፏል ፡ ማለት ፡ አይቻልም ፡ እርግጥ ፡ ከፍ/ፍ/ቤት ፡ አንድ ፡ የዘነጋው ፡ ነገር ፡ አለ ፡ እሱም ፡ ያው ፡ በመ ጋቢት ፡ ፲፭ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፪ ፡ ዓ. ም. ተሻሽሎ ፡ የቀረበውን ፡ የሽፍቶች ፡ አዋጅ ፡ በተከሰሱበት ፡ የጥፋተኝነ ትና ፡ ፍርዱን ፡ ከመስጠት ፡ ፊንታ ፡ የቀድሞውን ፡ ጥቅምት ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፪ ፡ ዓ. ም. የቀረበው ፡ ክስ ፡ የሽፍቶች ፡ አዋጅና ፡ የወንጀለኛ ፡ መ/ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፭፻፳፪(፩)ሀ. ጠቅሶ ፡ በመፍረዱ ፡ ነው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ንን ፡ በመዘንጋት ፡ ለ፩ኛ ፡ ተከሳሽ ፡ የሚያከብድለት ፡ ነገር ፡ ፈጽሞ ፡ የለውም ፡ ምክንያቱም ፡ በሰኔ ፡ ፲፭ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፪ ፡ ዓ. ም. ተሻሽሎ ፡ የቀረበ ፡ የክሱ ፡ ማመልከቻ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነም ፡ በ፩ኛው ፡ ክስ ፡ ተዘር ዝሮ ፡ የተመለከተውን ፡ እንደሚገልጸው ፡ ፩ኛው ፡ ተከሳሽ ፡ ብቻ ፡ ብሎ ፡ እ. ኤ. አ. በ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. ስለሽ ፍቶች ፡ የወጣው ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፪. ፫. ፩. (፪. ፫.) የተመለከተውን ፡ በመተላለፍ ፡ ፩ኛው ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ ሐምሌ ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፩ ፡ ዓ. ም. የፈጸመውንና ፡ በማስረጃ ፡ የተረጋገጠው ፡ ወንጀል ፡ ሲሆን ፡ የመቶ ፡ አለቃ ፡ መኰንን ፡ መብራሀቱን ፡ ሞት ፡ የሚመለከት ፡ ክስ ፡ ስለሆነ ፡ እና ፡ በዚሁ ፡ ክስ ፡ ጥፋተኛ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘው ፡ ወንጀለኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶቹ ፡ የሞት ፡ ቅጣት ፡ ከመፍረድ ፡ ሌላ ፡ ምርጫ ፡ ስለሌላቸው ፡ በዚሁ ፡ ክስ ፡ ነው ፡ ሞት ፡ የተፈረደበትና ፡ አሁንም ፡ ስህተት ፡ አልፈጸመም ፡ ባይ ፡ ነኝ ። ስለ ፡ ፪ኛ ፡ እና ፡ ፫ኛ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በአምስት ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ብቻ ፡ ቢቀጡም ፡ አንሷል ፡ ብሎ ፡ ይግባኝ ፡ ማለት ፡ ያለበት ፡ የዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ጽ/ቤት ፡ ነው ፡ ባይሉም ፡ ያው ፡ አነስተኛ ፡ ቅጣት ፡ ከማጽደቅ ፡ ሌላ ፡ ምርጫ ፡ ልንሰጥ ፡ አይፈቀድም ።

ስለዚህ ፡ እላይ ፡ በማብራራት ፡ የገለጽኩት ፡ ምክንያት ፡ እና ፡ በአሳብ ፡ የተለየሁበት ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ስገልጽ ፡ እንደዚሁ ፡ የመሰለ ፡ ክርክርና ፡ የሐሳብ ፡ ልዩነት ፡ አንድ መፍትሄ ፡ ያገኝ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ክቡር ፡ ምክትል ፡ አፈንጉሥ ፡ መዝገቡ ፡ ተላልፎ ፡ አከራካሪውን ፡ ነገር ፡ ተመልክተው ፡ ጉዳዩ ፡ አንድ ፡ የመንግሥት ፡ አዋጅ ፡ የሚነካ ፡ በመሆኑ ፡ ከበላይ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ቢመካከሩበት ፡ ቀና ፡ መንገድ ፡ ሆኖ ፡ ታይቶኛል ።

የኢትዮጵያ ፤ ንጉሠ ፤ ነገሥት ፤ መንግሥት ፤
በኤርትራ ፤ ከፍተኛ ፤ ፍርድ ፤ ቤት ፤

አሥመራ ።

ዳኞች ፤—

አቶ ፤ ማሕሙድ ፤ ኑርሑሴን ፤
” ግርማይ ፤ ካሣ ፤

ከሳሽ ፤ ዓቃቤ ፤ ሕግ ፤
ተከሳሾች ፤ እነ ፤ ገብረዝጊ ፤ ገብረሙሴ ፤

የወ/ መዝ/ ቁ. ፷፩/ ፷፬
ሰኔ ፤ ፳፰ ፤ ቀን ፤ ፲፱፻፷፬ ፤ ዓ. ም.

## ፍርድ ።

ይግባኝ ፤ ባዮች ፤ ሰብሣ ፤ የተባለች ፤ መንደር ፤ የመራጉዝ ፤ ወረዳ ፤ ግዛት ፤ ባላባቶችና ፤ የመንደሪቷ ፤ ሽማግሌዎች ፤ ናቸው ።

በሠራው ፤ የተባለ ፤ ቦታ ፤ የመንደሪትዋ ፤ የርስት ፤ ክልል ፤ የሚገኝ ፤ ማሣ ፤ የግል ፤ ከሳሽ ፤ ገብረሚካኤል ፤ ገብረአብ ፤ ለጥቅምት ፤ ፲፬ ፤ ቀን ፤ ፲፱፻፷፬ ፤ ዓ. ም. የሚያነጋ ፤ ሌሊት ፤ ሰዓቱ ፤ ባልታወቀ ፤ ጊዜ ፤ ባልታወቁ ፤ ወንጀል ፤ ሰሪዎች ፤ ጤፍ ፤ ተዘርቶ ፤ ለማጨድ ፤ የደረሰ ፤ በሌሊት ፤ ታጭዶ ፤ ስለተወሰደ ፤ የታጨደ ፤ ማሣ ፤ ጤፉን ፤ በአዋቂ ፤ ተገምቶ ፤ ዋጋው ፤ ፪፻፴፩ ፤ ብር ፤ መሆኑ ፤ ስለተረጋገጠ ፤ አዋጁ ፤ የሚያዘው ፤ ይግባኝ ፤ ባዮች ፤ የመንደሪትዋ ፤ ሽማግሌ ፤ መሆናቸውን ፤ በማወቅ ፤ ፲፭ ፤ ቀን ፤ ጊዜ ፤ ከባለሥልጣኖች ፤ ተሰጥቷቸው፤ ፈልገው ፤ ጥፋተኞቹን ፤ ስላላቀረቡ ፤ በተራ ፤ ቁጥር ፤ ፪—፫. በ፲፱፻፳፫ ፤ ዓ. ም. በኤርትራ ፤ ጠቅላይ ፤ አስተዳደር ፤ የወጣ ፤ አዋጅ ፤ ቁ. ፲. በመተላለፍ ፤ በአባሪ ፤ አላፊነት ፤ ኮሌክቲቭ ፤ ሊያቢሊቲ ፤ አክት ፤ በሠራየ ፤ አውራጃ ፤ ግዛት ፤ ተከሰው ፤ ቀርበው ፤ ነበር ።

ይግባኝ ፤ ባዮች ፤ እፍርድ ፤ ቤቱ ፤ ቀርበው ፤ ክሱን ፤ ከተነበበላቸው ፤ በኋላ ፤ ወንጀሉ ፤ ባልታወቁ ፤ ወንጀል ፤ ሰሪዎች ፤ የተፈጸመ ፤ መሆኑን ፤ አልካዱም ፤ እንዲሁም ፤ አቃቤ ፤ ሕግ ፤ ሁለት ፤ የክስ ፤ ምስክሮች ፤ ለክሱ ፤ የሚደግፉ ፤ አቅርቧል ።

የሠራየ ፤ አውራጃ ፤ ግዛት ፤ ፍርድ ፤ ቤት ፤ ነገሩን ፤ መርምሮ ፤ ይግባኝ ፤ ባዮች ፤ ጥፋተኞች ፤ ናቸው ፤ በማለት ፤ በአዋጁ ፤ መሠረት ፤ ፭፻ (አምስት ፤ በቶ ፤ ብር) ለመንግሥት ፤ ግምጃ ፤ ቤት ፤ ገቢ ፤ መቀጮ ፤ ስለ ፤ ፈረደባቸው ፤ የቀረበ ፤ የይግባኝ ፤ ቅሬታ ፤ ነው ።

ይግባኝ ፤ ባዮች ፤ ቅሬታቸውን ፤ ሲገልጹ ፤ ሳሉ ፤ በአዋጁ ፤ መሠረት ፤ የተፈረደባቸው ፤ መቀጮ ፤ ልንቀጣ ፤ አይገባም ፤ ምክንያቱም ፤ ገና ፤ ከሳሹ ፤ ያን ፤ ጊዜ ፤ በጥርጣሬ ፤ ሌሎች ፤ ሰዎች ፤ ከሱ ፤ ጋር ፤ ጠብ ፤ የነበራቸው ፤ ወንጀሉን ፤ የፈጸሙ ፤ እነሱ ፤ ይሆናሉ ፤ በማለት ፤ ለፖሊስ ፤ አመልክተው ፤ ስለነበረ ፤ እነኚህ ፤ ሰዎች ፤ በፖሊስ ፤ ስለተያዙ ፤ እኛም ፤ በፖሊስ ፤ ጣቢያ ፤ ዘንድ ፤ ተጠርተን ፤ ቀርበን ፤ በተጠየቅንበት ፤ ጊዜ ፤ የተያዙ ፤ ሰዎች ፤ ከግል ፤ ከሳሽ ፤ ጋር ፤ ጠብ ፤ ስለነበራቸው ፤ ምናልባት ፤ እነሱ ፤ ይሆናሉ ፤ በማለት ፤ መስከረው ፤ ስለ ፤ ነበረ ፤ ብቻ ፤ ነው ፤ የሚሉት ።

ለዚህ ፤ ክርክር ፤ አቃቤ ፤ ሕጉ ፤ ሲመልሱ ፤ ሳሉ ፤ እርግጥ ፤ ነው ፤ ይህ ፤ ወንጀል ፤ በተፈጸመበት ፤ ጊዜ፤ ፖሊሶች ፤ በጥርጠራ ፤ በርካታዎች ፤ ሰዎች ፤ ይዘው ፤ ነበር ፤ ነገር ፤ ግን ፤ የተያዙ ፤ ሰዎች ፤ የተባለውን ፤ ወንጀል ፤ የፈጸሙ ፤ ለመሆናቸው ፤ በቂ ፤ ማስረጃ ፤ ስላልተገኘ ፤ ተለቀዋል ። ስለዚህ ፤ ይግባኝ ፤ ባዮች ፤ በደንቡ ፤ መሠረት ፤ ጊዜ ፤ ተሰጥቷቸው ጥፋተኞቹን ፤ ስለአላቀረቡ ፤ የሠራየ ፤ አውራጃ ፤ ግዛት ፤ ፍርድ ፤ ቤት ፤ የሰጠው ፤ ፍርድ ፤ ትክክለኛ ፤ በመሆኑ ፤ በሙሉ ፤ እንዲጸናልኝ ፤ ብለዋል ።

እኛም ፤ የቀረበውን ፤ የክስ ፤ ምስክርነት ፤ በመዝገቡ ፤ ውስጥ ፤ የሰፈረው ፤ መርምረን ፤ የታጨደ ፤ ጤፍ ፤ ተበላሽቶ ፤ ምናምን ፤ ሆኖ ፤ መቅረቱን ፤ ተገንዝበናል ። እንዲሁም ፤ ምናምን ፤ ሆኖ ፤ የቀረ ፤ ጤፍ ፤ በአዋቂ ፤ ታይቶ ፤ ግምት ፤ ዋጋ ፤ ፪፻፴፩ (ሁለት ፤ መቶ ፤ ሠላሣ ፤ አንድ ፤ ብር) ፤ ለመሆኑና ፤ ባልታወቁ ፤ ወንጀለኞች ፤ በሌሊት ፤ የታጨደ ፤ ለመሆኑ ፤ ተረድተናል ።

ሆኖም ፤ ይግባኝ ፤ ባዮች ፤ ወንጀሉ ፤ በመንደራቸው ፤ ርስት ፤ ክልል ፤ የተፈጸመ ፤ መሆኑን ፤ አልካዱም ፤ እንዲሁም ፤ ወንጀሉን ፤ የፈጸሙትን ፤ ለማቅረብ ፤ በአዋጁ ፤ መሠረት ፤ ፲፭ ፤ ቀን ፤ ጊዜ ፤ በፖሊስ ፤ የተሰጣቸው፤ መሆኑ ፤ እና ፤ ግዴታቸውን ፤ ያልፈጸሙ ፤ መሆናቸውን ፤ ተገንዝበናል ።

ይህ ፡ አዋጅ ፡ በኤርትራ ፡ አስተዳደር ፡ ጊዜ ፡ የታወጀ ነው ፡ አጋጊው ፡ አዋጁን ፡ ለመደንገግ ፡ ያበቃው ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ በጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ የሚገኙት ፡ ገጠሮች ፡ ውስጥ ፡ ባልታወቁ ፡ ወንጀለኞች ፡ ይህን ፡ የመሰሉ ፡ ወንጀሎች ፡ በብዛት ፡ ይፈጸሙ ፡ ስለነበር ፡ አጋጊው ፡ ይህ ፡ ተግባር ፡ ለማጥፋት ፡ እና ፡ ለማቆም ፡ ያወጣው ፡ ልዩ ፡ አዋጅ ፡ በመሆኑ ፡ እነዚህ ፡ ወንጀሎች ፡ ገና ፡ በጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ ስለአሉ ፡ አዋጁ ፡ እንዲኖርና ፡ እግ ብር ፡ እንዲውል ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ፡ ብለናል ።

በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ ይህ ፡ ይግባኝ ፡ ተቀባይነት ፡ የለውም ፡ ብለናል ። ምክንያቱም ፡ ይግባኝ ፡ ባዮች ፡ በተ ከሰሱበት ፡ ዋጅአ ፡ መሠረት ፡ ይህን ፡ ወንጀል ፡ የፈጸሙት ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፡ ብለው ፡ ማቅረብ ፡ ግዴታ ቸው ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ በጥርጠራ ፡ ጠብ ፡ ስለነበራቸው ፡ እነዚሁ ፡ ይሆናሉ ፡ ብለው ፡ ንጹህን ፡ ዜጎች ፡ መወንጀል ፡ ተገቢ ፡ አልሆነም ።

እላይ ፡ የተዘረዘረውን ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ የሠራዩ ፡ አውራጃ ፡ ግዛት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ጥር ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፬ ዓ. ም. የሰጠው ፡ ፍርድ ፡ በሙሉ ፡ አጽንተነዋል ።

ከዚህ ፡ ፍርድ ፡ ግልባጭ ፡ ለሠራዩ ፡ አውራጃ ፡ ግዛት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይላክ ።

ይህ ፡ ፍርድ ፡ በድምጽ ፡ ብልጫ ፡ ዛሬ ፡ ሰኔ ፡ ፳፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፬ ፡ ዓ. ም. ሰጥተናል ።

፪ኛው ፡ ዳኛ ፡ አቶ ፡ ወልዱ ፡ በርሄ ፡ በድምጽ ፡ ብልጫ ፡ የተሰጠውን ፡ ፍርድ ፡ አልስማማበትም ፡ በማ ለት ፡ ተለይተው ፡ በአነስተኛ ፡ የሰጡት ፡ ፍርድ ።

## ፍርድ ።

ተከሣሾች ፡ ሰብሳ ፡ የተባለ ፡ መንደር ፡ ሽማግሌዎች ፡ በመሆናቸው ፡ በኤርትራ ፡ አስተዳደር ፡ ይሠራ በት ፡ የነበረው ፡ አዋጅ ፡ ቁ. ፱. እ. ኤ. አ. ፲፱፻፶ ፡ ዓ. ም. ያወጣው ፡ የተመለከተውን ፡ ተላልፈዋል ፡ በማ ለት ፡ በአዲ ፡ ውግሪ ፡ አውራጃ ፡ ፍ/ቤት ፡ ተከሰው ፡ ቀረቡ ፡ አዋጅ ፡ የአውጫጪኝና ፡ አፈርሣታ ፡ የአገር ፡ ሥሪት ፡ ሕግ ፡ ተመሳሳይ ፡ ነው ፡ ጥቅምት ፡ ፲፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፬ ፡ ዓ.ም. ስራው ፡ በተባለ ፡ ቦታ ፡ የመራጉዝ ፡ ወረዳ ፡ ግዛት ፡ ባልታወቁ ፡ ሰዎች ፡ የግል ፡ ከሳሽ ፡ አቶ ፡ ገብረሚካኤል ፡ ገብረአብ ፡ የሆነው ፡ ሰብል ፡ ጤፍ ፡ ስለታጨደ ፡ የመ ንደሩ ፡ ሽማግሌዎች ፡ በፖሊስ ፡ ፲፭ ፡ ቀን ፡ ጊዜ ፡ ተሰጥቷቸው ፡ ወንጀል ፡ የፈጸሙትን ፡ ሰዎች ፡ ለማስረከብ ፡ በተሰጣቸው ፡ ጊዜም ፡ ለማስረከብ ፡ በለመስማማታቸው ፡ በሕብረት ፡ መንደሩ ፡ አባል ፡ ነው ፡ በማለት ፡ የመን ደሩ ፡ ሽማግሌዎች ፡ እፍርድ ፡ ቤት ፡ ከሰው ፡ አቀረቡዋቸው ። ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርበው ፡ ጥፋተኞች ፡ አይደለ ንም ፡ ሲሉ ፡ አስመዝግበዋል ። የግል ፡ ከሣሹ ፡ ሰብል ፡ ጤፍ ፡ ታጨደብኝ ፡ ብሎ ፡ ላጨዱት ፡ ሰዎች ፡ ስማ ቸውን ፡ በመዘርዘር ፡ በአዲ ፡ ውገሪ ፡ ወረዳ ፡ ፖሊስ ፡ ክስ ፡ አቅርቦ ፡ ነበር ። ሽማግሌዎቹ ፡ በበኩላቸው ፡ በፖ ሊስ ፡ በተጠየቁ ፡ ጊዜ ፡ የግል ፡ ከሳሽ ፡ ስማቸው ፡ የተጠቀሱት ፡ ሰዎች ፡ በግል ፡ ከሳሽ ፡ መካከል ፡ በዚሁ ፡ ማሳ ፡ ጠብ ፡ ሳላላቸው ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ካልሆኑ ፡ በስተቀር ፡ ሌላ ፡ የምንጠረጥረው ፡ ሰው ፡ የለም ፡ ሲሉ ፡ አመልክተዋል ። በፖሊስ ፡ በተደረገው ፡ ምርመራ ፡ ውጤት ፡ ሳይሰጥ ፡ በመቅረቱ ፡ በግል ፡ ከሳሽ ፡ የተጠቀ ሱት ፡ ሰዎች ፡ ፖሊስ ፡ ትተው ፡ በመንደሩ ፡ ከሰሱት ። አውራጃው ፡ ፍ/ቤት ፡ አዲ—ውገሪ ፡ ኢት. ብር ፡ ፩፻ አምስት ፡ መቶ ፡ መቀጫ ፡ ተከሳሾች ፡ እንዲከፍሉ ፡ ወስነዋል ። በዚሁ ፡ ውሳኔ ፡ ላይም ፡ ይግባኝ ፡ ብለው ፡ ወደዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርበዋል ። የዚሁ ፡ አዋጅ ፡ ስለ ፡ ሕጋዊነቱ ፡ ክርክር ፡ ባይነሣም ፡ ክሱን ፡ መንግ ሥት ፡ የሚቃወምበት ፡ ምክንያቶች ፡ ቢገለጽ ፡ ለወደፊቱ ፡ ጠቃሚ ፡ ይሆናል ። ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ቁ. ፶፬ ፡ የሚደነግገው ፡ ቅጣት ፡ የሚፈጸመው ፡ አጥፊው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ሕጉ ፡ እንደሚፈቅደው ፡ ካል ሆነ ፡ ያደረገው ፡ ጥፋት ፡ ካልተረጋገጠ ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ አይቀጣም ፡ ይላል ።

ሕገ ፡ መንግሥት ፡ የአገሪቱዋ ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ በመሆኑ ፡ ማናቸውም ፡ ሕግ ፡ ድሮ ፡ ይሠራበት ፡ ያለ ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ ለወደፊት ፡ የሚወጣው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በሚያዘው ፡ መከተል ፡ ግዴታ ፡ ነው ።

ምንም ፡ እንኳ ፡ ትእዛዝ ፡ ቁ/፳፯/፶፭ ፡ ቁ. ፮. ፡ የተመለከተው ፡ "በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ ጸንተው ፡ የሚሠራባቸው ፡ ወይም ፡ የፌዴራል ፡ አቋም ፡ በመኖሩ ፡ ምክንያት ፡ የወጡት ፡ ሕጎች ፡ አዋጆ ችና ፡ ደንቦች ፡ በሙሉም ፡ ሆነ ፡ በከፊል ፡ የወጡት ፡ ለአስተዳደሩ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆነው ፡ እንዲሠራባቸው ፡ የሚያስፈልጉት ፡ ሁሉ ፡ ወደፊት ፡ በሚወጡ ፡ ሕጎች ፡ ተሠርዘው ፡ እስኪተኩ ፡ ድረስ ፡ እንዳሉ ፡ ጸንተው ፡ የሚሠራባቸው ፡ ይሆናሉ ፡ ያሉትም ፡ የአስተዳደር ፡ ድርጅቶች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ን. ነ. መንግሥት ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ሆነው ፡ እነዚሁ ፡ ሕጎች ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ መዋላቸውን ፡ እንዲቀጥሉ ፡ ይደረጋል ፡ ይላል ። ትእዛዙ ፡ በሚገባ ፡ ነው ፡ ምክንያቱም ፡ የነበረውን ፡ (ሕጎች) ደንቦች ፡ ድርጅትን ፡ የሥራ ፡ አመራር ፡ አቋም ፡ ከነበረው ፡ (ሕጎች) ደንቦች ፡ ተያይዞ ፡ ይሠራበት ፡ ስለነበረ ፡ በአዲስ ፡ ደምቦችና ፡ ሕጎች ፡ ወዲያውኑ ፡ ሲተካ ፡ የሥራ ፡ አመራርና ፡ አቋም ፡ ይሰናከላል ፡ በማለት ፡ ነው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ በተሰጣቸው ፡ ሥልጣን ፡ ከሕገ መንግሥት ፡ የሚጋጭ ፡ ደንቦችና ፡ ሕጎች ፡ ለይቶ ፡ በቀዳሚነት ፡ ማስወገድ ፡ ይኖርባቸዋል ።

ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ተከሣሾች ፡ በተከራከሩበት ፡ ነጥብ ፡ እንመለስ ፡ እ. ኤ. አ. ሐምሌ ፡ ፲፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፭ ዓ. ም. በኤርትራ ፡ አስተዳደር ፡ የወጣውን ፡ አዋጅ ፡ የአዋጁን ፡ መቅድም ፡ (ፕረአምብል) የሚለው ፡ "በገ ጠሮች ፡ ሆነ ፡ ብለው ፡ ወንጀል ፡ የሚፈጽሙ ፡ ሰዎች ፡ ሳይገለጹ ፡ በመቅረታቸው ፡ ይህንንም ፡ ምስክሮች ፡

ለፖሊስ ፡ በቀጥታ ፡ ባለማመልከታቸው ፡ ምክንያት ፡ ወንጀለኞች ፡ ከቅጣቱ ፡ ስለሚያመልጡ ፡” ይህ ፡ ከሆነ ፡ የአዋጁ ፡ ዓላማ ፡ የግል ፡ ከሣሽ ፡ የከሰሳቸው ፡ ሰዎች ፡ ስማቸውን ፡ ለይቶ ፡ በክሱ ፡ ከጠቀሰ ፡ ሽማግሌዎቹም ፡ የሚጠረጥሯቸው ፡ ሰዎች ፡ ካመለከቱ ፡ ማለት ፡ የመተባበር ፡ መንፈስ ፡ ካሳዩ ፡ ከአቅም ፡ በላይ ፡ የሚጠቀሙበት ፡ በፍጹም ፡ ሕጋዊ ፡ አይደለም ። በእኔ ፡ አስተያየት ፡ በአዲ ፡ ውግሪ ፡ በመዝገብ ፡ ቁ/፲፫/፷፬ ፡ ታህሳስ ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፬ ፡ ዓ. ም. በተከሳሾች ፡ ላይ ፡ የተሰጠውን ፡ ፍርድ ፡ በማይገባ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ በተከሰሱበት ፡ በነፃ ፡ እንዲ ለቀቁ ፡ በአነስተኛ ፡ ድምፅ ፡ ፍርድ ፡ ሰጥቻለሁ። ይህ ፡ ፍርድ ፡ ዛሬ ፡ ሰኔ ፡ ፳፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፬ ፡ ዓ. ም. ተሰጠ ።

እንደኔ ፡ አሳብ ፡ የዚህ ፡ የድምጽ ፡ ልዩነት ፡ ውሳኔ ፡ ለማወቅ ፡ ያህል ፡ ለክቡር ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ከፍተኛ ፡ ፍ/ቤት ፡ የበላይ ፡ ባለሥልጣን ፡ ሊቀርብ ይገባል ፡ ባይ ፡ ነኝ ።